# ምእራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

### 1.1 የስነ ግጥም አጀማመር

"ስነ ግጥም እንዴት ተጀመረ? መሰረቱ፣ መነሻው ምንድነው?" የሚለው ጥያቄ ለረጅም ዘመናት በተለያዩ ሊቃውንትና ምሁራን ሲነሳ ቆይቷል፤ በመነሳት ላይም ነው::
ጥያቄው ሲነሳ የቆየውም ሆነ በመነሳት ላይ ያለው በስነጽሁፍ ባለሙያዎች ብቻ ሳይሆን በሌሎች መስኮች ምሁራንም ጭምር ነው::

እዚህ ላይ የሚከተሉት ጥያቄዎች ይነሳሉ::

- የስነግጥም አጀማመር ለምን የተለያዩ መስኮችን ሊቃውንት ትኩረት ሳበ?
- ለምንስ ከጥንት ዘመን አንስቶ በተለያዩ ጊዜያተ ሲነሳ ቆየ?

ለዚህ ዋነኛነት የሚጠቀሱይ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው::

- ስነግጥም ከሰው ልጅ እድሜ ጋር የተቆራኘ በመሆኑ
- ከሰው ልጅ ጋር የተቆራኘ ነገር ደግሞ የሰውን ትኩረት መሳቡ ስለማይቀር

ምሁራኑና ሊቃውንቱ "ስነግጥም እንዴት ተጀመረ?" ለሚለው ጥያቄ የተለያዩ መላምቶችን ሲሰነዝሩ ቆይተዋል::
ከዚህም ውስጥ የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ::

1. የስነግጥም መነሻ ሃይማኖታዊ እምነት ነው::
   በጥንት ጊዜ ሰዎች የሚያመልኩባቸውን ነገሮች ለመማጸንም ሆነ ለማወደስ የሚያሰሟቸው ድምጾች ነበሩ::
   ድምጾቹም ወደ ቃላትና ሃረጋት እያደጉ ሄዱ::
   እነዚህ ድምጾችም ሆኑ ቃላቱና ሃረጋቱ ዜማዊ ነበሩ::
   ዜማዊነታቸውም ቀስ በቀስ ወደ ስነግጥምነት እንዲለወጡ እያደረጋቸው መጣ::

የስነግጥምን መነሻ ከሃይማኖታዊ እምነቶች በማሳለፍ ከክርስትና ሃይማኖት ጋር የሚያያይዙት ሰዎችም አሉ::

መዝሙረ ዳዊትን ለዚህ በምሳሌነት ይጠቅሳሉ::

ሆኖም ግን አጀማመሩን ከክርስትና ሃይማኖት አጀማመር ጋር የሚያያይዙት ምሁራን መልስ ሊያገኙላቸው ያልቻሏቸው በርከት ያሉ ጥያቄዎች አሉ::

ከነዚህም ውስጥ ዋነኛው:

"ስነግጥም የተጀመረው የክርስትና ሃይማኖት በአለም ላይ ከመሰበኩ በፊት ሆኖ ሳለ ሃይማኖቱ ለስነግጥም መነሻ የሚሆነው እንዴት ሆኖ ነው?" የሚለው ነው::

2. የስነግጥም መነሻው ስራ ነው::

በጥንት ጊዜ ሰዎች በጥንድም ሆነ በህብረት ስራን በሚሰሩበት ጊዜ ሃይልን በአንድ ጊዜ ለማሳረፍ ሲሉ የሚያሰሟቸው ድምጾች ነበሩ::

ለምሳሌ አንድን ድንጋይ ለመፈንቀል በአንድነት "ሆ. . .!" ብለው የሚያሰሙት ድምጽ ይጠቀሳል::

ድምጾቹም አጫጭርና ዜማዊ ነበሩ::

የድምጾቹ ዜማዊ መሆንም ቀስ በቀስ ወደ ስነግጥምነት እንዲለወጡ አድርጓቸዋል::

3. የስነግጥም ምንጩ ስሜት ነው::

የሰው ልጅ ጥንትም ቢሆን የደስታም ይሁን የሃዘን አንድ ቅጽበታዊ ስሜት ሲሰማው ስሜቱን ለመግለጽ ድምጾችን እና ቃላትን ያሰማ ነበር::

የሚያሰማቸው ድምጾች እና ቀላትም ዜማዊ ነበሩ::

የድምጾቹ እና የቃላቱ ዜማዊ መሆንም ቀስ በቀስ ወደስነግጥምነት እንዲለወጡ አደረጋቸው::

ለምሳሌ

- ኡ!፣ አ!፣ ሆ!፣ ወዘተ. የሚሉት ይጠቀሳሉ::

- እነዚህ ድምጾች ወደ ቃላተና ሃረጋትነት እየተለወጡ ሲመጡ ደግሞ "ኦ! አምላኬ፣ ምን መከራ ነው!፣ ሞተ እንዴ!. . ." እንደማለት እየሆኑ መጡ፡፡

4. የስነግጥም መሰረቱ ኩረጃ (Imitation) ነው፡፡
ጥንታዊው የሰው ልጅ በአካባቢው የሚሰማቸው ድምጾች ነበሩ፡፡
እነዚህ ድምጾችም ዜማዊ ነበሩ፡፡

ለምሳሌ በአማርኛው ብንወስድ

- ድንጋይ ሲፋጭ ሰምቶ፤ ኳኳ፣ ኳኳ፣ ኳኳታ፣ ኪል፣ ኪል ወዘተ.
- ግድግዳ ሲመታ ከሚሰማው ድምጽ በመነሳት፤ ግም ግም
- ወንዝ ሲፈስ በመስማት፤ ሿሿ፣ ሹዋ ወዘተ.

የሆነው ሆኖ ስነግጥም ጥንታዊ የሆነ የስነጽሁፍ ዘርፍ መሆኑን ከመናገር ስለአጀማመሩም መላምት ከመሰንዘር አልፎ የተጀመረው በዚህ ዘመን በዚህ መንገድ ነው ብሎ እቅጩን መናገር እንደማይቻል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡
ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ጥንታዊ በመሆኑ የተመዘገበ ነገር ስላልተገኘ አፍን ሞልቶ ለመናገር የሚያስችል መረጃ ባለመገኘቱ ነው፡፡

## 1.2 የስነግጥም ምንነት

ስነግጥም በእድሜው ከሁሉም የስነጽሁፍ ዘርፎች የበለጠ ጥንታዊ እንደሆነ ከፍ ሲል ተጠቁሟል፡፡
ስነግጥም በጽሁፍ ከመቅረቡ በፊት በቃል ሲባልና ሲዜም የኖረ ዘርፍ መሆኑ በእድሜው ከሰው ልጅ እድሜ አለመተናነሱን እና ጥንታዊ መሆኑን ይጠቁማል፡፡
ይህ ጥንታዊ የሆነ፣ ግን ከሰው ልጅ ህይወት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ የስነጽሁፍ ዘርፍ ምንነትም በየዘመኑ ከስነጽሁፍ ባለሙያዎች አልፎ ተርፎም የተለያዩ የጥናት መስኮች ምሁራንን (የፍልስፍና፣ የታሪክ፣ የስነሰብ፣ የህግ፣ ወዘተ) ስሜት ሲስብ ቆይቷል፡፡

እነዚህ የስነጽሁፍ ምሁራንም ሆኑ ሌሎች ምሁራን የተለያዩ ብያኔዎችን ሲሰጡትም ቀይተዋል::

በየዘመናቱ የተለያዩ ብያኔዎች ሲሰጡ ከቆዩባቸው ምክንያቶችም ውስጥም:

- በየዘመናቱ የኪነጥበብ አተያይ መለያየት የተነሳ ሁሉም ከየዘመኑ አኳያ ብያኔ መስጠቱ
- ብያኔ ሲሰጡ የቆዩት ባለሙያዎች የትምህርት መስክ መለያየት
- ሁሉም ብያኔ ሰጭ ለየራሱ ማድላቱ
- እያንዳንዱ ገጣሚ እና የስነጽሁፍ ባለሙያ የየራሱ የስነጽሁፍ ይትብሃልና አተያይ ያለው በመሆኑ ሁሉም ከራሱ ረገድ መመልከቱ
- ስነግጥም የተለያዩ የይዘት ገጽታዎችን ማቀፉ
  ምሳሌ "ስነግጥም ቤት የሚመታ የአገላለጽ ስልት ነው" ቢባል ለመሆኑ "ቤት የሚመታው ሁሉ ስነ ግጥም ነውን?" የሚል ጥያቄን ያስነሳል::

የሚሉት ይጠቀሳሉ::

በዚህም የተነሳ አንድ ወጥ ብያኔ ለማግኘት አልተቻለም::
ሆኖም ለረጅም ዘመናተ ምሁራን ለስነግጥም ብያኔዎችን ለመስጠት መሞከራቸው አልቀረም::
በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ የትምህርት መስኮች ሊቃውንት ከተሰነዘሩት ብያኔዎች ውስጥ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ::

- ምርጥ ቃላትን በምርጥ ቦታቸው ማስቀመጥ ነው::
- ሰፊ ልምድንና ህይወትን በሙዚቃዊ ቃና መግለጽ ነው::
- ምት ያለውና የብርቱ ስሜት መግለጫ ነው::
- የጠንካራ ስሜቶች ከውስጥ ገንፍሎ መውጣት ነው::
- በሌላ መንገድ የማይገለጽን እና ሊባል የማይቻልን ነገር የሚያቀርብ ነው::

- ደስታን ከእውነት ጋር አጣምሮ ማቅረብ ነው::
- ቤት የሚመታ የአገላለጽ ዘዴ ነው::
- በስነግጥማዊ እውነትና ውበት ድንጋጌ ላይ የተመሰረተ የህይወት ሂስ ነው::

ከዚህ በላይ ከቀረቡት የግጥም ብያኔዎች የምንገነዘበው ለስነግጥም አንድ ብያኔ መስጠት አለመቻሉን ነው::

ከፍ ሲል የተጠቀሱንት ነጥቦች መነሻ በመድረግም ለስነግጥም ብያኔ ለመስጠት መሞከርን አጠንክረው የሚሞግቱ ምሁራን እና የስነጽሁፍ ሊቃውንት ይገኛሉ::

ከነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ::

1. ጸጋዬ ገብረመድህን

   "የስነ ግጥምን ድንጋጌ ይሄኛው አይነት ብቻ መሆን አለበት፤ ወይም ደግሞ ከዚህኛው የቋንቋ መሰረት ድንጋጌ በተወረሰው አይነት ብቻ መመራት አለበት ብሎ መወሰን ያው ከተወሰነ አእምሮ የሚመጣ ድፍረት ነው::"

2. ሀሪሾው

   ስነግጥም የተለያዩ የቅርጽ፣ የይዘት፣ የግብ እና የቴክኔክ ገጽታዎችን ስለሚያቅፍ አንድ ወጥ ብያኔ ሊሰጠው አይችልም::

ስለሆነም ለስነግጥም ሁልአቀፍ የሆነ አንድ ወጥ ብያኔ ለመስጠት ከመሞከር ይልቅ የስነጽሁፍ ዘርፉን የቅርጽና የይዘት ሁኔታውን የሚያሳዩ ባህሪያቱን ለማሳየት መሞከሩ ይሻላል::

## *1.3 የስነግጥም አስፈላጊነት*

*ስነግጥም ለሰው ልጅ ከፍተኛ አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል:: በመስጠትም ላይ ይገኛል::*
*ከነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ::*

1. *ማህበራዊና ባህላዊ የህይወት ገጽታን ለመግለጽ ያስችላል::*

*የሰው ልጅ:*

- *የሚኖርበትን አካባቢ ከሚገለጽባቸው*
- *ማንነቱን ከሚያንጸባርቅባቸው*
- *ማህበራዊና ባህላዊ ህይወቱን ከሚያስተላልፍባቸው መንገዶች*

*ውስጥ አንዱ ስነ ጽሁፍ ነው::*

*ስነ ግጥምም የስነ ጽሁፍ ዘርፍ በመሆኑ ይህንን ይጋራል::*

2. *ፈጣንና ቅጽበታዊ ስሜቶችን ለማንጸባረቅ ይረዳል::*

*የሰው ልጅ ከሌሎች እንስሳት ከሚለይባቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ስሜታዊነቱ (ስሜቱ በተለያዩ ነገሮች መነካቱ) እና ስሜቱን ማንጸባረቁ ነው::*

*በአስደሳችና በአሳዛኝ፣ በሰናይና በእኩይ ተግባራት ስሜቱ ይነካል::*

*በሀዘን ጊዜ ውስጡ ይጨነቃል፤ በደስታ ጊዜ ውስጡ ይፈነድቃል::*

*ተቃራኒ ነገሮች ሲገጥሙት ተቃራኒ ስሜቶች ይፈራረቁበታል::*

*የሚፈራረቁበትንና የሚሰሙትን ስሜቶች በውስጡ አፍኖ በመያዝ ፋንታ ለመተንፈስና ከጭንቀቱ ለመገላለል ይፈልጋል::*

*ስሜትን ተንፍሶ ለመገላገል ከሚያስችሉት ነገሮች ውስጥ አንዱ ደግሞ ስነጽሁፍ ነው:: ስነግጥምም በስነጽሁፍነቱ የሰው ልጅ የሚሰሙትን ፈጣን፣ ልውጣ ልውጣ የሚሉ ስሜቶች ለማስወጣት (ለመተንፈስ) ያገለግላል::*

*ጠንካራ፣ ፈጣን፣ ትኩስ ስሜቶች ከምንም በላይ በስነግጥም ይገለጻሉ::*

3. የአድማጭን ወይም ተቀባይን ስሜት በቀላሉ ለመሳብና ለመግዛት ያግዛል፡፡

ስነግጥም በሌላኛው ሰው ውስጥ:

- ፈጣን እና ቅጽበታዊ
- ትኩስ
- ጠንካራ

ስሜቶችን ለመፍጠር፣ ስሜትን ቀስቀሶ ወደ ተግባር ለማሸጋገር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ ለምሳሌ: የፉከራ፣ የቀረርቶ፣ ወዘተ የሰውን ስሜት የማነሳሳት ሃይላቸውን ከፍተኛ መሆን አንዱ ምክንያት ግጥማዊነታቸው ነው፡፡

የእናት ሃገር ጥሪዎች

- የጦርነት
- የረሃብ
- የበሽታ
- የድህነት ወዘተ

በስነግጥም መልክ የመቅረባቸው ዋነኛ ምክንያትም ስነግጥም ስሜት ቀስቃሽና ለተግባር የሚያነሳሳ መሆኑ ነው፡፡

4. እውቀትን ያጎለብታል፡፡

የስነጽሁፍ ባለሙያዎች (ጸሃፊያንና ሃያሲያን) ስለስነጽሁፍ ተግባር ካላቸው አመለካከት አኳያ በሁለት ይከፈላሉ፡፡

- ኪነት ለኪነት
- ኪነት ለእውቀት (ለማስተማር)

"እዚህ ላይ የትኛው የበለጠ ተቀባይነት ይኖረዋል?" የሚለው ጥያቄ ሊጤን ይገባዋል፡፡ ያም ሆነ ይህ እውቀት ከሚተላለፍባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ ስነጽሁፍ ነው፡፡ ስነግጥምም በስነጽሁፍ ዘርፍነቱ እውቀትን በማስተላለፊያነት ያገለግላል፡፡

ስነግጥም፡

- በገጣሚው አተያይና ምናባዊ ምልከታ ላይ ተመስርቶ ስለሚቀርብ
- ስሜትን በሚነካና በሚመስጥ መልክ ስለሚቀርብ
    - ስለአለም
    - ስለአካባቢ
    - ስለማህበረሰብ

እያዋዙና እያስደሰቱ ለማሳወቅ ያገለግላል፡፡

ሆኖም፡

> "ስነግጥም ሁልጊዜ የሚጻፈው አዲስ እውቀትን ለማስተላለፍ ነው" ብሎ ማሰብ ተገቢነት የለውም፡፡

ለዚህም በዋናነት የሚጠቀሱ ምክንቶች አሉ፡፡

ዋነኛው ምክንያት ግን፡

- ስነግጥም በዋነኛነት የሚጻፈው የራስን ስሜት ለመተንፈስ መሆኑ ነው፡፡

5. በራስ መንገድ የመተርጎምንና የመመርመርን አድማስ ያሰፋል፡፡

በስነግጥም የሚተላለፍ ነገር ሁሉ ግልጽ ላይሆን ይችላል፤ ትርጉሙም ፈጥጦ ላይታይ ይችላል፡፡

አንዳንድ ገጣሚያን የሚያቀርቧቸውን ሃሳቦች የሚያቀርቡት ከተለመደው መንገድ ዘወር በማድረግ ነው፡፡

በመሆኑም ስነግጥም እያንዳንዱ አድማጭ ወይም አንባቢ በራሱ መንገድ፣ በራሱ ገጠመኝ የሚመረምረው፣ የሚተረጉመው ጭምር ነው፡፡

ለዚህም የስነግጥም ይዘት ዋነኛ ማስተላለፊያ የሆነው ተምሳሌታዊ ዘይቤ ይጠቀሳል፡፡

በመሆኑም የሰዎችን ውስጥን የሚያናውጥ ሰሜትን

- ስሜትን በሚገዛ
- ስሜትን በሚይዝ መንገድ የተላለፈን ነገር
- በራስ ስሜትና መንገድ ማየትን
- መመልከትን
- መግለጽን
- የተገለጸውንም በራስ መንገድ መተርጎምን

ስለሚጠይቅ የመመራመር አድማስን ያሰፋል፣ አእምሮን ያጎለብታል።

6. ስሜትን ኢዘርዛሪ በሆነ መንገድ ለማስተላለፍ ያገለግላል።

ስነግጥም ከስድ ጽሁፍ የበለጠ ስሜትን ኢዘርዛሪ እና ክት በሆነ መንገድ ለማስተላለፍ ያገለገላል።

## 1.4 የስነግጥም መለያ ባህሪያት

የስነጽሁፍንም ሆነ የስነጽሁፍ ዘርፎችን ምንነት በሚመለከት አጭር ብያኔ ለመስጠት አስቸጋሪ እንደሆነ የስነጽሁፍ ባለሙያዎች እንደሚገልጹ ከነምክንያቶቹ ከላይ ተጠቁማል።
አጭር ብያኔ ለመስጠት ከመሞከር ይልቅ ከመለያ ባህሪያቱ ረገድ መመርመሩ እንደሚሻልም ከላይ ተጠቁሟል።
በእርግጥም አንድ ወጥ ብያኔ ለመስጠት ከመሞከር ይልቅ ከመለያ ባህሪያቱ ረገድ መመርመሩ ይሻላል።

ለዚህም ዋና ዋና የሚባሉት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

- አንድ ስነግጥም የሚገኝበትን ደረጃ ለማመላከት የሚያስችሉ መስፈርቶችን ለማውጣት ስለሚያግዝ
- በአንድ ስነግጥም ላይ በአንድ ሰው በተለያዩ ጊዜያት የሚሰጠውን ሂስ የበለጠ ተጨባጭ ለማድረግ
- በአንድ ስነግጥም ላይ በተለያዩ ሰዎች የሚሰጠውን አስተያየት የበለጠ ተጨባጭ

ለማድረግ

- ስነግጥም "ይህን ያሚላል ይህን አያሚላም በሚል ለክቶ የሚገኝበትን ደረጃ ለማመልከት
- በስነግጥም ላይ የሚሰጠውን ግምገማና ሂስ ከግላዊ ይልቅ ተጨባጭነትን እስንዲላበስ ለማድረግ
- ለገጣሚያንም ሆነ ለተመራማሪዎችና ለሃያሲያን አንድ ስነግጥም ጥሩ የሚባለው ምን ሲያሚላ እንደሆነ ተጨባጭ ጥቆማ እና መመዘኛን ለማስገኘት

በዚህ መነሻነትም ስነግጥም ከሌሎቹ የስነጽሁፍ ዘርፎች ጋር የሚጋራቸው እና የግሉ የሆኑ መለያ ባህሪያት አሉት።

ከሌሎች የስነጽሁፍ ዘርፎች ከሚጋራቸው ባህሪያቱ ውስጥ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ።

- የፈጠራ ስራ መሆኑ
- በቋንቋ መቅረቡ
- በሰው ልጅ ህይወት ላይ መመስረቱ
    - የስነግጥም ዋነኛ ትኩረተ እንደሌሎች የስነጽሁፍ ዘርፎች ሁሉ የሰው ልጅ ህይወት ነው።
    - የሰውን ልጅ የእለት ከእለት ህይወት በገጣሚው ምናብና አመለካከት ረገድ ስሜት በሚነካ፣ በሚመስጥና በሚያስደስት ስልት ያቀርባል።

ከሌሎች የስነጽሁፍ ዘርፎች የሚለይባቸ ዋና ዋና ባህሪያቱ ውስጥ የሚከተሉት ናቸው። የእነዚህ ባህሪያት የግጥም ግላዊ ባህሪነት ደረጃ እንደሚለያይ ግን ልብ ማለት ያሻል።

ሀ. ኢዘርዛሪነት (ክትነት)፡

ኢዘርዛሪነት በጥቂት ቃላትና ሃረጋት ሰፊ ሃሳብን መግለጽን ይመለከታል።

ለስነግጥም ኢዘርዛሪት የሚከተሉት ማስረጃዎች ይጠቀሳሉ።

- የሚመረጡት ቃላትና ሃረጋት ሰፊ ሃሳብን የሚያስተላልፉ ናቸው::
- በአብዛኛው በውስጡ አያያዥ ቃላትና ሃረጋት አይኖሩትም::
- ብዙውን ጊዜ የትረካ ወይም የዘገባ ቃላትና ሃረጋት (እንደገለጸውም፣ እንዳስረዳውም፣ አለች፣ አለ ወዘተ. የሚሉ) አይኖሩም::
- በዙውን ጊዜ ማሰሪያ አንቀጾች የሉትም::
- በአብዛኛው የምክንያትና ውጤት ጣጣ መግለጫዎች (ማብራሪያዎች እና ትንተናዎች) አይኖሩም::
    - ይህ በውስጥ ታዋቂነት የሚቀር ነው::
    - ይህንን ክፍተት የሚሞሉት አንባቢያን ወይም አድማጫች ናቸው::
- በርከት ያሉ ባለታሪኮች አየኖሩም::

በነዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች መነሻነት ስነግጥም ከቴሌግራም ጋር ይመሳሰላል::

የሚከተሉት ግጥሞች ለኢዘርዛሪነት በምሳሌነት ይጠቀላሉ::

1. በእህል ከውሃ ሌላ
የሰው የመኖር ትርጉም
የሰው የመኖር መላ
አንድም ለካ በትዝታ
በትዝታና በተስፋ::
(ፈቃደ፡ ጩኸት 05)

2. ዘመዴን ስስመው
ጉንጩ ቢሻክረው
እኔንም ሻከረኝ
እድሜ መለስለሱ ማብቃቱ ታወቀኝ::
(ደበበ ሰይፉ፡ *የብርሃን ፍቅር*)

3. ወረት

ነይ ነይ ነይ ነይ
አነቃት
ሂጂ ነይ ሂጂ ነይ
ነቀነቃት::
ሂጂ ሂጂ ሂጂ ሂጂ
ለቀቃት

(ታገል ሰይፉ: *ቀፎውን አትንኩት*)

4. ጋሬጣና አሽሚጣጭ አንድ ነው ባህሪያቸው
የሚያልፈውን ሁሉ በመቦጨቃቸው
ጋሬጣስ በጭቆ ያስቀራል በጥሶ
አሽሚጣጭ ክፉ ነው ይከተላል ነክሶ::

(ከበደ ሚካኤል)

5. የቋጥኙ ላይ ሬሳ
የዚያ እምቦሳ
የካሳ
በመቶ አመቱ ቢያገሳ
ስንቱን ስንቱን ቀሰቀሰውሳ::

(ሰይፉ መታፈሪያ)

6. የህይወት እንጉርጉሮ
ሙዳ ስጋዬ ወድቆብኝ
መሬት
አፈር አንስቶብኝ
እንዳልበላው አሸዋው

እንዳልተወው ስጋው::

ህይወት! ህይወት!

እንቆቅልሽ ህይወት

ፍችም የላት::

(ሰይፉ መታፈሪያ፡ 1964፡ 31)

7. ለምን ሞተ ቢሉ

ለምን ሞተ ቢሉ

ንገሩ ለሁሉ

ሳትደብቁ ከቶ

"ከዘመን ተኳርፎ

ከዘመን ተጣልቶ"

(ደበበ ሰይፉ፡ የብርሃን ፍቅር ቅጽ ሁለት)

ለምሳሌ ያህል "ወረት" የሚለውን ግጥም ከኢዘርዛሪነት ባህሪ ረገድ ብንመለከተው የሚከተሉትን ነጥቦች ማንሳት ይቻላል::

በግጥሙ ውስጥ

- አያያዥ ቃላት የሉም::
- የጊዜ ቅደም ተከተሉን የሚጠቁሙ አገላለጾች (በመጀመሪያ፣ ቀጥሎም፣ ከዚያ በኋላ፣ ወዘተ. የሚሉ) የሉም::
- የዘገባ ቃላትና ሃረጋት አይገኙም::
- በጣም ጥቂት ቃላት (አምስት ብቻ) ቢገኙም በቃላቱ የተላለፈው ሃሳብ ግን በጣም ሰፊና ብዙ ገጾች የሚባልበት ነው::
- የወረትን ምንነት ቅልብጭ ባለ መንገድ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው::

እዚህ ላይ ግን አጫጭር የሆኑ ግጥሞች ምንጊዜም ኢዘርዛሪዎች፣ ረጃጅም የሆኑት ደግሞ

ዘርዛሪዎች ናቸው ማለት አለመሆኑን ልብ ማለት ያሻል፡፡

ለ. ከፍተኛ እና ፈጣን የሆነ ስሜትን የመንካት፣ ምናብን የመፍጠር፣ ምስልን የመከሰት ሃይል አለው፡፡

ጥሩ የሚባል ግጥም የአድማጭን ስሜት የመንካት፣ ምናብን የማጫር ሃይሉ ከሌሎች የስነጽሁፍ ዘርፎች ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ነው፡፡

ይህንን ሃይሉን የሚጎናጸፈውም በውስጡ ከሚገኘው የላቀና የመጠቀ የቋንቋ ገጽታ ነው፡፡

በውስጡ የሚገኘው ቋንቋ፡

- ደረጃው የላቀ
- በዘይቤዎችና በልዩ ልዩ አገላለጾች የተሞላ

ነው፡፡

ይህም ከላይ የተጠቀሰውን ባህሪውን ያላብሰዋል፡፡

የቋንቋ አጠቃቀሙ እንደ ግጥሙ የድባብ ሁኔታ

- ያስለቅሳል፡፡
- ያስቃል፡፡
- አንጀት ይበላል፡፡
- ለድርጊት ያነሳሳል፡፡
- የስሜት ድባብን ይፈጥራል፡፡
- ምናብን ያሰላል፡፡

ይህ የሚሆነውም ስነግጥም፡

- አእምሯዊ
- ስሜታዊ
- ምናባዊ

በመሆኑ ነው::

በአጠቃላይ

- የስሜት ድባብን ይፈጥራል::
- የምናብ መስላትን ይፈጥራል::

ይህ ሁሉ የሚሆነውም በውስጡ ከሌሎች የስነጽሁፍ ዘርፎች የላቀ የቋንቋ አጠቃቀም ያለው በመሆኑ ነው::

ከላይ የተጠቀሱት ሁሉ ከቃላት አመራረጡ፣ ከዘይቤ አመሰራረቱ እና ከሌሎች ልዩ ልዩ ቴክኒካዊ ጉዳዮች ይመነጫሉ::

የሚከተሉት ግጥሞች ለዚህ ጥሩ ምሳሌዎች ይሆናሉ::

**1.** ............................

የእናትነት ፍዳ
አምጣ ተስፋዋን ወልዳ
ድንገት እሬሳ ሆኖባት በበድኗ ሬሳ አቅፋ
"ተስፋዬን አልለቅም" ብላ ከሞት ጋር ስትሟገት
በሙጥኝ ልጇን ስታነባ
"አቤት ሰብእና!" እሚያሰኝ የእኛ መቀጫ
ህጻንን አቅፎ፣ ከረሃብ አመልጥ ብሎ፣ በሰለለ እግር ሩጫ፣
የኮረም ፍዳ
የሀገሬ እዳ
የእኔ ሰቆቃ
የሬሳ ክምር
የእንባ ናዳ::
ጥሬ እንደተበተነለት ጫጩት
ወይም እንደውሻና አጥንት

እህል ሲያይ ግር ብሎ ሰው ሰውነቱን አጥቶ
እንደ እንስሳ በእህል እይታ
ግር.ር.ር.ር.ር.ር.ታ።
አዛውንቱ ክብሩን አጣ
አንገቱን ቆልምሞ
ጥርሱን አግጦ፤
እጆቹን ሁለት እግሩ መሃል አቅፎ
በየስርቻው ተደፋ ሰውነቱን ተደግፎ።
ብቻ! ብቻ!
እሱ
ስድስት ፍሬ ባቄላ
በምጣድ ሙሉ ሲቆላ
ክትፎ እንምረጥ እኛ
ቁርጥ እንቁረጥ እኛ
ወሬ እናውራ
እንመቻች እንጣለፍ፤ በስልጣን ለስልጣን እኛ
………………………………………………….

**2.** "ያንዬ ነው"

ጸሀይ በሹል የጠራራ ጥርሶችዋ!!
ቁልቁል ነዋሪ ፍጡር ስትወጋ
ህይወት በሀሩር ጨርቅ ሲጠቀለል
በአሸዋ እሳት ሲቀበር
ምድር ስትቀልጥ
ህይወት ፈሳሽ፣ ህይወት ደረቅ ሲቅለጠለጥ
አዝእርት ደርቀው በንነው የመሬት ጸጉር ሲመለጥ
የፍጡራን ደም በጸሀይ እሳት ሲነጥር

ህይወት በጸሃይ ብረት ድስት ሲፈላ!
ፈሳሽ እንደተፈጥሮ አመሉ
ውሃ ውሃ ሽቅብ እያገ
ሲዘቅጥ ወደታች፣ ወደታች እውነተኛ ገላ አተላ፡፡

..................................................

በሌላ በኩል ደግሞ ስርአቱ ተለውጦ
ጸሃይ እስከ ሙቀት እስከ ብርሃኑ በቅዝቃዜ ዜና፣ በጨለማ
ተውጣ፡፡
ሰማየ ሰማያት አኩርፎ
በጉም በዝናም በረዶ ጎርፍ ጎርፎ፡፡
መብረቅ ነጉድጓድ
በቋፍ ያለው የመሬት ዳቦ
አፈር ድንጋይ ተንዶ
ድርቀትን በርጥበት በመለወጥ ተፈጥሮ ከብሮ ነግዶ

ውርጭ፤
የብብት ስር ለስላሳ እባጭ
ባካል ውስጥ ስር ሰዶ
በደም ቦይ ውስጥ ሲወራጭ፤

በረዶ፤
ያጥንት ውስጥ ፈሳሽ አንጓ
ሲታገል ድንጋይ ሊያደርገው
ሊያረጋ
ሲዋጋ፡፡

በሽታ፤

የሞት መደበቂያ

መጠቅለያ ሹራብ ጋቢ ኩታ፤

በፍርደ ገምድል ጥርሶቹ

የግፍ ደም በሰራቸው አይኖቹ

የሰውን ልጅ ቡቃያ ሲያየው

ሲያኝከው ሲቀጭ ሲያጭደው::

አንዱ ከጥርሱ ውስጥ

እየተሳሳተ ሲያመልጠው

በእልፍ አእላፍ የሚቆጠር

ህይወት አያሌ ገንዘብ

በህመም በደዌ ማእበል

አልቋል በበሽታ ሰበብ::

ጦርነት፤

ውጊያ የእልቂት መሸር አዝመራ

መከራ ደዌ ልብሱ፣ ጥፋት ትራሱ

ለህይወት የማይራራ

ያለምን ፊት የተለተለ

ውበቱንም ያጠፋ

የበጋ ጸሃይ በጥርሱ

ህይወትን ሳይወጋጋ

ክረምት መቅሰፍትነቱን ሳያዘናጋ

በሽታም ሆነ ጦርነት ሁለቱ

ለዘላቂነቱ ድል ሲመቱ::

ጥሩ ምግባር ለጥሩነቱ እንጂ

ለጽድቅ ለዋጋ መሆኑ ሲቀር
ያንዬ ነው የህይወት ሙሉነቱ
የንጹህ የፍጹምነት ምስጢር
ያንዬ ነው! ያንዬ ብቻ ነው!

የግጥሙ ስሜት ነኪነትም ሆነ ምናብ ጫሪነት የሚወሰነው ግን በአንባቢው ወይም በአድማጩ ምናባዊነትና የህይወት ልምድ ጭምር መሆኑን ልብ ማለት ይገባል፡፡

ሐ. የአጻጻፍ ነጻነት ያለው የስነጽሁፍ ዘርፍ ነው፡፡

ስነግጥም ከሌሎቹ የስነጽሁፍ ዘርፎች የበለጠ የአጻጻፍ ነጻነት አለው፡፡

የአጻጻፍ ነጻነቱ ከሚከተሉት ነጥቦች ረገድ ይታያል፡፡

- ከድምጾች
- ከቃላትና ከሃረጋት ቅርጽ
- ከቃላትና ከሃረጋት ቅደም ተከተላዊ አሰላለፍ

ገጣሚያን ይህን የሚያደርጉባቸው ምክንያቶች ብዙ ናቸው፡፡

ከነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

- የተለየ ግብን መምታት ሲፈልጉ
- የተሻለው መንገድ ይህ ነው ብለው ሲያምኑ
- የሚያዋጣኝና የሚሆነኝ የስነጽሁፍ ስልት ይህኛው ነው ብለው ሲወስኑ
- በስነግጥማቸው ውሰጥ አንድ ፋይዳ ወይም ረብን ሲሹ

i. በስነግጥም ውስጥ አንዳንድ ጊዜ በቃላት ውስጥ የሚገኙ ድምጻች የተለመደ ቅርጻቸውን ለውጠው ሊገኙ ይችላሉ፡፡

ለዚህም ገጣሚው የራሱ ምክንያት ሊኖረው ይችላል፡፡

ምክንያቱን መርምሮ፣ ለግጥሙ የሰጠውን ፋይዳ ተንትኖ መመልከቱ ግን የአንባቢው ወይም የአድማጩ ድርሻ ነው፡፡

የሚከተለው የመንግስቱ ለማ ግጥም ለዚህ በማስረጃነት ይጠቀሳል።

ሹመት
(ውስጠቀ ግጥም)

ካላጨበጨቡ
ወይ ካልቸበቸቡ
ወይም ካልሰረቱ
ወይ ካላሰረቱ
ወይ ካላሳበቱ
ማ ለማ ያቀምሳል ከዚያ ከሱረቱ?
(ባሻ አሸብር በአሜሪካ፣ 05)

ii. ገጣሚያን በግጥሞቻቸው ውስጥ ቃላትን ከተለመደ ቅርጻቸው ለውጠው ሊገለገሉባቸው ይችላሉ።
እነዚህ ቃላት ግን ግጥሙ ከቀረበበት ቋንቋ ፍጹም ያፈነገጡ፣ ፍጹም ገጣሚው በራሱ የሚፈጥራቸው መሆን የለባቸውም።
ይህ ከሆነ ገጥሙ ውበቱን ያጣል፤ አሰልቺ፣ አንብቡኝ አንብቡኝ የማይል ይሆናል።
አንባቢያን የቃላቱን መነሻ ፈልገው፣ ይህኛው ቃል ከዚህኛው ቃል ላይ የተመሰረተ ነው ብሎ ለመናገር የሚያዳግቱ መሆን የለባቸውም።

የሚከተሉት ግጥሞች ለዚህ በምሳሌነት ይጠቀሳሉ።

1. ልጅቱ የዘመነችቱ
ልጅቱ የዘመነችቱ
ጧቱን ብድግ ንስት
ትለውና

ፊቷን ትጥብ እሽት
ፍትግ ፍትግትግ
ዱሩላዋን ልቅቅ ጥፍት
ሌላ ምናምን ዱቅት
ሽፋሏን ቅልም ጥቁርት
ከንፈሯን ቅብት ቅልት

ታደርግና፣

ልጅቱ የዘመነችቱ

ሱሪዋን ለምቦጫሙን ሱርት
ጫማዋን ነጠላውን ጭምት
ቀበቶዋን ሰፊውን ቅብትት
ጃኬቷን የቆዳውን ጅክት
ታደርግና፣
ልጅቱ የዘመነችቱ
መስቷቱ ትልቁ መስቷት ፊት
ትቆምና፣
ሳቅ ግጥጥ. . .ሳቅ ግጥጥ. . .ሳቅ
ደርሶ ፍልቅ. . .ፍልቅልቅ. . .ፍልቅልቅልቅ
ከንፈር ገጠም. . .ደሞ ከፈት. . .
ደሞ ገጠም. . .ገጠምጠምጠም
ወደ ኋላ ሂድት. . .ሂድት
ደሞ ምልስ. . .ምልስ. . . ምልስልስልስ
ሽንጧን ሰበር. . .ቅልስ. . .ቅልስልስልስ
ዳሌዋንም ውዝ ውዝ
ቂብ ቂብ. . .ቁንን ቁንን
ክው ክው. . .ጅንን ጅንን
ደሞ ፈገግ. . .ደሞ ቅጭም. . .ቅጭምጭምጭም
አይኗን ከፈት. . .ደሞ ጨፈን. . .ስልምልምልም

ደሞ ጉርጥ. . .ደሞ ጥቅስ. . .ደሞ ጉልጉል
በራሷ ትቀልድ ይመስል
ልጅቱ የዘመነችቱ
ፕሮቫው ብሎ ጥቅልል
ወደ ቁርሷ መለስ ስትል
እማማዋ ንድድ ቁጥት
ትንሽ እህቷን ጥርት
በኩርኩም ግጭት
"ገና ካሁኑ ይወጣብሽ
ለምነው ጣት መነሳትሽ?"
ደሞ ማለት፡፡
አባባዋም እዝን ቁጭት
ጸሎያቸውን ዝንግት
"ወይ ጉድ መበላሸት"
አርዝመው እያዩ ማለት፡፡
ልጅቱ የዘመነችቱ
ገራብ ገራብ እያለች
እማዬዋን እያሳቀለች
አባዬዋን እየገረመመች
ቦርሳዋን እንደ ቦረሰች
ላስቲክ ብጤ ነገር ባፏ እያላመጠች
እያንቀጫቀጨች
ርፍድ ብሎባት ችኩል ችኩል እያለች
እሁድ ጧቱን ባንድ ሰአት ውልቅ ያለች
አፍታም ሳትቆይ ወዲያውኑ
ሰኞ ጧቱን ምልስ ትላታለች፡፡
ልጅቱ የዘመነችቱ፡፡
(ደበበ ሰይፉ፡ የብርሃን ፍቅር: 44 - 45)

ከዚህ በላይ በቀረበው ግጥም ውስጥ ከዚህ በታች የተመለከቱት ቃላት በግጥም የነጻነት ባህሪ ላይ በመመስረት የተዋቀሩ ናቸው::

- ዱቅት
- ጥቁርት
- ሱርት
- ቅብትት
- ጅክት

2. የጧቱ ጎህ በገፍ
   ወርቃማው የብርሃን ጎርፍ
   አፈር ቅጠሉን ሲያጥለቀልቀው
   እና ሲያብጫጫው
   እና ሲያቀላላው
   ሌላ ትሆናለች ህይወት
   በዚያው በድህነት መልካ ያማረች
   በልዩ ልዩ ቀለማተ የተሸበረቀች::

በግጥም 2 ውስጥ ገጣሚው የአጻጻፍ ነጻነቱን በመመርኮዝ የተገለገለባቸው ቃላት ይገኛሉ:: እነሱም

- ሲያብጫጫው
- ሲያቅላላው
- የተሸበረቀች

የሚሉት ናቸው::

3. ሀ. . .ም

ጊዜም እንደዘበት አስቀምጦን ንጉድ
አይናችን እያየ፣ ልጅነትም እርፍድ
ይገርማል አንችዬ
አ. . .ዬ!
በህይወት ጎርፍ ላይ አንችም እኔም እሱም
ጭልጥ አልነው፣ አልነው እል. . .ም
ሳናጠነጥነው፣ ሳይመለስ ዳግም
አቤ. . .ት
አራት አመት እንደዘበት
የድሚያችን ልቃቂት፣ ከሙዳዩ ክትት
አቤ. . .ት
የታል የትላንቱ?
ሰማየ ሰማያት የነጎድንበቱ
እርገተ ስሜቱ
የተንሳፈፍንበት፣ የዋሸንቱ ፉጨት
የክራሩ ቅኝት
የታለ ንዝረቱ?
ሁሉንም ጣጥለን፣ የጠፋንበቱ
መቼስ ምን ይደረግ
ትዝታ ስንቅ ሆኖ፣ ነፍሳችን ሳትፈልግ
እኔም አንችም እሱም፣ ሁላችንም ጥርግ. . .
ጊዜም እንደዘበት አስቀምጦን ንጉድ. . .
አይናችን እያዬ፣ ልጅነትም እርፍድ. . .
አራት አመት ስልቅጥ
አንጎላችን ብጥብጥ
ጉንጫችንም ምጥጥ

ጣታች ደንቁሎ፣ ከብእር ተዋደን
ቀለም አጥበርብሮን
ፊደሉን ፈድለን
ቀመሩን ቀምረን
ወረቀት ወርቀን
ካመል አመል ነስቶን
ንጭንጭ ንዝንዝ አርጎን
አምና ካቻምናውም፣ ጣጥሎን ነጎደ
ልጅነት ታጠበ፣ እድሜም ረፈደ
ግንባርም ታረሰ፣ ጢምም ተገመደ
እሳት አፍላ ጊዜ ረምጦ አመደ
ይገርማል አንችዬ
አዬ ጉድ፣ አዬ ጉድ
ጊዜም እንደዘበት፣ አስቀምጦን ንጉድ
ህም!
(መስፍን አሸብር)

በግጥም 3 ውስጥ ገጣሚው የአጻጻፍ ነጻነቱን በመመርኮዝ የተገለገለባቸው ቃላት ይገኛሉ፡፡ እነሱም

- ፈድሰን
- ወርቀን

የሚሉት ናቸው፡፡

iii. ሌላው የስነግጥም የአጻጻፍ ነጻነት ማስረጃ ገጣሚው የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ መዋቅር የመከተል ግዴታ የሌለበት መሆኑ ነው፡፡

ገጣሚያን በግጥማቸው ውስጥ፡

- አስፈላጊ መስሎ ሲታያቸው

- አንድ ግጥማዊ ፋይዳ ይኖረዋል ብለው በሚያምኑበት ጊዜ

የሚጽፉበትን ቋንቋ ሰዋሰው መዋቅር ሊጥሱ ይችላሉ::

ገጣሚው የቋንቋውን የቃላት ክፍሎች ቅደም ተከተላዊ አሰላለፍ ላይከተል ይችላል::

ለዚህ ከሚያበቁት ግጥማዊ ፋይዳዎች ውስጥ:

- ምቱን ለማስተካከል
- ምጣኔውን ለመጠበቅ
- ዜማው የተስተካከለ እንዲሆን
- የቤት አመታት ስልቱን ለማስተካከል
- አዲስነትን በመፍጠር ስሜትን ለመግዛት

የሚሉት ይጠቀሳሉ::

የሚከተሉት ሁለት ስንኞች ግጥም ለዚህ ምሳሌ ይሆናል::

እርስ በርስ አባልቶ ቤተሰብ ደምሳሹን
ከቶ ምን ይሉታል ዘመን ይህ አይነቱን

እዚህ ላይ አንድ ነገር ልብ ማለት ይገባል::

- ዝም ብሎ ነጻነት አለ በሚል ሰበብ ብቻ የሚከናወን አይደለም::
- አንድ ሊመታ የታሰበ፣ ሊደረስበት የተፈለገ የተለየ ግብ መኖር አለበት::

መ. ስርአታዊ ምት፣ ሙዚቃዊ ቃና እና ዜማ ያለው መሆኑ

በስነግጥም ውስጥ ስለምት ማሰብ አይቀሬ ጉዳይ ነው::

ከሌሎች የስነጽሁፍ ዘርፎች የሚለይበት ዋነኛ ባህሪውም የጠበቀ እና ስረአታዊ የሆነ ምት ያለው መሆኑ ነው::

በስነግጥም ውስጥ ቃላት ሲመረጡ

- ሃረጋት ሲዋቀሩ

- ስንኞች ሲመሰረቱ

የግጥሙን ምት በማያፋልስ እና በሚያጠናክር መልክ መሆን አለበት፡፡

የግጥሙ ምጣኔ መጠበቅ፣ ሙዚቃዊ ቃና መጠንከር፣ ወዘተ. የሚመነጨውም ከዚሁ ከስርአታዊ ምቱ መጠበቅ ነው፡፡

ስነግጥም ሙዚቃዊ ቃና ያለው በዜማ የሚነበብ የስነጽሁፍ ዘርፍ ነው፡፡

ገጣሚያንም እነዚህን እያሰቡ ነው የሚገጥሙት፡፡

ስለምት እና ምጣኔ አጠባበቅ በሚቀጥለው ምእራፍ ላይ ዘርዘር አድርገን እንመለከታለን፡፡

በስነግጥም ውስጥ

- ስርአታዊ ምት ከምጣኔው ይመነጫል፡፡
- ስርአታዊ ምቱም ሙዚቃዊ ቃናውን ይፈጥራል፡፡

ሠ. የቤት አመታቱን የተጠበቀ መሆኑ

ስነግጥም በአብዛኛው ቤት በሚመታ መንገድ የሚቀርብ የስነጽሁፍ ዘርፍ ነው፡፡

በሚቀርብበት ጊዜ የየሃረጋቱ ወይም የየስንኞቹ የመጨረሻ ድምጻች ይመሳሰሉ ዘንድ ጥረት ይደረጋል፡፡

ይህን በጣም ጥንታዊ የሆነው የስነ ግጥም ብቸኛ ባህሪው ነው፡፡

እዚህ ላይ ግን አንድ ነገር ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

ቤት የማይመቱ ስንኞች ያሉበት ስነግጥም፣ ስነግጥም ሊባል አይችልም ከሚል መደምደሚያ ላይ መድረስ አይገባም፡፡

ስነግጥምን በግንባር ቀደምተኑት ማገናዘብ ያለብን ከቤት አመታቱ ጋር ሳይሆን ከምቱ መጠበቅ ጋር ነው፡፡

ረ. የአይረሴነት ባህሪ ያለው መሆኑ

በስነግጥም የቀረበ ሃሳብ በሌሎች የስነጽሁፍ ዘርፎች ከቀረበ የበለጠ በአንባቢ ወይም በአድማጭ አእምሮ የመቆየት ባህሪ አለው፡፡

አንባቢ ወይም አድማጭ ሙሉውን ግጥም፣ የተወሰኑ አንጓዎችን፣ ስንኞችን፣ ሃረጋትን፣ ስንኞችን በአእምሮ ቀርጾ ለዘመናት የሚያቆይበት አጋጣሚ አለ፡፡

ለስነግጥም ያለመረሳት ባህሪ የሚከተሉት ነጥቦች ማስረጃዎች ይሆናሉ፡፡

- ጉዳዩን በሚመለከት ተዋንያን የሚሰጧቸው አስተያየቶች

  በስድጽሁፍ ከቀረቡት ተውኔቶች ይልቅ በግጥም መልክ የሚቀርቡት በቀላሉ እንደሚጠኗቸው እንከሚያዟቸው ለረጅም ጊዜም በአእምሯቸው ተቀርጸው እንደሚቆዩ ተዋንያን ሲናገሩ ይከመጣሉ፡፡

- አያሌ ሙዚቃዎችና እና ዘፈኖች በአእምሯችን ተቀርጸው በቆየታቸው
- የእኛ የእራሳችን የህይወት ልምድ ሌላው ማስረጃ ነው፡፡

  ከልጅነታችን አንስቶ እስከዛሬ ድረስ በርከት ያሉ በስነግጥም እና በዝርው የቀረቡ ስራዎችን አንብበናል፤ አለባለዚያም አድምጠናል፡፡

  ከነዚህ ሁሉ ግን በውስጣችን ተቀርጸው የቀሩ ካሉ፣ እነሱም በግጥም መልክ የቀረቡት ናቸው፡፡

# ምእራፍ ሁለት

## 2. የስነግጥም ፍሬነገሮች

የስነግጥም ፍሬነገሮች የሚባሉት፡

- አንድ ጥሩ ስነግጥም እንዲያሟላቸው የሚፈለጉ ነጥቦች (የስነግጥም ባህሪያት የምንላቸውን) ያሟላ ዘንድ ከግንዛቤ የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው፡፡

ከዚህ ቀጥለንም እነዚህን ፍሬ ነገሮች አንድ ባንድ እንመለከታለን፡፡

## 2.1 የቃላት ምርጫ

ቃላት ለስነግጥም መሰረቶች ናቸው፡፡

- ስነግጥም ለቃላት ገላው ስስ ነው፡፡
- አንድ ስነግጥም የጥሩ ስነግጥም ባህሪያትን የሚጎናጸፈው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በቃላት አማካኝነት ነው፡፡
- በመሆኑም ገጣሚያን በግጥሞቻቸው ውስጥ ለቃላት ምርጫቸው መጨነቅ ይገባቸዋል፡፡

ቃላት፡

በቀጥተኛው መንገድ

- በቃላትነታቸው ሃሳብን ይገልጻሉ፡፡
- ለግጥሙ የግጥምን ባህሪያት ያጎናጽፉታል፡፡

- የግጥሙን የዘት ያስተላልፋሉ።

በተዘዘዋዋሪው መንገድ ደግሞ፡

- ሀረጋት ይመሰረቱባቸዋል።
- ስንኞች ይገነቡባቸዋል።
- ዘይቤዎች ይዋቀሩባቸዋል።
- የስነግጥሙ ቅርጽ ይዋቀርባቸዋል።
- ምናብ ይፈጠርባቸዋል።
- ምስል ይፈጠርባቸዋል።

ቃላት በቀጥተኛውም ይሁን በተዘዋዋሪው መንገድ፡

- ለስነግጥሙ ውበትን ይለግሳሉ።
- ለይዘቱ ጥልቀትን ያላብሳሉ።
- አሮጌውን፣ የተለመደውን አዲስ ያስመስላሉ።
- እጅ እጅ ያለውን፣ የሰለቸውን እና ስሜትን የማይኮረኩረውን ስሜትን እንዲኮረኩርና እንዲነካ፣ ምናብን እንዲያጭር ያደርጋሉ።
- ደብዛዛውን በማድመቅ ምስልን ይፈጥራሉ።
- ረቂቁን ያገዝፋሉ።
- ተጨባጩን ረቂቅ ያደርጋሉ።

በአጠቃላይ የግጥሙ ይዘትም ሆነ ቅርጽ በቃላቱ እጅ ስር ነው።

ይህ ሁሉ እውን የሚሆነው ቃላት ይህንን ሁሉ ሚና እንዲጫወቱ ሆነው ሲመረጡ ነው።

ስለሆነም ገጣሚያን በግጥሞቻቸው ውስጥ ቃላትን በሚመርጡበት ጊዜ ለሚመርጧቸው ቃላት መጠንቀቀ ብዙ ማሰብ፣ ማውጣት ማውረድ ይገባቸዋል።

ገጣሚያኑ ቃላትን በሚመረጡበት ጊዜ ከግንዛቤ ከሚያስገቧቸው ነጥቦች ውስጥ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ።

- የቃላቱ የመግለጽ አቅም

- የቃላቱ የቅርጽና የፍች ባህሪያት
- የቃላቱ የፍች ደረጃ
- ሌሎች የቃላቱ ልዩ ልዩ ባህሪያት
- የቃላቱ ተዘውታሪነት
- የቃላቱን ጎንዮሽም ይሁን ተዋረዳዊ አብሮ ተሰላፊነት

ገጣሚያን የሚመርጧቸውን ቃላት ቃላት ከሚከተሉት ነጥቦች ረገድ መመርመር ይገባቸዋል፡፡

- የሚገለጸውን ጉዳይ ቁልጭ አድርገው የሚያሳዩ (ገላጭ) መሆናቸውን
- ከሚገለጸው ጉዳይ ጋር በጥብቅ የተቆራኙና የሚጣጣሙ (አውዱን የጠበቁ) መሆናቸውን
- በግጥሙ ውስጥ ሊፈጠር ከተፈለገው አውድና ድባብ ጋር የተሰናሰሉ መሆናቸውን
- በጎንዮሽም ሆነ በተዋረዳዊ መልኩ አብረው ሊሰለፉ የሚችሉ መሆናቸውን
- የግጥሙን ቅርጽ የሚጠብቁ መሆናቸውን
    - ምቱን
    - ምጣኔውን
    - ቤት አመታቱን
    - ዜማውን
- ስሜትን የመቆንጠጥ ሃይል ያላቸው መሆናቸውን

ለምሳሌ ያህል በሚከተሉት ግጥሞች ውስጥ የቃላቱን ሁኔታ እንመልከት፡፡

1. የጉልታዊ ስርአት ፍግ
   የከበርቴው ስርአት ኩስ
   ሲሰነፍጥ ሲገለማ
   አገር ሲበክል ሲቆንስ

አላስቆም አላስቀምጥ ሲል
በሽቅጦ ሰርን ሲበጥስ፡፡

<u>ጥያቄ</u>፡ ከላይ የቀረበውን ግጥም ከቃላቱ ረገድ ተንትነው (ተንትኝው)፡፡
በዚህ ግጥም ውስጥ የሚገኙት ቃላት ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ነጥቦች ረገድ ሲቃኙ፡

- የግጥሙን የምሰላ ደረጃ ከፍ አድርገውታል፡፡
- በገላጭነታቸው የስርአቱን ከልክ ያለፈ መበሻቀጥ ጥሩ አድርገው ያሳያሉ፡፡
- በጥሩ አሰዳደር ቀርበዋል፡፡
- ግጥሙ ሲነበብ ወይም ሲነበብ ሲደመጥ የስርአቱ ግማት እንዲሰማ ያደርጋሉ፡፡
- የስርአቱን መበሻቀጥ ስሜትን በሚቆነጥጥ መልኩ ያቀርባሉ፡፡
- የግጥሙን ቅርጽ ይጠብቃሉ፡፡

በግጥሙ ውስጥ የሚከተሉት ቃላት፣ ለቃላቱ ግብ መችነት፣ ገላጭነት እና ግጥማዊነት በምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡፡

- ኩስ
- ሲሰነፍጥ
- ሲገለማ
- ሲቆንስ
- በሽቅጦ

2. ጠብቄሽ ነበረ
መንፈሴን አንጽቼ
ገላዬን አጥርቼ

አበባ አሳብቤ

አጱኛ ሰብስቤ

ጠብቄሽ ነበረ፤

ብትቀሪ ጊዜ፣

መንፈሴን አሳደፍኩ

ገላዬን አጎደፍኩ

አበባው ደረቀ

አጱኛው አለቀ፤

ብትቀሪ ጊዜ፣

የጣልኩብሽ ተስፋ

እኔን ይዞ ጠፋ፡፡

(ደበበ ሰይፉ፡ 1992፡ 13)

ጥያቄ፡ ከላይ የቀረበውን ግግም ከቃላቱ አመራረጥ ረገድ ተንትን (ተንትኚ)፡፡

በግጥሙ ውስጥ ያሉት ቃላት፡

- ከርእሰ ጉዳዩ ጋር በጥብቅ የተቆራኙ ናቸው፡፡
- ሰፋፊ ሃሳቦችን ይዘዋል፡፡
- አንድ ባንድ ቢተነተኑ የያዙት ጽንሰ ሃሳብ ተተንትኖ አይዘለቅም፡፡
- የገጸባህሪውን አንድን ነገር ተሰናድቶና በጉጉት መጠበቁን ፍንትው አድርገው የሚያሳዩ ናቸው፡፡
- የጎንዮሽም ይሁን የተዋረዳዊ አብሮ ተሰላፊነታቸው ጥሩ ነው፡፡
- ገጸባህሪው የጠበቀውን እና ተስፋ ያደረገበትን ሳያገኝ ሲቀር የሆነውን ቁልጭ አድርገው ያቀርባሉ፡፡
- በገላጭነታቸው የተዋጣላቸው ናቸው፡፡

ናቸው፡፡

3. ተይው እንተወው

ተይው እንተወው፣....
የዘመን ቃፌሩን ማለፍ አልቻልንና
ይህ አለም ጥበቱ አልመጠነንና፤
ተይው እንተወው፣....
ውጥኑ ግብ ይሁን
ጅማሬው ፍጻሜ፣
ቅጽበቷ ሙሉ እድሜሽ
ወቅቷ ዘላለሜ፡፡

ከዚህ በላይ የቀረበው ግጥምም ቢሆን በቃላት ምርጫው የተዋጣለት ነው፡፡
ለቃላት ምርጫው የተዋጣ መሆንም የሚከተሉት ቃላትና ሃረጋት በምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡፡

- የዘመን ቃፌሩን
- ውጥኑ ግብ ይሁን
- ጅማሬው ፍጻሜ

የሚከተለው ግጥምም ከቃላት ምርጫው ረገድ የተዋጣለት ነው ማለት ይቻላል፡፡

4. ጓዙን ሁሉ ጠርፎ

ማገዶ ሸምቶ
እቶን አደረገው
ጸጸት ልቤ ገብቶ፡፡
(ፈቃደ 1985፡ 15)

ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች ከግንዛቤ በማስገባት ገጣሚያን በግጥሞቻቸው ውስጥ የሚያዝወትሯቸውን የቃላት አጠቃቀሞች በሁለት አጠቃላይ ክፍሎች ከፍለን መመልከት እንችላለን፡፡

## ሀ. በተለመደ ፍቻቸው መገልገል

እነዚህ ቃላት፡

- በተለመደ ፍቻቸው የምንገለገልባቸው ናቸው፡፡
- ፍቻቸውን ለማወቅ መዝገበ ቃላትን ማገላበጥ ወይም ሰው መጠየቅ አያስፈልግም፡፡

የተወሰኑ ገጣሚያን ቃላትን በተለመደውና በቀጥተኛው ፍቻቸው በመገልገል ስነግጥም ይጽፋሉ፡፡

ይህም የስነጽሁፋዊ ስልት ምርጫ ጉዳይ ስለሆነ "ገጣሚው እንዴት በስነግጥም ውስጥ ቃላትን በተለመደ ፍቻቸው ይገለገላል?፣ ማድረግ አልነበረበትም" በማለት መንቀፍ አይቻልም፡፡

ቃላቱ ሁልጊዜ የምንገለገልባቸው በመሆናቸው፡

- ስሜትን የመያዝ
- ምናብን የመተንኮስ
- አዲስነትን የመፍጠር
- ኢዘርዛሪነትን የማላበስ
- በአጠቃላይ የግጥሙን ደረጃ የማላቅ

ደረጃቸው ዝቅተኛ ነው፡፡

በመሆኑም ቃላትን ከዚህኛው ፍቻቸው ረገድ በመገልገል ስነግጥም መጻፍ ከፍተኛ ችሎታን ይጠይቃል፡፡

በአብዛኛው ስንመለከትም በእነዚህ ቃላት የተዋጣላቸውን ግጥሞች የጻፉት አንቱ የተባሉና ጥቂት ገጣሚያን ብቻ ናቸው፡፡

ከበደ ሚካኤል ለዚህ በምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡፡

የከበደ ሚካኤል የሚከተሉት ግጥሞች ለዚህ ጥሩ ማስረጃዎች ይሆናሉ፡፡

1. ሁለት ነገር አለው ሰው በአለም ላይ ሲኖር
መልካም አመልና አንድ ክፉ ጠባይ
የሁለቱም ጠባይ እያደር ይስፋፋል
ሰውም ባንዱ ለምቶ ባንደኛው ይጠፋል፡፡

2. የተማረ ሆኖ እውቀቱን የማይገልጥ
ባለጠጋ ሆኖ ለድሃ የማይሰጥ
ደሃ ሆኖ መስራት የሚጠላ ልቡ
ሶስት ፍሬ ቢሶች ለምንም አይረቡ፡፡

3. ቢቆስልም ይድናል የተደበደበ
ምላስ ግን ይኖራል እንዳንገበገበ፡፡

ገጣሚ ደበበ ሰይፉም በተለመዱ ቃላት የተዋጣላቸው የሚባሉ ግጥሞችን ጽፈው እናገኛቸዋል፡፡
የሚከተሉተ በማስረጃነት ይጠቀሳሉ፡፡

## ለ. በተደራቢ ፍቻቸው መገልገል

የቃላትን ከተለመደውና ሁልጊዜ ከሚያገለግለው ፍች በተደራቢነት የሚያገለግሉ የቃላትን ፍችዎች ይመለከታል፡፡
ቃላቱ ከተለመደው ፍቻቸው በተጨማሪ ተደራቢ ፍች ያላቸው በመሆናቸው፡

- ብዙና ሰፊ ሃሳብን ለማስተላለፍ ያግዛሉ፡፡
- ግጥሙ የክትነት ባህሪ እንዲላበስ ያግዛሉ፡፡

ቃላቱ በፍቻቸው ከተለመደው ወጣ ያሉ በመሆናቸውም፡

- በቀላሉ አዲስነትን ይፈጥራሉ፡፡

- ስሜትን ይኮረኩራሉ፡፡
- ምናብን ያጭራሉ፡፡
- ትኩስነት ወይም ያለመሰልቸት ባህሪን ይፈጥራሉ፡፡

የሚከተሉት ግጥሞች ለዚህኛው በምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡፡

1. አይ መርካቶ
አገር ከየጎራው ወጥቶ
አንችን ብሎ ነቅሎ ወጥቶ
ግሳንግሱን ጓዙን ሞልቶ
ሁልቆ መሳፍርትሽ ሞልቶ
ባንች ባዝኖ ተንከራትቶ
እንደባዘቶ ተባዝቶ
ተንጠራውዞ ዋትቶ ዋትቶ
አይ መርካቶ
የምድር አለም የእንጀራ እናት
ላንዱ ርካሽ ለሌላ እሳት
ላንዱ ሲሳይ ለሌላ እሳት
ላንዱ ተስፋ ላንዱ ስጋት
የግርግር የሆይታ ቋት
አይ መርካቶ
. . . . . . . . . . . . .
(ጸጋዬ ገብረመድህን፡ እሳት ወይ አበባ፡ 30)

በግጥሙ ወስጥ በፍካሬያዊ ፍቻቸው ካገለገሉት ቃላት ውስጥ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

- አገር
- ከየጎራው

- የምድር አለም
- ለሌላ እሳት

ጥያቄ: በግጥሙ ውስጥ ከተዘረዘሩት ቃላት ውስጥ "አገር" እና "ከየጎራው" የሚሉት ቃላት የሚሸከሙትን የፍች ገጽታ ዘርዝረህ (ዘርዝረሽ) አሳይ።

2. ለስጋ ውድነት

ፍየል ሞልቶ ፍየል ተርፎ
ላሙ ሞልቶ በሬው ተርፎ
በጉ ሞልቶ …
ምን ቢመጣ አዲስ ታምር አዲስ ነገር
ከብት ይወደድ በከብት አገር።
(ፈቃደ 1990፡ 30)

በዚህኛው ግጥም ውስጥ የሚከተሉት ቃላት ከፍቻቸው ረገድ ፍካሬያዊ ቃላት ናቸው።

- በግ
- ከብት
- በከብት አገር

ጥያቄ: በግጥሙ ውስጥ ከተዘረዘሩት ቃላት ውስጥ "በከብት አገር" እና "ከብት" የሚሉት ቃላት የያዙትን የፍች ገጽታ ዘርዝረህ (ዘርዝረሽ) አሳይ።

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ገጣሚያን ለግጥሞቻቸው ግብ መምታት ሲሉ በግጥሞቻቸው ውስጥ የሚገለገሉባቸውን ቃላት በሚከተለው መልክ ከፍለን መመልከት እንችላለን።

## ሀ. የተውሶ ቃላት

የተውሶ ቃላት ወደሚለው ከመሸጋገራችን በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንመልከት፡፡

1. በሃራችን በቤተክርስቲያን ትምህርት የገፉ በተለይም የግእዙን ቋንቋ ጠንቅቀው የሚያውቁ ሰዎች ከግእዝ የተወሰዱ ቃላትና ሃረጋትን በእየለቱ የሃሳብ መግለጫቸው ውስጥ ጣልቃ የሚያስገቡት ለምን ይመስልሃል (ይመስልሻል)?

2. በአረብኛው ቋንቋ ትምህርት የገፉ የሃይማኖቱ ሰዎች ሃሳባቸውን በሚገልጹበት ጊዜ የአረብኛ ቋንቋ ቃላትና ሃረጋትን ጣልቃ የሚያስገቡት ዋነኛ ምክንያት ምን ይመስልሃል (ይመስልሻል)?

3. በሃገራችን ዘመናዊውን ትምህርት የተከታተሉ፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋንም ያጠኑ ሰዎች በየንግግራቸው ጣልቃ የእንግሊዝኛ ቃላትና ሃረጋትን የሚያስገቡበት ምክንያት ምን ይመስልሃል (ይመስለሻል)?

የተወሰ ቃላት የሚባሉት በአብዛኛው ቋንቋውን ጠንቅቀው የሚያውቁ ሰዎች የሚያውቋቸው እና የሚገለገሉባቸው ናቸው፡፡
ማወቅ ሲባል ተራ ሽምደዳ፣ የቃላቱን ቀጥተኛና ነጠላ ትርጉም ማወቅ ብቻ ሳይሆን ከፍቺ ጋር የሚያያዙ ሰፊ እሳቤዎችን፣ ቃላቱ ሲጠቀሱ የሚፈጠረውን ድባብ ሁሉ ጠንቅቆ መመርመርን፣ ማገናዘብን፣ ማወቅን ይመለከታል፡፡

ገጣሚያን የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሲሹ ቃላቱን ይገለገሉባቸዋል፡፡

- አንድ የተለየ ግብ መምታትን
- በግጥሙ ውስጥ የተጠቀሰን ገጸ ባህሪማንነት በሚገባ ለማሳየት
- ሙያዊ ሁኔታዎችን ለመግለጽ

ገጣሚያን እነዚህን ቃላት ከሚገለገሉባቸው ምክንየቶች ውስጥ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

- በመጡበት ቋንቋ ውስጥ ሰፊ ሃሳብን በመያዛቸው
- ጉዳዩን ቁልጭ አድርገው በማሳየታቸው
- የመጡበት ቋንቋ የበለጸገ በመሆኑ ገላጭነት ስላላቸው
- በመጡበት ቋንቋ ውስጥ ሰፊ እውቅና (popularity) ያላቸው በመሆናቸው ለሃሳብ ማጉያነት ስለሚገለገሉ
- ተመጣጣኝ ትርጉም መፈለግ፣ ዙሪያ ጥምጥም የሚያስሄድ ሃሳቡን የሚያደበዝዝ መስሎ ሲታይ
- በግጥሙ ውስጥ የቀረበውን ገጸባህሪ ማንነት ከነሁለተናዊ ገጽታው ለማሳየት በመፈለግ

ሆኖም ቃላቱ የውስንነት ባህሪ የሚታይባቸው መሆናቸውን ልብ ማለት ይገባል፡፡
ቃላቱ በግጥሙ ውስጥ የተሸከሙትን ፍች የሚገነዘቡት፡

- ቃላቱ የተወሰዱበትን ቋንቋ ጠንቅቀው የሚያውቁ
- ቃላቱ፣ በተወሰዱበት ቋንቋ ውስጥ የሚሸከሙትን ሰፊ እሳቤ የሚገነዘቡ ሰዎች

ብቻ ናቸው፡፡

ይህንን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ የሚከተለውን ግጥም እንመልከት፡፡

1. ያን መሰል ተፈጥሮሽ መሰሉን ካልተካ
ያን መሰል ውበትሽ መሰሉን ካልተካ
ይህ አለም ለመኖር ከቶ መች ሊያስመካ፡፡
ቅኔ ውበት ዘርፈሽ ምስጢሩ ረቂቅ
ወርቁም እየኳሸ አንቀጹ ሳይጸድቅ
የግራና ቀኝ ልጅ የሰምና የወርቅ
ቅኔው ይፈታና ይታይ ይበል ብቅ፡፡

ያን መሰል ተፈጥሮሽ የፍጥረት ይባቤ
ያን መሰል ቁመናሽ ያካል ቅርጽ ይባቤ
ያን መሰል ውበትሽ የውበት ይባቤ
ከሀቱም ምድር እንጅ አይገኝ ከሩካቤ፡፡
(ዮሃንስ አድማሱ፡ ስብስብ ግጥሞች፡ 73)

ከላይ በቀረበው ግጥም ውስጥ፡

- ገጣሚው ለሃሳቡ ማጉያነት የተገለገለበት ቅኔ መዝረፍን ነው፡፡
- የቀረበችዋ ገጸባህሪ የውበት ድባብ፣ የውበት ምስጢር ረቂቅነት የቀረበው ከቅኔ ውበት፣ ከሰምና ከወርቅ ረቂቅነት ጋር ተያይዞ ነው፡፡
- ሁኔታውን በሚገባ ለማጣጣም፣ ከስሜት ጋር ለማዋሃድ እና በውስጡ ያለውን ድባብ በምናብ ለመዳሰስ፣ ዝም ብሎ የቅኔን ፍች ማወቅ ብቻ ሳይሆን የሰምና ወርቅን ሁለንታዊ ገጽታ ጠንቅቆ ማወቅን ይጠይቃል፡፡

ለዚህም የሚከተሉትን ከቅኔ ጋር የተያያዙና ከግእዝ ቋንቋ የተወሰዱ የተወሶ ቃላት ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

ይባቤ፡

- እልልታ
- ምስጋና
- የደስታ መዝሙር
- የሚያፍነከንክ
- በእልልታ ልብን የሚያስደስት

ሀቱም፡

- የተዘጋ
- የተቆለፈ

- በቀላሉ የማይከፈት
- አለመነካት
- አለመደፈር
- ተቃራኒ ጾታን አለማወቅ
- ንጽህና
- ድንግልና

<u>ወርቁም እየኳሸ</u>

<u>አንቀጹ ሳይጸድቅ</u>

ገጣሚው ከግእዝ ቋንቋ በተወሰዱት ቃላት አማካኝነት በግጥሙ ውስጥ የቀረበችዋን ገጸባህሪ፡
- የውበት መርቀቅ
- እንደሷ ያለች የውበት ደባብ የተላበሰች ያለመኖር
- በረቀቀ ጥበብ፣ በንጽህና፣ የተገኘች እንጅ በተለመደው መንገድ በሩካቤ ስጋ ልትገኝ አለመቻሏን
- እሷን የሚገልጽበት ምንም ቋንቋ ሊገኝ የማይችል መሆኑን
- በቋንቋ ልግለጸው፣ በቅኔ ላስፍረው ቢባል እንኳን የመግለጫ ቋንቋና ቅኔ እንደማይገኝ
- ከዚህ ሁሉ የተደበቀው ውበቷ ጎልቶ በመውጣት ቢታይ የሚሻል እንደሆነ

ይጠቁማል፡፡

ከዚህ በታች የቀረቡት ግጥሞችም ሃሳባቸው የሚጎላው በምሁር ቃላት አማካኝነት ነው፡፡

1. ኦ! ባለን እንደሰት፣ ባለን እንጫወት
ኦ አዳም ሳንባል ግባ ውስተ መሬት

ትቢያ ወደ ትቢያ ትቢያ ስር አለሜ
ያለ ወይን ያለ ጠጅ ያለፈውን አውራጅ ያለ እስክስታ
ወራጅ ወእንበለ ፍጻሜ::

ከዚህ በላይ በቀረበው ግጥም ውስጥ

- ግባ ውስተ መሬት
- ወእንበለ ፍጻሜ

የሚሉት ቃላትና ሀረጋት የተውሰ ቃላት ናቸው::

2. ህይወት

ችግር ነው መፈጠር፣ ማግኘትም ማጣትም
ይህ አለም ይህ ኑሮ አዱኛ ህይወትም::
ሲገኝ መናጠጡ
ሲያጡ መራወጡ ... መኮረማመቱ::
"ለጽድቅ ኢንዜከራ፣ ወኢትዝከረና ጽድቅ
እስመ ጊዜ ብእልነ ንትኤበይ
ወጊዜ ንዴትነ ንስርቅ::"[1]
የበሽታስ ጉድ
መጋኛው ነቀርሳው
ልክፍቱ ዳፍንቱ!

የመገላገያው፣ የመፍትሄ ማግኛው
ምንድነው ብልሃቱ?
"መሞት፣ መኖት - ማንቀላፋት
እስከመቼም ባለመንቃት"
አሄሄ!
መች እንዲህ በዋዛ
ከመኖር ሞዛዛ

እንዲህ በቀላሉ … ይገላገላሉ?
ላንዲት ኩርማን እድሜ
ላምስት ቀን ጳጉሜ
በጉሉኮስ ጠርሙስ ሳይንበላጠጡ …
ሜዲካል፣ ሰርጂካል፣
ኦፒዲ አይ. ሲ.ዩ ሳይወርዱ ሳይወጡ
በዘመድ ባዝማዱ
ከንቱ ሽር ጉዱ
በከንፈር መጣጩ
ባዛኝ ቅቤ አንጓቹ ሳይሰለቻቹ
መች እንዲህ በዋዛ
ከመኖር ሞዛዛ
እንዲህ በቀላሉ …?
"ወአመ ተመከረ ኢዮበ በእጸበ ደዌ መሪር
ተመነየ መቃብረ ወኢረከበ ለመቃብር"[2]
አይመልሱት ነገር የትናንቱንና የትናንቱን በስቲያ
አይናፍቁት ነገር ነግ ተነገ ወዲያ …
ኧረ ወዲያ! _______ ወዲያ ወዲያ!

ሺ ቅኔ ቢቀኙ

ሺ ሙሾ ቢያወርዱ አዳሜ ቢንጫጫ
መንጌ! "ስልቻ ቀልቀሎ፣ ቀልቀሎ ስልቻ"
ኧረ ወዲያ! _______ ወዲያ ወዲያ!

(ተስፋዬ ገሰሰ: *መንግስቱ ለማ: ግለታሪክ:* 250-251).

1. ከሀገራችን ቅኔ "ጽድቅን እውነት አናስታውሳትም፣ እሷም አታስታውስንም፣ ባለንጊዜ እንታበያለን፣ በአጣን ጊዜ አንሰርቃለን።"
2. ኢዮብ በመራራ ስጋ ደዌ በተጎበኘ ጊዜ መቃብርን ተመኘ። መቃብር ግን አልረከብህ

አሻፈረኝ አለው።

በተለያዩ የፈቃደ አዘዘ ግጥሞች ውስጥም (ለምሳሌ *እየሄድኩ አልሄድም* "የእንግሊዙ ኤክስፐርት"፡ 47) አንዳንድ የእንግሊዝኛ ቃላትን በትውስት ገብተው እናገኛለን።
በእንግሊዝኛ ግጥሞች ውስጥም የተለያዩ የላቲንም ሆነ የሌሎችን የአውሮፓ ቋንቋዎች ቃላትንና ሃረጋትን እናገኛለን።
ዋናው ጉዳይ ገጣሚያኑ የተውሶ ቃላትን መገልገል አለመገልገላቸው ሳይሆን ቃላቱ በግጥሙ ውስጥ የተፈለገውን ድባብ ፈጥረዋል ወይ? የሚለው መሆኑን ልብ ማለት ያሻል።

## ለ. ድምጸ ቀድ

የአንድን ነገር ድምጽ በመቅዳት ይፈጠራሉ።
ቃላቱ ድርጊት ሲከናወን ከሚሰማው ድምጽ በመነሳት ይፈጠራሉ።
ቃላቱ ድርጊትን ከድምጽ ጋር አዋህደው ስለሚያቀርቡ የሚከተሉትን ፋይዳዎች ይጫዎታሉ።

- በእዝነ ህሊና ስሜትን በሚስብ መልኩ እንዲሰማ
- በአይነ ህሊና እንዲታይ
- በምናብ እንዲገዝፍ

ቃላቱ፡

- በግጥሙ ውስጥ የቀረበውን ሃሳብ በየእለቱ ከምንሰማቸው
- ስሜታችንንም ከሚነኩን

ድምጾች ረገድ በመግለጽ

  - ሃሳቡ የበለጠ እንዲጐላ
  - የበለጠ ተፈጥሯዊ እንዲሆን

የሚደረግባቸው ናቸው።

የሚከተሉት ሁለት ግጥሞች ለዚህ ምሳሌዎች ይሆናሉ፡፡

1. ለስራ ጓደኞቼ ለመምህራን

ለስራ ጓደኞቼ ለመምህራን
የሆዴ ቡጭቡጭታ
የእንባዬ ቀረርታ
የስሜት መታወክ
እያዩኳቸው ከመድረክ
የጽህፈት ቤት መድረክ፡፡
አለቆቼ
እንባ ጠባቆቼ
ጓዶቼን አይዋቼው
እርቧቼው
የበሉም አይመስሉ
ሁሉም ተኮሳትረው፣ እያሰላሰሉ
ሲሉ፣ ምን እበላው?
ምን እጠጣው?
እሞተው? እቀበረው?
ወይ ግሩም እንዴት ልሆነው ነው?
ደግሞ ሲሉ፣ ምን ይበሉት?
ምን ይጠጡት?
ይሞቱት? ይቀበሩት?
ወይ ግሩም እንዴትስ ሊወጡት?
ይህን ክረምት
ሚስቴና ልጆቼ
ሳር ቅጠሉ እኒያ ዘመዶቼ
አሁንም አሁንም ይህንኑ ሲሉ
በሹክሹክታ

ሹክሹክታው ተባዝቶ በህምታ
ጉርምርምታ
ቻቻታ
ጫጫታ
በድምጽ ማእበል ግቢው እስኪምታታ::
(አፈር ያነሳ ስጋ: 34 - 35)

2. ማነው. . . ምንትስ?
ስለዚህ አንዳንዴ ብቻ፣ አልፎ አልፎ ብቻ ላንዳፍታ
አሳቤም ስጋዬም አብሮ፣ ትንፋሼም ሲያገኝ እፎይታ
ምንትሶች ለምትሉን፣ የለንምና ጸጥታ
ከዚያ ከሌት ውጣ ውረድ፣ ከቀን መኝታው ድውታ
ላመል ታህል ብቻ ድንገት፣ ለህሳብ ንቃት ለትዝታ
ገለል ቀለል ሲለኝ፣ ከስንቱ ሆይታና ዋይታ
ካዳር ዋጋው ካንድ ጊዜው፣ ከሂሳብ ዛቻው ቆይታ
ከግራ ማፎን ቀረርቶው፣ ከድም ድሙ ካካታ
ከሙዚቃው ሆያ ሆዬ፣ ከናላ ወቀጣው ፋታ
ከዳንኪራው ውትር ግትር
ከመጠጡ ብዥ ድንብር
ትንሽ የህሊና ሰላም፣ አገኘሁ ስል . . . የሚለኝ ቅር
እንደገና ለብቻዬ፣ የልቤን ቁስል የሚያጥር
አለብኝ የሀቅ ብትር
ነፍሴን ከስሶ እሚያከራክር::
(ጸጋዬ ገ/መድህን: 1966: 65)

3. የማልወደው ድምጽ
ግም!
ቀርጨም - ጨም - ጨም!

ሲ - ጢ - ጢ - ጢ - ጥ!

ፍሬኑ ሲረገጥ

ልብ የሚሰቀጥጥ

የመኪና ግጭተ

የመስታወት ፍጭት፡፡

ከዚያን ያፍታ አፍ መካፈት

ግብ ግብም አይጠፋበት፡፡

እና ይቀጥላል የቀረው

ከዚያ ወዲያ ያለው

\- - - - - - - - - - - -

የህይወት ያፍታ ስራ

የብዙ ጊዜዋን ፈጠራ

በቅጽበት ስታወድም

ግም . . . . . . . !

ቀር ጨም - ጨም - ጨም!

ፍሬኑ ሲረገጥ

ልብ የሚሰቀጥጥ

ጆሮ የሚያስጨብጥ

መጥፎ ድምጽ፡፡

የቅዝት ድምጽ፡፡

የማልወደው፣ የግጭት ድምጽ፡፡

**(ሰይፋ *መታፈሪያ* 1965፡ *አፈርያነሳ ለ.ፖ* 26- 27)**

ሐ. ባህል ነክ ቃላት

እነዚህ ቃላት፡

- በአንድ በተወሰነ አካባቢ ብቻ የሚዘውተሩ
- የአካባቢውን ባህል የሚገልጹ

- ከህበረተሰቡ ባህላዊ ሁኔታዎች ጋር የተያያዙ
- ከባህሉ ጋር በጥብቅ የተቆራኙ

ናቸው::

የቃላቱ ጠንካራ ጎን:

- ግጥሙ መሰረት ያደረገውን ህብረተሰብ ማህበረ ባህላዊ የህይወት ገጽታ በሚገባ ለማሳየት ሲባል ይመረጣሉ::
- ባህሉንና ወጉን ለመግለጽ ዙሪያ ጥምጥም ከመሄድ፣ ማብራሪያም ከመፈለግ ይልቅ ቃላቱን እንዳለ ወስዶ በአቋራጭ ለመገልገል ያስችላሉ::
- ቃላቱና ሃረጋቱ በሚጠሩበት ጊዜ የሚከናወነው ድርጊት ሁሉ ከነአጠቃላይ ድባቡ ቁልጭ ብሎ እንዲታይ ሊያደርጉ ይችላሉ::

    ስምሳሌ ሚር (መፍቻ)፣ በእንደድ የታጠበ፣ በርኮታ፣ ጠጆ ሳር የሚሉትን ቃላት በምናነብበት ወይም በምንሰማበት ጊዜ ሰፊ ባህላዊ ጉዳዮች በአእምሯችን ውስጥ ይመጣሉ::

የቃላቱ ደካማ ጎን:

- ቃላቱ ውስንነት ስላላቸው ሊገነዘቧቸው የሚችሉት ባህሉንና ወጉን የሚያውቁ ሰዎች ብቻ ናቸው::
- ግጥሙ የተመሰረተበትን ባህል እና ወግ የማያውቁ ሰዎች የቃላቱን መሉ ፍች ስለማያውቁ ግጥሙን በሚገባ አጣጥመው አይረዱትም::
- በገጣሚው እና በአንባብያን መካከል የመግባባት ግርጆሽ ሊፈጥሩ ይችላሉ::
- ገጣሚውም ሆነ አንባቢው የቃላቱን ተናጥላዊ ፍች ብቻ ቢገነዘቡም ግጥሙን ላይረዱት ይችላሉ::
- የሚያንጸባርቁትን ባህላዊ ጉዳይ በሙሉ ማሰብን፣ ማጤንን፣ መመርመርን ይጠይቃሉ::

ለዚህ ደካማ ጎናቸው ማካካሻም:

- አንዳንድ ገጣሚያን የቃላቱንና ሃረጋቱን ፍች በቅንፍ ውስጥ ያስቀምጣሉ::

- ሌሎቹ ሙዳየ ቃላት ይሰጣሉ::
- ሌሎቹ ደግሞ የግርጌ ማስታዎሻ ይሰጣሉ::
- ግጥሙን የጥሩ ግጥም ባህሪያት እስካላበሱት ድረስ፣ ከቃላት ምርጫ ረገድ የተሳካላቸው እስከሆኑ ድረስ የአንባቢው ትርጉሙን የማወቅ ወይም ያለማወቅ ሁኔታ ገጣሚውን ሊያጨንቀው የሚገባ ጉዳይ አይደለም የሚሉም ገጣሚያን አሉ::

የሚከተሉት ግጥሞች ለባህል ነክ ቃላት ማስረጃዎች ይሆናሉ::

1. አዴ ላንቃሞ (አንድ የሲዳሞ ወንድ)

ብርማይቱ ጨረቃ
የብርሃን ጠበል አፍልቃ
ተፈጥሮን ስታጠምቃት
እንደገና ስትወልዳት
　　ነፋሱ በቀስታ
　　በበረዶ እጁ ሲማታ፤
አዴ ላንቃሞ
ጦሩን ከጎኑ አጋድሞ
ያስተውላል እንደ ነገሩ
አሽቆልቁሎ ከስሩ
　　　እንደዘበት
አፈርሳታ የቆመበቱን
　　　　የእንሰት::
ጭስ ይጨሳል አልፎ አልፎ
እየተዳፈነ ነው ቀቄሶ፤
ለአዴ ላንቀሞ
በቅቤ የጠገበውን
　　　ቡልኮውን

ገለጥ እንደማድረግ ብሎ

ሆዱን ሊያሻሸው

እንዲበርደው

መልሶ ተወው

ብርድ ነክስ ቢያደርገው።

ከዛም ታየው. . . ታየው ባእምሮው

እንደ ደግ ህልም ደስ ደስ እያለው

ሶስቱም ሚስቶቹ ሲርመጠመጡ

የሱን ጉሮሮ ሊያጣፍጡ።

በልቡ አደመጠ ሲበታ

የያንዳንዷ ልብ ድርብ ድርብ

ሽቅብ ሽቅብ

በ"እኔጋ ነው የሚያድር ዛሬ ማታ"።

አዬ ላንቃሞ

የዘወትር ጭምቱ

ቀልድ ቀልደ ሲለው ብልሃቱ

(ከአልፎ አልፎ አንድ እለት

እየከፋ እንደ መዝናናት)

ወደ ጎጆአቸው ተጉዞ

ሚስቶቹን ይመጣል አዞ፣

"እራት እንዲበስልልኝ

አዳሬን እመጣለሁኝ"

ታዲያ እንዲህ እንደዛሬው

ብርማይቱ ጨረቃ

የብርሃን ጠበል አፍልቃ

ተፈጥሮን ስታጠምቃት

እንደገና ስትወልዳት

ነፋሱ በቀስታ
በበረዶ እጁ ሲማታ፤
ካፋፏ ላይ ቁጭ ብሎ
ጭሱ ሲወጣ ተጥመልምሎ
እያየ፣ ፈገግ ፈገገ ይላል
ከት ከት ብሎ ይስቃል
ወንድ የመሆንን ጽድቅ ይክባል
ያደንቃል፡፡
ደሞም ይፈልጋል
ማወቅ ማረጋገጥ
መገኖ እንደሰጠው
ምኔም እንዳይነፍገው፣
ለእያንዳንዷ ሰአት
በእያንደንዷ ሌሊት
ሶስት ሴት ከሶስት ራት፡፡
. . . . . . . . . . . . . . .
(የብርሃን ፍቅር: 28 - 29)

2. ፋጤ ኢብሮ
ፋጤ እራት በልታ
ማወራረጃዋን ውሃ ተጎንጭታ
ሽምቅቅ ሽምቅቅ
ፈርታለች፡፡
ያ ቀልደኛ
የልፊያ ሱሰኛ
ብብትዋን ነክቶባት
ድንገት

ቡፍ

ስቃ እንዳይፈስባት

ያፍዋ ጉንጭት።

ስለዚህ፣ እየተከላከለች

ከዚያው ከቀልኛው ጋራ

ሸጎዩ

(የቆቱ ዳንኪራ)

. . . . . . . . . .

ዝናብ ሰበርዋ ጨረቃ

እንደ ነገራ ነገሩ ደምቃ

ጥድፈያው

የጨረቃዋን ብርሃን ሽሚያ ነው።

ድንገት ያ ነጩ ደመና

ጠቁሮት

ያ ጥቁረቱ ሟሙቶት

ሰማይ መሬቱን ሳያሾቅ

ከማዶው መንደር ለመድረስ

ሸጎዩ ሊደነስ

ሌቱን ሙሉ

አዳር ይፈቅዳል ባህሉ።

. . . . . . . . . .

ደይና ሙሩ ደይና

(የግዝረታዊ ቀዶ ጥገና)

ስዱብሮች ክብርና

ዋስትና።

ዋስትና አላት ፋጤ ኢብሮ

ያለ ፍርሃት ለመጨፈር

ለመዳራት ሳይታፈር

ሌቱን ሙሉ ጨፍሮ ፍሮ::

(የተስፋ እግር ብረት: 135 - 136)

መ. ወለለት አምጭ ቃላት

ጥያቄዎች:

1. የመንግስት አዋጆች፣ መግለጫዎች፣ ወዘተ. በመገናኛ ብዙሃን ሲቀርቡ በገደል ማሚቶ (echo) እንዲታጀቡ የሚደረገው ለምን ይመስልሃል (ይመስልሃል)?

2. በገደል ማሚቶ በመታጀብ እና ሌጣቸውን በመገናኛ ብዙሃን በሚቀርቡ አዋጆች፣ መግለጫዎች፣ ዜናዎች ግጥሞች ወዘተ. መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

3. አብዛኞቹ የገበያ ማስታዎቂያዎች በገደል ማሚቶ እየታጀቡ የሚቀርቡበት ምክንያት ምን ይመስልሃል?

ቃላቱ:

- ወለለት አምጭ ቃላት የቃላቱን መጽረሻ ድምጾች አከታትሎ በማምጣት ይመሰረታሉ::
- የወለለት (echo) ባህሪ የሚታይባቸው ናቸው::
- ድምጽ ከገደል ማሚቶ ጋር ሲጋጭ ከሚፈጠረው ድምጽ ጋር ተመሳሳይ ናቸው::
- ከአንድ ድምጽን ከሚያንጸባርቅ ጋራ፣ ሸለቆ፣ ወዘተ. አካባቢ እንደሚሰማ ድምጽ (ማሚቶ) ይፈጥራሉ::
- በዚህም በአብዛኛው የቃላቱና ሃረጋቱ የመጨረሻ አካባቢ ድምጾች ተደጋግመው ይሰማሉ::

ከቃላቱ ስነግጥማዊ ፋይዳዎች ውስጥ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

- ሙዚቃዊ ቃናን ይፈጥራሉ፡፡
- የምስል ደረጃን ከፍ ያደርጋሉ፡፡
- ትኩረት ለሚደረግባቸው ገለጻዎች አጽንኦት ለመስጠት ያግዛሉ፡፡
- ሁኔታውን የበለጠ ስእላዊ ለማድረግ ያግዛሉ፡፡
- ጉዳዩን በአይን የመመልከትን ያህል አድርገው ያቀርባሉ፡፡
- በአጠቃላይ የገላጭነት፣ የምስል ከሳችነት፣ አዲስነትን የመፍጠር አዝማሚያ አላቸው፡፡

የሚከተለው ግጥም ለዚህ ምሳሌ ይሆናል፡፡

1. የመተሃራው ባላባት

አሁኑኑ፣ አሁን እንድታመጣ ወሬውን
ሙሽሮቹ ጀምረው እንደሆን
መረዳት፣ የሀብታችን መጠን፣ እንጀራችን
የቱን ያህል፣ የቱ እንደሆን፡፡
ይህን ብሎ፣ ጀመረ አባ ጉዳ
መጎብኘቱን ከዳስ እዳስ ከጓዳ እጓዳ
የሰው ጉንዳን፣ ኋላ ኋላው፣ ትርምስ - ምስ - ምስ
እርሱ እፊት እፊት፣ ገበስ - በስ - በስ
ገንደስ - ደስ - ደስ
ከዚያንንም ሲሻ አንዳች ማጣራት
ስለሆነው ነገር ስለሆነው ማለት
ያደርገዋል፣ ግራ ቀኙን ገርመ - መ - መም
እና ሲገረመሙም ጭጭ ምጭጭ ዝም
እኒያ፣ እኒያ፣ እኒያ የዙሮቹ
የሰው ጉንዳን የሰው ጉንዳኖቹ

ባባ ጉዳ ዙሪያ፣ የጉንዳን ስጦቹ::
አባ ጉዳ አሁንም አሁንም ባጀቦቹ
ጎረጥ - ረጥ - ረጥ
እና አጀቦቹም ትርምስ - ምስ - ምስ
ገስጥ - ስጥ - ስጥ
የመተሀራው ባላባት ዐይኖቹ ባዩበት::
(አፈር ያነሳ ስጋ: 48)

ሠ. የፈጠራ ቃላት

እነዚህ ቃላት:

- ግጥሙ በሚቀርብበት ቋንቋ መነሻነት በገጣሚው በራሱ የሚፈጠሩ ናቸው::
- በመሆኑም በመደበኛው የቋንቋ አጠቃቀማችን ውስጥም ሆነ በመዝገበ ቃላት ውስጥ አይገኙም::
- ግጥም የነጻነት ባህሪ ስላለው ገጣሚው ቃላትን መፍጠር ይችላል በሚለው እሳቤ ላይ የሚመሰረቱ ናቸው::

ገጣሚያን በእነዚህ ቃላት ግጥማቸውን በሚያቀርቡበት ጊዜ ልብ ከሚሏቸው ነጥቦች ውስጥ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ::

- በግጥሙ ውስጥ እንደፈርጥ አልፎ አልፎ ጣል ጣል መደረግ አለባቸው:: የግጥሙ ፈርጥ ሊሆኑ ይገባል፣ ይህ ካልሆነ ግን አሰልች ይሆናሉ::
- በቋንቋው ውስጥ በሚገኙ ቃላትና ሀረጋት ላይ ተመርኩዞ ሊፈጠሩ ይገባል::
- የፈጠራ ቃላቱን "ይህ ቃል ከየትኛው የተገኘ ነው?" ሲባል በቋንቋው ውስጥ የፈጠራ ቃላቱ መነሻ የሆነው ቃል ተፈልጎ ሊገኝ ይገባዋል::

ቃላቱ:

- የገላጭነት
- የሙዚቃዊነት

- የምስል ከሳችነት
- አዲስነትን የመፍጠር

ሚናን ይጫወታሉ፡፡

የሚከተለው ግጥም ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ይሆናል፡፡

1. የምድሩን ጉብታ ጥሳ
ከተረተር
ብቅ ስትለው ጀምበር
የጧቱ ቁር
ጤዛው ሳይቀር
ይረግፍና
እጸዋት፣ እንሰሳት፣ ፍጥረት ሲባልና
ተኮማትሮ የነበረው ሁሉ እንደገና
አንሰራርቶ
ተፍታቶ
ፈክቶ
የጧቱ ጎህ፣ በገፍ
ወረቃማው የብርሃን ጎርፍ
አፈር ቅጠሉን፣ ሲያጥለቀልቀው
እና ሲያብጫጫው
እና ሲያቅሳሳው
ሌላ ትሆናለች ህይወት
በዚያው በድህነት መልኳ፣ ያማረች
በልዩ ልዩ ቀለማት የተሸበረቀች፡፡
(ሰይፉ መታፈሪያ: አፈር ያነሳ ስጋ: 94)

ከዚህ በላይ በቀረበው ግጥም ውስጥ፡

- ሲያብጫጫው
- ሲያቅላላው
- የተሸበረቀች

የሚሉት የፈጠራ ቃላት ናቸው፡፡

ረ. ክሊሼ አንጋሽ ቃላት

እነዚህ ቃላትና ሀረጋት፡

- በተደጋጋሚ በአገልግሎት ላይ በመዋላቸው የተነሳ የቸኩ፣ የሰለቹ ቃላት ናቸው፡፡
- በመሰልቸታቸውና እጅ እጅ በማለታቸው የሚፈለገውን ነገር አያጎሉም፤ እንዲያውም ያደበዝዙታል፡፡
- በመሆኑም በአብዛኛው በስነግጥም ውስጥ በአገልግሎት ላይ አይውሉም፡፡
- በአገልግሎት ላይ የሚውሉ ከሆነም አሰልችነታቸውን ለመቀነስ ሲባል ለውጥ ያስፈልጋቸዋል፡፡
- በግጥም ውስጥ እንዳሉ ለወጥ ሳናደርግ አንገለገልባቸውም፡፡ ግጥሙ አሰልች እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡
- ግጥም የአዲስነት ባህሪ ያለው በመሆኑ ለወጥ በማድረግ ማቅረብ ይገባል፡፡

ምሳሌዎች፡

- የረቀቀውን አጐለቶ
- የተሰወረውን ገልጦ
- እንደሰም አቅልጦ ወዘተ.
- አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ

ገጣሚያን እነዚህን ቃላት በግጥሞቻቸው ውስጥ የሚገለገሉበት አጋጣሚ መኖሩን ግን ልብ ማለት ያሻል፡፡

- አንድ የተለየ አላማ ወይም ግብ ሲኖራቸው
- ለወጥ በማድረግ አስልቺነታቸውን ሲቀንሱት

ሰ. ነውር ቃላት

ቃላቱ፡

- የቋንቋው ተናጋሪ ህብረተሰብ በአይነኬነት የሚፈርጃቸው
- የሚገለገልባቸውን ሰው እንደ ባለጌ የሚያስቆጥሩ
- አብዛኛውን ጊዜ ሀገር እንደባለጌ የማስቆጠሩ ሁኔታ ጎልቶ የሚታይባቸው፡፡
- አብዛኞቹ ገጣሚያንም የሚሸሹቸው

ናቸው፡፡

እዚህ ላይ ግን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ማንሳት ይገባል፡፡

1. አንድ ቃል አይነኬ (ነውር) ላለመባል ወይም ለመባል መለኪያው ምንድነው?
2. ህብረተሰቡ ለመጥራት የሸሸው ቃል ሁሉ ነውር ይባላልን?
3. አንድ ገጣሚ እነዚህን ቃላት የመገልገል ነጻነቱ እስከምን ድረስ ነው?
4. ለመገልገል ወይም ላለመገልገል ከግንዛቤ ማስገባት የሚገባው ነጥቦች አሉን?

ገጣሚያን አንድ የተለየ ግብን ለመምታት ሲፈልጉ ቃላቱን ሊገለገሉባቸው ይችላሉ፡፡
ምሳሌ፡ ሰለሞን ደሬሳ፡ 1991፡ ዘበት እልፊቱ ወለሎታት "ክቡር ኢትዮጵያውን"፡፡

## 2.2. ዘይቤዎች

ስለዘይቤ ሲነሳ የሚከተሉትን ነጥቦች ማንሳት አስፈላጊ ነው፡፡

- የዘይቤ ምንነት
- የዘይቤ አስፈላጊነት
- የዘይቤ አመሰራረት
- የዘይቤዎች ብዛት

### 2.2.1. ምንነት

የዘይቤን ምንነት በሚመለከት እስከ ዛሬ ድረስ በርከት ያሉ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ፡

- "ለአገላለጽ ትኩስነት ለመስጠት ሲባል ከመደበኛው የቋንቋ አጠቃቀም ይሆነኝ ብሎ ማፈንገጥ ነው" የሚለው የሀሪሻው (Dictionary of literary terms) አገላለጽ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነትን ያገኘ ይመስላል፡፡

ዘይቤ ከተለመደውና በውል ከሚታወቀው የቃላትና የሃረጋት አገባብና ትርጉም ወጣ በማድረግ ለአገላለጽ ላቅ ያለ ደረጃ መስጠት ነው፡፡

### 2.2.2. አመሰራረት

ዘይቤዎች በተለያዩ መንገዶች ይመሰረታሉ፡፡

ከሚመሰረቱባቸው መንገዶች ውስጥ የሚከተሉት በዋነኛነት ይጠቀሳሉ፡፡

- አንድን ነገር ከሌላ ነገር ጋር በማወዳደር

- አንድን ነገር ከሌላ ነገር ጋር በማመሳሰል
- የአንድን ነገር ባህሪ ለሌላ ነገር በማላበስ
- የአንድን ነገር ባህሪ በመቅዳትና ለሌላ በመስጠት
- አንድን ነገር በሌላ በመወከል

ሆኖም አንድ ገጣሚ ዘይቤዎችን ሲመሰርት የሚከተሉትን ነጥቦች ከግንዛቤ ማስገባት ያስፈልገዋል፡፡

ሃያሲያንም ቢሆኑ አንድን ግጥም በውስጡ ከሚገኙት ዘይቤዎች ረገድ በሚገመግሙበት ጊዜ ከግንዛቤ የሚያስገቡት እነዚህን ነጥቦች ነው፡፡

- አዲስነት (ክሊሼ አንጋሽ ወይም የሰለቹ አለመሆን)
- ከግቡ ጋር በጥብቅ መጣመር፣ መዛመድ እና መቆራኘት
- የወጥነት ወይም የግላዊነት ደረጃ
- የሚገለጸውን ነገር የሚያጎሉ እንጅ የማያደበዝዙ መሆን
- በአንባቢ ወይም በአድማጭ አእምሮ ምስልን የመፍጠር ደረጃ
- ምናብን የማጫር ምናብን የመተንኮስ ደረጃ

ለምሳሌ፡

አዲስነት የሚለውን ብንወስድ

- ጠንካራውን - ብረት
- ሆዳሙን - ጅብ
- ክፉውን - ሰይጣን
- ቆንጆዋን - ጸሃይ የመሰለች
- ፈጣንና ቆፍጣናውን - ነብር

ማለት የተለመደ ነው፡፡

እነዚህ ደግሞ ብዙ ከማገልገላቸው የተነሳ

- የነፈሰባቸው፣ የሰለቹ እጅ እጅ ያሉ ናቸው፡፡

- ለረጅም ዘመናት ከማገለገላቸው የተነሳ አንድን ጉዳይ በማጉላት ፋንታ የሚያደበዝዙ ናቸው፡፡

በመሆኑም ዘይቤዎች ሲታሰቡ የሚከተሉትን ነጥቦች ከግንዛቤ ማስገባት ይገባል፡፡

- ዘይቤዎች የአመሰራረት ህግ ያላቸው መሆናቸውን
- ህጉን መነሻ በማድረግ መመስረታቸውን
- በቋንቋው ውስጥ እንደ ቃላት ተዘጋጅተው የተቀመጡ አለመሆናቸውን
- በቋንቋው ውስጥ ካለው ክምችት ውስጥ የማይመረጡ መሆናቸውን
- በአብዛኛው በራስ ምናብ የሚፈጠሩ መሆናቸውን
- ገጣሚው ተጨንቆ ተጠቦ፣ አውጥቶ አውርዶ የራሱን ሃሳብ በገልጽ የሚያሳዩለትን የራሱን ግላዊ የሆኑ ዘይቤዎች የሚመሰርት መሆኑን
- ከዚያ በፊት በሌሎች ገጣሚያን የቀረቡትንም ሆነ ባለቤታቸው የማይታወቁትን የቆዩ ዘይቤዎች ወስዶ ከመድገም ይልቅ በራስ እይታ በራስ ምናብ የተመሰረቱ የራስ ዘይቤዎችን መመስረት የሚሻል መሆኑን

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ከዘይቤ ጋር የተያያዙ ነጥቦች መነሻነትም አንዱ ገጣሚ ከሌላው በሚከተሉት ነጥቦች ይለያል፡፡

- በዘይቤ አመሰራረት ስልቱ
- በሚያተኩርባቸው የዘይቤ አይነቶች
- ዘይቤዎችን ለመመስረት እና ለሃሳቡ ማጉያነት በሚያስባቸው ነገሮች

የገጣሚው የዘይቤ አመሰራረት ወጥነትና ብቃትም በሚከተሉት በጥቦች መነሻነት ይወሰናል፡፡

- በምናብ ጥልቀቱ
- በቋንቋ ችሎታው
- ባሳለፈው የህይወት ገጠመኙና ልምዱ

- ነገሮችን በትኩረትና በጥልቀት በመመርመር ችሎታው

## 2.2.3 የዘይቤ ሚና በግጥም ውስጥ

ዘይቤያዊ አገላለጽ በግጥም ውስጥ ከሌላው አገላለጽ በተለየ ግብ መችነት አለው።

ዘይቤ ከሌላው አገላለጽ በተለየ ግብ መች ከሚሆንባቸው ምክንያቶች ውስጥ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ።

- ከተራው አገላለጽ ጋር ሲወዳደር የላቀ የቋንቋ አጠቃቀም ያለው በመሆኑ
- ለግጥሙ የኢዘርዛሪነት ባህሪ ስለሚያላብስ (በጥቂት ቃላት ብዙ ለማለት ማስቻሉ)
- ስሜትን ስለሚይዝ (የስሜት ቅርበትን ስለሚፈጥር)
- ተጨባጩን ረቂቅነት በማላበስ፣ አንባቢን ወይም አድማጭን በመንፈስ እንዲጓዝ ስለሚያደርግ
- ረቂቁን ስለሚያገዝፍ
- ለአገላለጹ ማራኪነት ውበትን ማጎናጸፉ (የልብ፣ ውስጣዊ ሃሴት መለገሱ፣ አስደሳች ስሜትንም መፍጠሩ)

## 2.2.4 የዘይቤ አይነቶች

የዘይቤዎችን አይነትና ቁጥር በሚመለከት እስከዛሬ ድረስ የተለያዩ አስተያየቶች ሲሰነዘሩ ቆይተዋል፤ በመሰንዘር ላይም ይገኛሉ።

የዘይቤዎችን ቁጥር በሚመለከት የሚሰነዘሩ አስተያየቶች ከሚለተሉት ነጥቦች ረገድ ይለያያሉ።

- ከባለሙያ ባለሙያ
- ከዘመን ዘመን

ከዘይቤዎች ብዛት ረገድ፡

- የተወሰኑ ምሁራን በአለም ደረጃ የዘይቤዎችን ቁጥር እስከ 250 ያደርሷቸዋል።

በአማርኛ ቋንቋ ውስጥም የዘይቤዎችን ቁጥር በሚመለከት የተለያዩ አስተያየቶች ሲሰጡ

ቆይተዋል፡፡

ከነዚህም ውስጥ የሚከተሉት በዋነኛነት ይጠቀሳሉ፡፡

- አንዳንዶቹ 29 አካባቢ ያደረሷቸዋል - ለምሳሌ አለማየሁ ሞገስ፡፡
- ሌሎቹ ወደ 21 ይደርሳሉ ይላሉ፡፡
- አብዛኞቹ ደግሞ ወደ 15 ያደርሷቸዋል፡፡

ምሁራኑ በአለም አቀፍ ደረጃ 250፣ በሃገራችን 29 አካባቢ የሚደርሱ ዘይቤዎች አሉ ይበሉ እንጅ አሉ የሚሏቸውን ዘይቤዎች ከሚከተሉት ነጥቦች ረገድ ተንትነው ለማሳየት አልቻሉም፡፡

- አመሰራረታቸውን
- የቅርጽ ባህሪያቸውን
- የአገባብ ባህሪያቸውን
- ስነጽሁፋዊ ፋይዳቸውን

በሃገራችን የዘይቤዎችን አይነትና በዛት በሚመለከት ችግር አለ፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ዋና ዋና የሚባሉት ችግሮችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የውጭውን ለኛ እንደሚስማማ አድርገው ሳይሆን እንዳለ ገልብጦ በማምጣት ለመገልገል መሞከራቸው (በስነልሳኑ ዘርፍ የንግግር ክፍሎች ሲባል እንደቆየው ማለት ነው)
- ዘይቤዎቹን በስነግጥም ውስጥ ካላቸው አገልግሎት ረገድ አለመመልከት
- በአብዛኛው በማገልገል ላይ በሚገኙትን ዘይቤዎች ላይ ብቻ አለማተኮር
- ልዩነታቸው ከጭራ የቀጠነ በመሆኑ በአንድ ሊጠቃለሉ የሚችሉ ዘይቤዎችን ራሳቸውን አስችለው በመዘርዘር ማስቀመጣቸው
- የዘይቤዎችን ቁጥር ከልክ በላይ ማብዛታቸው
- በአወቃቀራቸው ላይ ብቻ እንጅ በአገልግሎታቸው ላይ አለማተኮር

ከዚህ ቀጥለን አብዛኞቹ የአማርኛ ቋንቋ ገጣሚያን በግጥሞቻቸው ውስጥ ለሃሳብ ማጉያነት በብዛት የሚገለገሉባቸውን ዘይቤዎች አይነት እና በስነግጥም ውስጥ ያላቸውን ፋይዳ እንመለከታለን፡፡

ገጣሚያን እነዚህን ዘይቤዎች በግጥሞቻቸው ውስጥ ለሃሳብ ማጉያነት በሚገለገሉበት ጊዜ በሚከተሉት ነጥቦች ይወሰናሉ፡፡

- በስነጽሁፋዊ ስልታቸው
- በዘይቤ ምርጫቸው
- በችሎታቸው
- በህይወት ልምዳቸው
- ለሚኖሩባት አለም እና ለሰው ልጅ ህይወት ባላቸው አመለካከት

በነዚህ ነጥቦች መነሻነት፡

- አንዳንድ ገጣሚያን በአንዱ ወይም በተወሰኑ ዘይቤዎች ግጥሞቻቸውን ያዋቅራሉ፡፡
- ሌሎቹ ደግሞ በሌሎቹ ዘይቤዎች ግጥሞቻቸውን ይጽፋሉ፡፡

ለምሳሌ፡

- ገ/ክርስቶስ ደስታ አነጻጻሪ፣ ተለዋጭ እና ሰውኛ ዘይቤዎችን በሃሳብ ማጉያነት በስፋት ተገልግሎባቸዋል፡፡
- ፈቃደ አዘዘ ደግሞ ተምሳሌት ዘይቤዎችን በከፍተኛ ደረጃ ይገለገልባቸዋል፡፡

በስነግጥሞች ውስጥ የሚገኙት የዘይቤዎች ቁጥርም በሚከተሉት ነጥቦች መነሻነት ይለያያል፡፡ እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ

- በአንድ ስንኝ
- በአንድ አንጓ
- በሙሉ በግጥሙ

ውስጥ ተደራራቢ ዘይቤዎችን የምናገኝበት ጊዜ አለ።

አንድ ስነግጥም እንደ ገጣሚው ምርጫ በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊመሰረት ይችላል።

- በአንድ አይነት ዘይቤ ብቻ
- በሁለት ዘይቤዎች
- በሶስት ዘይቤዎች
- ከሶስት በሚበልጡ ዘይቤዎች

በግጥሙ ውስጥ ካሉት ዘይቤዎች ውስጥ፡

- አንዱ አብይ (ዋና የሃሳብ ማጉያ)
- ሌሎቹ ንኡሳን (ዋናውን የሚደግፉ)

ሊሆኑ ይችላሉ።

ዋናው ነገር፡

> "በግጥሙ ውስጥ በሃሳብ ማጉያነት የገቡት ዘይቤዎች መኖር ለግጥሙ ያበረከተው አስተዋጽኦ ምን ያህል ነው?" የሚለው እንጅ በውስጡ ያሉት ዘይቤዎች ብዛት አይደለም።

ከዚህ በመቀጠል ከዚህ በላይ የተሰነዘሩትን ነጥቦች ከግንዛቤ በማስገባት፣ በአማርኛ ቋንቋ ግጥሞች ውስጥ ገጣሚያን በስፋት የሚገለገሉባቸውን ዋና ዋና ዘይቤዎች አጠር አጠር በማድረግ እንመለከታለን።

## ሀ. አነጻጻሪ

የዘይቤው አመሰራረት፡

- ሁለት ነገሮችን በማነጻጸር ይመሰረታል።
- የሚነጻጸሩት ነገሮች ከአንድ ወይም ከተመሳሳይ ጎራ ሊመጡ ይችላሉ።

የሚነጻጸሩት ነገሮች ከአንድ ጎራም ይምጡ ከተለያዩ ጎራዎች ዋናው ነገር፡

- የጋራ የሆነ የሚዛመድ ባህሪ ያላቸው መሆኑ ነው፡፡

የዘይቤው አላማም፡

- አንዱን ከሌላው ጋር በማነጻጸር ማጉላት ደረጃውን ከፍ ማድረጉ ላይ ነው፡፡

በመዋቅራዊነቱ በኩል በዚህ ዘይቤ ውስጥ የሚከተሉት ነገሮች ይኖራሉ፡፡

- ገላጭ
- ተገላጭ
- የጋራ ባህሪ (የንጽጽር ሰበብ)
- የማነጻጸሪያ ቃላት

ገጣሚያን ይህን ዘይቤ በግጥሞቻቸው ውስጥ በሚገለገሉበት ጊዜ፡

- አንዳንድ ጊዜ በማገለገል ላይ ያሉትን አነጻጻሪ ዘይቤዎች እንዳሉ ይወስዳሉ፡፡
- ሌላ ጊዜ በሌሎች ሰዎች ተመስርተው ሰፊ ተቀባይነት ያገኙትን አነጻጻሪ ዘየቤዎች ይመርጣሉ፡፡
- በሌላ ጊዜ ደግሞ የራሳቸውን አዳዲስ ዘይቤዎች ይመሰርታሉ፡፡

ከላይ የቀረቡት ሁሉም ያስሄዳሉ፡፡

ዋናው ነገር በግጥሙ ውስጥ ያለው አነጻጻሪ ዘይቤ፡

- በግጥሙ ውስጥ የቀረበውን ሃሳብ ማጉላቱ
- የአንባቢን ወይም የአድማጭን ስሜት መንካቱ
- ግጥሙን የጥሩ ግጥም ባህሪ ማላበሱ
- ምናብን መፍጠሩ እና ምስል መከሰቱ

ላይ ነው፡፡

ገጣሚው በአገልግሎት ላይ የቆዩትን አነጻጻሪ ዘይቤዎች በሚገለገልበት ጊዜም ሆነ የራሱን

*አነጻጻሪ ዘይቤዎች በሚፈጥርበት ጊዜ ግን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡*

*ዘይቤዎቹ፡*

- *ክሊሼ አንጋሽ እንዳይሆኑ መጠንቀቅ*
- *የገላጭነት፣ የማጉላት፣ ምናብን የማጫር አቅማቸው የደበዘዘ እንዳይሆን መጣር*
- *ሊጎላ የተፈለገውን ነገር የማደብዘዝ አዝማሚያ እንዳይፈጥሩ ማሰብ*

*ይጠበቀበታል፡፡*

*በዘይቤው ውስጥ ከገላጭና ተገላጭ ረገድ አራት የማነጻጸር ሂደቶች አሉ፡፡*

1. *ተጨባጩን በተጨባጭ ማጉላት*
   - *የሚጎላውም ሆነ የሚያጎላው ተጨባጭ ነገር ነው፡፡*

     *ምሳሌ፡ ከተቀመጠችበት እንደኳስ ነጥራ ተነሳች፡፡*

     *ሎሚ የማመሰለው ተረከዟ አይንን ይስባል፡፡*

2. *ተጨባጩን በረቂቅ ማጉላት*
   - *የሚጎላው ተጨባጭ ሲሆን የሚያጎላው ደግሞ ረቂቅ ነገር ይሆናል፡፡*

     *ምሳሌ፡ የቀለም አባቴን እንደመጽሃፍ ቅዱስ ቃል አከብረዋለሁ፡፡*

     *አባቴን እንደ እግዚአብሄር ቃል አከብረዋለሁ፡፡*

*እዚህ ላይ ላይ አንድ ጥያቄ ማንሳት ይገባል፡፡*

*"የሚዳሰስ፣ የሚታይ፣ በራሱ የጎላ፣ እንዴት ሆኖ ነው በማይዳሰስ፣ በማይታይ እንኳን ሌላውን ሊያጎላ በራሱ ያልጎላ ነገር የሚጎላው?" የሚል፡፡*

አንድ ነገር የሚጎላልን ተጨባጭም ይሁን ረቂቅ ጉልህነቱን ልብ ባልነው፣ ስሜታችንን በሚነካን በሌላ ነገር በኩል ሲቀርብ ነው፡፡

3. *ረቂቁን በረቂቅ ማጉላት*
   - *የሚጎላውም ሆነ የሚያጎላው ረቂቅ ነገር ነው፡፡*

ምሳሌ፡ ፍርሃት እንደብርድ አንቀጠቀጠው፡፡

4. ረቂቁን በተጨባጭ ማጉላት

- የሚጎላው ረቂቅ ሲሆን የሚያጎላው ደግሞ ተጨባጭ ነገር ነው፡፡

ምሳሌ፡ እንደመርግ የከበደ ሃሳብ ይዞኛል፡፡

እንደ ጋራ የማልገፋው ሃዘን ወድቆብኛል፡፡

እንደ ቋጥኝ የከበደ ሃዘን ደርሶብኛል፡፡

የተለያዩ ገጣሚያን እንደራሳቸው ምርጫ እና ስልት ከላይ ከተጠቀሱት የማነጻጸሪያ ስልቶች ውስጥ አንዱን፣ ሁለቱን፣ ሶስቱን ወይም አራቱን በመምረጥ ግጥሞቻቸውን ያቀርባሉ፡፡

ዋናው ገዳይ፡

- የዝንባሌ እና የምርጫ
- የንጽጽር ሂደቱ በግጥሙ ውስጥ የተጫወቱት ሚና
- የገላጩና ተገላጩ ውህደት ወይም ጥምረት
- የገላጩ ተገላጩን የማጉላት አቅም
- የተገላጩ በተለመደው መንገድ ከሚገለጸው የበለጠ ጎልቶና ደምቆ የመገኘት ደረጃ

ነው፡፡

በመሆኑም ገጣሚያኑ በራሳቸው ምርጫ በተለያዩ የነጻጸሪያ ስልቶች ግጥማቸውን ያቀርባሉ፡፡ አንባቢያን እና ሃያሲያንም ጥያቄ ማንሳት ያለባቸው "ገጣሚያኑ በአቀራረባቸው ተሳክቶላቸዋልን?" ብለው ነው እንጅ "ለምን ይህኛውን የማነጻጸር ሂደት መረጡ?" ብለው መሆን የለበትም፡፡

የሚከተሉት ግጥሞች ለአነጻጻሪ ዘይቤ በጥሩ ማስረጃነት ይጠቀሳሉ፡፡

1. እኔ እወድሻለሁ

............................

እኔ እወድሻለሁ

የሰማይ መሬቱን

የባህር ስፋቱን

የአለም ዳርቻ የርቀቱን ያህል

እንደ ጽጌረዳ

እንደ አደይ አበባ

እንደ ሎሚ ሽታ

እንደ ከርቤ፣ ብርጉድ፣ እንደእጣን ጢስ እንጨት

ውድ እወድሻለሁ

አበባ እንዳየ ንብ

እንደ ቢራቢሮ ጫካ እንደሚያስሰው

ፍቅርሽን በፍቅሬ በፍቅርሽ ልቅመሰው

ማር ወለላዬ ነሽ ከረሜላ ስኳር

አማርኛ አይበቃ

ወይ ጉድ!

ባለም ቋንቋ ሁሉ ቢወራ ቢነገር

እኔ እወድሻለሁ

እንደ ማታ ጀንበር

እንደጨረቃ ጌጥ

እንደተወርዋሪ ኮከብ እኔ እማልጠግብሽ

ስወድሽ ስወድሽ

ስወድሽ ስወድሽ

ጡት እንዳየ ህጻን ወተት እንዳማረው

ጠጋ በይ ዘመዴ አፍሽ ህይወቴ ነው::

..............................................

(ገብረ ክርስቶስ ደስታ)

2. ቀረሽ እንደዋዛ

እንደ ድመቶቹ
የትም እንደሚያድሩት
እንደስልክ እንጨቶች
እንደዛፍ ሀረጎች
እንደቤት ክዳኖች
ብርድ አቆራመደኝ
ስጠብቅ ስጠብቅ፡፡
"ትመጫለሽ ብዬ ሳይ ማዶ ሳይ ማዶ
የልጅነት አይኔ ሟሟ እንደበረዶ"
ትመጫለሽ ብዬ ደቂቃ ስቆጥር
ትመጫለሽ ብዬ ሰአቱን ስቆጥር
ትመጫለሽ ብዬ ባዝን ባንጐራጉር
ትመጫለሽ ብዬ በበራፍሽ ብዞር
ብርድ አቆራመደኝ
የመንገድ መብራቶች አይተው አፌዙብኝ
ወንዙ ቀለደብኝ
ጨለማው ሳቀብኝ
አለመምጣትሽን
    አውቀዋል ያውቃሉ
መስኮቶች ጨልመው
    ቤቶች ተቆልፈው
ከተማው ሲተኛ
አይተዋል ያያሉ
አለመምጣትሽን
አውቀዋል ያውቃሉ፡፡
..............................
(ገብረ ክርስቶስ ደስታ)

3. በነግ ነግ

እዛፎቹ ጫፍ ላይ

እንዳለችው ጎጆ

እንደተበሳሳ

የውሃ ኮሮጆ

እየተሳቀቀ

ልቤ እያላዘነ

አይ ከነገ ዛሬ

ይሆናል ከሆነ

እንገናኛለን

ግድየለም እያለ

እንደተሳቀቀ

እንዳጉተመተመ

እንደጥቅምት ጉም

ነጎደ በነነ

በነግ-ነግ በነግ-ነግ

በነግ-ነግ ዘመነ

ባለመዘንጋቱ

ህሊና አለቀሰ

"ጨዋታ ፈረሰ

ዳቦ ተቆረሰ"

ልቤም ልብነቱን

በልቡ ወቀሰ።

(ሰናይት አበራ፡ 1990፡ *እኛ 170 ግጥሞች፡* 156)

**ለ. ተለዋጭ**

*አመሰራረት፡*

- *የአንድን ነገር ባህሪ ለሌላ በመስጠት (በማላበስ) ይመሰረታል፡፡*

*ዘይቤው የአነጻጻሪ ዘይቤ ሌላው ገጽታ ነው፡፡*

*ከአነጻጻሪ ዘይቤ በሚከተሉት ነጥቦች ይለያል፡፡*

- *የማነጻጸሪያ ቃላቱ በግልጽ ባለመኖራቸው*
- *የጋራ ባህሪው ይፋ ሆኖ ባለመቀመጡ*
- *የማነጻጸሪያ ቃላቱና የጋራ ባህሪው በአንባቢው ወይም በአድማጩ የሚሞሉ በመሆነናቸው*

    በዘይቤው ውስጥ የሚገኙትን የማነጻጸሪያ ቃላት በግልጽ በማስቀመጥ፣ የጋራ ባህሪውንም ቁልጭ አድርጎ በማመልከት ይህን ዘይቤ ወደ አነጻጻሪ ዘይቤ መለወጥ ይቻላል፡፡

- *በባህሪው የበለጠ ክረት የሚታይበት መሆኑ*
- *በተለይም በውስጥ የታመቀና ገነፍሎ ልውጣ ልውጣ እያለ ጊዜ የማይሰጥ ስሜትን ከአነጻጻሪ ዘይቤ በበለጠ ለመተንፈስ የሚያችል በመሆኑ*
- *ሃሳብን በጣም ፈጣን በሆነ መንገድ ለመግለጽ በማስቻሉ*
- *የአነጻጻሪ ዘይቤ አቋራጭ መንገድ በመሆኑ*

*ተለዋጭ ዘይቤ ከዚህ በላይ የተጠሱት ባህሪያት ባለቤት ለመሆኑ ማስረጃው*

- *አብዛኞቹ በፍጥነት የሚወጡ ግጥሞች (ለምሳሌ የፉከራ ግጥሞች) በዚህ ዘይቤ የሚዋቀሩ መሆናቸው ነው፡፡*

*ገጣሚያን በዚህ ዘይቤ ሃሳባቸውን በሚገልጹበት ጊዜ፡*

- *በሚነሳውና በሚያነሳው ነገር መካከል የጠበቀ ቁርኝት (ጥምረት) ሊኖር ይገባል፡፡*
- *ስሜትን መያዝ አለበት፡፡*
- *አንዱ ሌላኛውን የሚያነሳ ሊሆን ይገባዋል፡፡*

የሚከተሉት ግጥሞች ከሌሎች ዘይቤዎች በበለጠ በተለዋጭ ዘይቤ የተዋቀሩ ናቸው።

1. የፍቅር ቃጠሎ

ጉንጭሽ ጽጌረዳ
ሞቆት የፈነዳ
አይንሽ የጧት ጨረር ያበራ ማለዳ
የማትጠገቢ የስንዴ ራስ ዛላ አገዳ ጥንቅሽ
ጣፋጭ ከረሜላ የማር እሸት ነሽ
ጠብ አትይ አንጀቴ ባኝክ ብመጥሽ።
ቆንጆ ነሽ አንችዬ
እሳት ነበልባል ነሽ ንዳድ ባካላቴ
ሆነሻል ሙቀቴ
ሆነሻል ህይወቴ።
የጋለው ትንፋሽሽ
የሞቀው ምላስሽ
ማርኮኝ በከንፈርሽ
    እጄን ሰጥቻለሁ
    እስረኛ ሆኛለሁ
ያንቀጠቀጠኛል ወባ ቅናት ገብቶ
ልቤን አስፈራርቶ
ትኩሳት አምጥቶ
ፍቅረሽ አቃጠለኝ በመልክሽ ልተክዝ
እቀፊኝ ልቀዝቅዝ
ንከሽኝ ልደንዝዝ።
(ገብረ ክርቶስ ደስታ)

2.

አይ እኔ አይ አንች
ቀርተሽ አትቀሪ - ቀርቼ አልቀር
ኖረሽ አትኖሪ - ኖሬ አልኖር
ሄደት መጣ ብለን
ንፋግ ደመና ሆነን
  ስንጎመዣዥ በርቀት
  ስንሚገት በቅርበቱ
  ከረምን!
  እኔና አንች፡፡
(ፈቃደ አዘዘ፡ 1993፡ 77)

3. ያገር ልጅ
አካሄድሽ ይምጣ
አረማመድሽ
ጥርስ አገላለጥሽ
ከከንፈሮችሽ
ትህትናሽ አይለይ ከቅንነትሽ፡፡
አንገትሽ ብርሌ
ወይኒቱ
ማር ነሽ፡፡
እቀፉኝ ቢል እንኳን
ደግፉኝ አይልም
አቋቋመ መልካም
ወጣቱ ጡትሽ፡፡
ጨዋታ አዘወታሪ ቀበጥ ነው ዳሌሽ፡፡
ተረከዘ ሎሚ ጫማ የሌለሽ

ነይልኝ ያገር ልጅ

አውቃለሁ

አለሽ፡፡

(መንግስቱ ለማ)

4. ውሃ ማየጠፋው

ውሃ ማያጠፋው እሳት ነው ፍቅርሽ፡፡

ነደድኩኝ፡፡

ቢል አልኩኝ፡፡

ተቃጠልኩልሽ፡፡

ወደድኩሽ፡፡

ወደድኩህ በይኝ እባክሽ፡፡

(መንግስቱ ለማ፡1955፡22)

5. ጀግና

የወለደችው እናት አምጣ፣

ለሙያ ሚውል ሰበዝ ግራምጣ፣

የሚደባልቅ ዲቡን ከዲብ፣

ፈጥኖ ሚያረካ የቆንጆ ልብ፡፡

ክንዱ ያንበሳ መቼ የሌላ፣

ለጠላቱ እግር ክፉ አሜኬላ፣

አንደበቱ ጦር ቃሉ ምሳር፣

የሚቆራርጥ ሲሰነዝር፡፡

ወኔው ሃይለኛ ሰደድ እሳት

የሚለበልብ በሄደበት፡፡

ክንዱ ያንበሳ ቁጣው ግስላ፣

መካች የሌለው ደሙ ሲፈላ፡፡

ፍጥነቱ እንጅ ዛር የሰማይ ሲላ፣

ኮርቶ የኖረ ልቡ የሞላ፣

ጉልበቱ ሙላት የሃምሌ ጎርፍ፣

ከቶ አይደፈር አይታለፍ፡፡

ሲወለድ ብርቱ ያባቱ ልጅ፣

ባህር ሚያናውጥ የባህር መውጅ፡፡

መሳይ ቅዝምዝም ሲወነጨፍ፣

ወዘት የሚያደርግ የሚያራድፍ፡፡

እሱ ነበልባል ፈረሱ ላንቃ፣

ወኔው ጥሩ ፍም ላገር ሚበቃ፡፡

የገደል ጌታ የጎራ እሳት

አይኑ የንስር የሚያይበት፡፡

የበርሃ ገኘ የዋእይ ጌታ፣

ጥም አይበግረው ምን ቢንገላታ፡፡

ገና በሽሉ ከናቱ ሆድ

ይወራጭ ነበር ሲሻ መንገድ፡፡

..................................

**(ዮሃንስ አድማሱ፡ 1990፡ *እስኪ ተጠየቁ፣* 129 - 130)**

6. አስደንጋጭ

የፈነዳ አበባ . . . . .

ሰይጣን የቀናበት

እንደመልአክ ቆንጆ ነበረ ውበቷ

ዘመናይ እመቤት፡፡

አልማዝ ያስነጠፈች

ወርቅ ያስጎዘጎዘች

በሽነል፣ በዲየር ሽቱ የታጠበች::
በጌጥ ተብረቅርቃ፣
ጌጥ ሆና ገጥ ይዛ
ጨረቃ ታፍራለች
ጸሀይ ትጠፋለች
ጸዳል፣ ብርሃን፣ ንጋት ሁሉን ታስንቃለች
ስትናገር ስቃ
ድምጿ ነው ሙዚቃ::
ማር እንጎቻ ከንፈር . . . . .
ንግግሯ ህይወት ፈገግታዋ ሚስጥር
አልባብ ጠረን አፏ ጫወታዋ ፍቅር
ውብ የውብ ውብ ናት
የሌላ አለም ውበት
በከንፈሯ ገዳይ ጥርሷን አሳይታ
በጡቷ ተዋጊ ዳሌዋን መክታ
የሰራ አከላቷ ባለግርማ ሞገስ
ሰው የሚያፈራርስ::

## ሐ. ተምሳሌት:

አመሰራረት

- አንድን ሊገለጽ የተፈለገ ነገር በሌላ ነገር በመወከል ይመሰረታል::
- አንድ ነገር ለሌላ ጉዳይ በመቆም የሚቀርብበት ነው::

የዘይቤው ዋና መለያ ባህሪ ውክልና ነው::

በዘይቤው ውስጥ:

- በግጥሙ ውስጥ የቀረበውን ጉዳይ ለሌላ ጉዳይ የቆመ ነው ብሎ ማሰብን ይጠይቃል::
- በግጥሙ ውስጥ በግልጽ የተቀመጠው ጉዳይ ለሚባለው ነገር ሽፋን ሲሆን ዋናው ሊተላለፍ የተፈለገው ጉዳይ ግን በድብቅ የሚቀር ነው::

- በድብቅ ካለው ጉዳይ ላይ መድረስ ደግሞ የአንባቢው ወይም የአድማጩ ፋንታ ነው::
- በግልጽ በተቀመጠው እና ሊተላለፍ በተፈለገው ጉዳይ መካከል የጠነከረ ስሜት የሚሰጥ ተጠይቃዊ የሆነ ጥምረት ሊኖር ይገባል::
- ከህብረተሰቡ እምነት ባህል አመለካከት የውክልና ይትብሃል ረገድ በወካዩ እና ተወካዩ መካከል ያለው ዝምድና ትርጉም የሚሰጥ ሊያስሄድ የሚችል መሆን ይኖርበታል::
- ለበዙ ጊዜ በአገልግሎት ላይ በመዋላቸው የተነሳ የተምሳሌትነት ወዘናቸው የጠፉና ተራ አገላለጾች የሆኑትን አለመገልገል ይገባል::

ተምሳሌቱ ከሚከተሉት ነጥቦች ረገድ ሊገኝ ይችላል::

- በቃል ደረጃ
- በሀረግ ረገድ
- በስንኝ ረገድ
- ሙሉ ግጥሙ አንጻር

ዘይቤው በስነግጥም ውስጥ የሚከተሉት ፋይዳዎች አሉት::

- ግጥሙን ምስጢራዊ በማድረግ አንባቢን ወይም አድማጭን ያመራምራል::
- ገጣሚያንን በልዩ ልዩ ምክንያቶች መነሻነት በግልጽ ማስተላለፍ የፈለጉትን ጉዳይ ዞር አድርጎ ለመግለጽ ያስችላቸዋል::
- አንድን ነገር በቀጥታ ከመግለጽ መልእክትን በግልጽ ከማስተላለፍ ይልቅ ዞር በማድረግ አዲስነትን ለመፍጠር ያስችላል::
- ለአንድ ጉዳይ አያሌ የፍች ገጽተዎችን ለመስጠት ያገለግላል::
- የእያንዳንዱን አንባቢ ወይም አድማጭ ምናብ ለመተንኮስ ያስችላል::

ከሚወክሏቸው ነገሮች እውቅና ረገድ ተምሳሌቶችን በሶስት ከፍሎ መመልከት ይቻላል::

1. ሁለንተናዊ ተምሳሌት (ውክልናቸው ከሞላ ጎደል በአለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቁ)
    - ጨለማ - ለድንቁርና
    - ርግብ - ለሰላም
    - ጽጌረዳ - ለውበት
    - እሳት ለጥፋት
    - ተራራ ለማየጋፋት ጠላት

2. አካባቢያዊ ተምሳሌት (ውክልናቸው በአንድ አካባቢ ባህልና ወግ ላይ የተመሰረተ)
    - ጥቁር ልብስ
    - ነጭ ልብስ
    - ጺምን ማሳደግ
    - ጸጉርን መላጨት
    - አንገት ላይ ክር ማሰር

3. ግላዊ ተምሳሌት

- በገጣሚው ግላዊ ምልከታና ምናብ ይመሰረታል፡፡
- ገጣሚው ለተፈጥሮና ለህይወት ባለው አመለካከት ይወሰናል፡፡
- በአንባቢ ወይም አድማጭ ረገድም ሊገለጽ የተፈለገውን ጉዳይ ማግኘቱም የዚያን ያህል አስቸጋሪ ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ተምሳሌት ዘይቤዎች ግላዊነት ከገጣሚው ብቻ ሳይሆን ከአንባቢውም ረገድ ይታያሉ፡፡
ዋናው ነገር የገጣሚውም ሆነ የአንባቢው ተምሳሌትነቱን ተጠይቃዊ እና ምክንያታዊ በሆነ አይን መመልከቱ ነው፡፡

በአንድ ግጥም ውስጥ ከአንድ በላይ ተምሳሌቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

እነሱም በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ሊከፈሉ ይቻላሉ፡፡

1. አብይ ተምሳሌት
    - በሙሉ በግጥሙ ደረጃ የሚኖር እና በዋነኛነት ሊተላለፍ የተፈለገውን ሃሳብ የሚይዝ ነው፡፡

2. ንኡሳን ተምሳሌቶች
    - በቃል በሃረግ ወይም በስንኝ ደረጃ የሚኖሩ እና ዋናውን ተምሳሌት የሚያጎሉ ወይም የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡

ተምሳሌት ዘይቤን ለመፍታት ከግንዛቤ ከሚገቡ ነጥቦች ውስጥ የሚከተሉት በዋነኛነት ይጠቀሳሉ፡፡

- ግጥሙ የተጻፈለትን ህብረተሰብ ሁለንተናዊ የህይወት ገጽታ መመርመር
    - ፍልስፍናው
    - እምነቱ
    - የህይወት አመለካከቱ
    - ሃሳብን በውክልና የመግለጽ አዝማሚያው
    - በአካባቢው ለሚገኙ ነገሮች የሚሰጣቸው ውክልና
- ግጥሙ የተጻፈበትን ዘመን ማጤን
    - ከግጥሙ በስተመጨረሻ የተጠቀሰ ዘመን ካለ እሱን መነሻ ማድረግ
    - በግጥሙ ውስጥ ያለውን ማህበራዊ ዘመን ማገናዘብ
- የገጣሚውን ማንነት መመርመር
    - ፍልስፍናው
    - የሚወደው
    - የሚጠላው
    - በአካባቢው ላሉት ተጨባጭም ሆነ ረቂቅ ነገሮች የሚሰጣቸው ውክልና
    - የሃዘን መግለጫው

- የደስታ ማብሰሪያው
- ያደገበት አካባቢ (ቤተሰብ፣ ህብረተሰብ እና አካባቢ) ሁኔታ
- በአስተዳደጉ የገጠመው ሰናይም ሆነ እኩይ ነገር
- ሲመኘው የኖረው እና ያገኘው ወይም ያጣው

ጥያቄ፡ በሚከተሉት ሁለት ግጥሞች ውስጥ ያሉትን አብይ እና ንኡሳን ተምሳሌቶች ከነውክልናቸው አመልክቱ፤ በምሳሌ በማስደገፍም አብራሩ፡፡

1. አንድ ዛፍ አይቼ
ቅርንጫፎች ያሉት
በትጋት ያጀቡት
የዋህ የሚመስል ቁመናውን ሲያዩት
............................................
ግን ዙሪያውን ሳየው
በአይነ ልቡናዬ ሆን ብየ ብቃኘው
ቅርንጫፉና እሱ ሊያብቡ ቁርጠዋል
ሌላ ሌላውን ዛፍ አጠውልገውታል፡፡
ባንድ ላይ ዶልቶ
ደግሞም ተመክቶ
በሽር በጉልበቱ
ውሃውን እንደልብ ውስጥ ለውስጥ መጦ
መጦ በትምክህቱ
ኖሩም እንዳይባል ወይ ጨርሰው ሞቱ
እያቀማመሰ
ትንሽ እያላሰ
ነው ለካ የወፈረ
እስካሁን የኖረ፡፡

(ፈቃደ አዘዘ)

2. ጎጆዬ ጠላችኝ

እኔን የጠላሽኝ ያለምክንያት ነው
ብመክርሽ አይደለም እንደሚከተለው
ጣራሽ ይበል ሰቀል ግድግዳሽም ይስፋ
ምሰሶሽ ይጠንክር አትቁጭ ተስፋ::
ወለልሽ ይጎዝጎዝ ጎጆ ጎጆ ይበል
የውስጥሽም መደበ እኩል ይስተካከል
ግድግዳሽም ይስፋ ሽንቁሩና ቅዱ
ከውጭ እየገባ አይቆንድደኝ ብርዱ
ጣራሽ ችምችም በሎ በደንብ ይሰራልኝ
ያናቱ በረዶ እንዳይኮረኩመኝ::
ታዛሽ ሰፋ ይበል ካፍ እስከ ገደፍ
መጠለያ እንዲሆን ከርታታው በዚያ ሲያልፍ::

(ሃይሉ ገብረ ዮሃንስ: 1968: ፍንዳታ: 156)

የሚከተሉት ግጥሞች በዋነኛነት የተዋቀሩት በተምሳሌት ዘይቤ ነው::

ጥያቄ: በእያንዳንዱ ግጥም ውስጥ ያለውን ውክልና ተጠይቃዊ እና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ተንትነህ አሳይ::

1. መሰላል መውጣት

መሰላል ለመውጣት፤
አለው ትልቅ ብልሃት፤
የላዩን ጨብጦ፤
የታቹን ረግጦ፤
ወደላይ መመልከት፤

እጆችን ዘርግቶ በሃይል መንጠራራት፤
ጨብጦ መነተት የላዩን
ላዩ ታች እንዲሆን
አንድ ባንድ እየረገጡ፤
መሰላል የወጡ
ብልሆች የማይጣደፉ፤
ሞልተዋል በያፋፉ
ዘርግተው የጨበጡትን መርገጥ፤
የመውጣት ህግ ነው የማይለወጥ
ሲወርዱ ግን ያስፈራል፤
የረገጡትን ያስጨብጣል፡፡
(*መስፍን ወ/ማርያም*: 1967: *እንጉርጉሮ* 26)

2. የማለዳ ትእዛዝ
ልጆቹ ሳይነቁ
ጀንበር ሳትወጣ
ማልዶ የተላከ፣ እንግዳ ሳይመጣ
ጥጆቹን ሳትለቁ
ከሌሎቹ በፊት፣ ጥገቷን እለቧት፤
መቼም እልኸኛ፣ ተዋጊ ናትና
እንዳታውካችሁ
አሞሌ አልሱና
አስራችሁ የጋዲ፣ እንዳትረግጣችሁ
ያደገውን ግቷን ቶሎ ቶሎ ሳቡት
አይገኝምና፣ ታልጨከኑ ቅቤ፣
ካልተሻሙ ወተት፡፡
**(አረጋሽ ሰይፉ፡ 1990፡ *እኛ 170 ግጥሞች፡* 40)**

3. ጽጌሬዳ

አትንኩኝ ባይ ቆንጆ
ሆደባሻ አኩራፊ
ባይን የምትዳሰሽ
ደርሰሽ ተናዳፊ፤
ምነው እንደንቧ
መቅሰሚያ ቢኖረኝ
ሳትቆጭ አንዳፍታ
መንካት ነው ያማረኝ።
ከግንድሽ ስር ቆሜ
ጣቴን አስረዝሜ
ቀጥፌሽ ለጥሜ
ላንዲት እርካታ ድሜ፤
ብወስድሽ እቤቴ
ላውጋር ላድባራቴ
ብዙ ላትቆይልኝ
ይቅርብኝ አልንካሽ
ግንድሽ ላይ ኑሪልኝ፤
ዳግም አልቀጥፍሽም....
አልል ታምሪኛለሽ
ጉያየ እንዳልከትሽ ትቀጭብኛለሽ
እዚያው እግንድሽ ላይ ብተውሽ ፈርቼ
አለሽኝ እያልኩኝ .... እንድኖር ኮርቼ
ማራኪው ውበትሽ፣ ሰንጣቂው ድምቀትሽ
ሳልነካው ጠውልጐ
ወደቅሽ በገዛጅሽ

ለዚ ለዚህማ....ምንድን አደከመው ፈጣሪ ሲያበጅሽ::

(ፊርማዬ አለሙ: 1990: *እኛ 170 ግጥሞች:* 80)

4. **ቆሜ አየዋለሁ**

ስጓዝ በጎዳና፣
አገኘሁ መንገደኛ፣
እድሜው ከናሳሩ፣
የሚታይ በግንባሩ::
"እንዴት ነው?" አልሁት "መንገዱ
የመውጣት የመውረዱ፣"
"ለኔ ከንግዲህ ወዲያ ቁልቁለት ነው፣
መውረድ ብቻ ነው የቀረው::
አንተ አፋፉን ካለፍከው፣
አያደክምህም ሌላው::"
ብሎ መለሰልኝና፣
ሊሄድ ሲል እንደገና፣
ጠየቅሁት፣ "ስንት አፋፍ አለ?"
"እንደ መንገድህ ነው፣" አለ፣
"እንደፍላጎትህ፣
ማንም አይከለክልህ፣
ታች ታቹን ከሄድህ አፋፍ አትወጣም፣
አፋፍ ከወጣህ መውረድ አይቀርም፣
ሜዳ ሜዳውን ሰላም ነው፣
አፋፉ ላይ ነው ጭንቅ ያለው፣"
"እባክህ ምከረኝ
የትኛው መንገድ ነው የሚሻለኝ?"
ብዬ ብጠይቀው፣

ጭንቀቱ ፊቱን ሞላው፡፡
"መንገዳችን ለየቅል፤
አንተ ዳገቱን እኔ ቁልቁል፤
የኔ ላንተ አይሆንም፤
የሚሻልህን አላውቅም፡፡"
አለኝና ቀጠለ፤ ቁልቁለቱን፤
እኔም ቆሜ አየዋለሁ፤ አቀበቱን፡፡

(መስፍን ወ/ማርያም፡ 1967፡ እንጉርጉሮ፡ 27-28)

5. የእግር እሳት
ጽጌረዳ አበባ፤
ደም መስላ
ግን ደምቃ
ውበት ነው ቀለሟ፡፡
አይቻታለሁኝ፤
ልጅ ሆኜ አብባለች፤
ልጅ ሆኜ ከስማለች
ዛሬም ታብባለች
ደርቃም ታፈራለች፡፡
ሞቼም ታብባለች
ከስማ ትፈካለች
እሷ እኔን አይደለች፡፡
እሷ እኔን አይደለች፡፡
ያስቀናል ጺጋዋ፤
ውበት የመለገስ
ቃና የማደሷ
ሳለች በህይወቷ፤

ደርቃ ስትረግፍ

ፊት አለማጭገን

ተስፋ የመቸሯ::

(ፈቃደ አዘዘ: 1990: ሊያ ጎሽሜ: 42)

6. ለውጥ

ስከታተላት ጸሃዬን

ወርቃማዋን አበባዬን

ከጉርምስና እስካዋቂነት

ስከተላት ... ስከተላት

ሳሳድዳት ልደርስባት

ስከታተላት ልይዛት

በ66 ፈገግ ብትል

ቀበጥኩላት "ሞትኩላት" ገጠምኩላት

ግን እሷ አመጣችው ኋላ ኋላ ጉዷን

ጀመረች መድመቋን ጀመረች መቅለሟን

ለትናንሽ ፍሬ፣ ብላ ደም መልበሷን

የጥይት ግርግር ውይይት መፍቀዷን

ጀመረች መቅላቷን

አእምሮ ምኞቴን

እውቀትና ልቤን

በጩቤ ማበካትዋን

ነፍሴን አጨማልቃ

የእንባ ጎተራ፣ ከልቤ መትከሏን::

ሆኜ ፍቅኛዋ በየአደባባዩ ሳላፍር የተዳራሁ
በህዝብ ፊት ጮኬ እሷን የተጣራሁ
አቅጣጫዋን ባልወድ የዛሬ ርምጃዋን
ትቼ ማሳደዴን ጀመርኩ ቆሜ አያት::

ግን ህሊና አያርፍም::
እንደ ትናንትና፣ ዛሬም ያባርራል፤
የጥንት ተስፋውን ፊልም ውስጡ ያጠነጥናል::
ፊት ኋላ እያየ በነቂስ ያትማል::

ፍቅሬም ያቻትና አዝና ተደፍታለች
ታንጎራጉራለች
"አይሄ! የልጅ ነገር አልሰማህም ለካ
ሲባል ይሄ ሌላ ... ሲባል ያኛው ሌላ
ቅዝምዝሙ ወዲህ ... ፍየሉ ወደዚያ::"
(*ፈቃደ አዘዘ*: 1990: *ሒያ ጎሽሜ:* 44 - 45)

7. ዞሮ ሲገጥም
ጵጌረዳ ማበብ፣ አብቦ መፈንዳት
ፈነዳድቶ መፍካት፣
ፈልጋ - ፈልጋ...
ዘመን እምቢ ብሎ አፍኖ ቢይዛት
ሸሽታ ጫካ ገባች
ዘመን አስገብራ፣ ከዘመን ተሚግታ፣ አሸንፋም መጣች::

መጣሁ ስትል ፈክታ፤
ደግሞ የአዲስ ዘመን፣ ሌላ ጵጌረዳ፣

ፈለገች ለማበብ ፈነዳድታ ፈክታ፣

ምንም አልሆነላት፡፡
ዘመኑ ፊት ነሳት፡፡
"እንዳልንሽ ሂጂ እንጂ
እንዳልሺው አትሂጃት"
ብሎ ፊቱን ነሳት፡፡

እሷም ትሸሽ ይሆን፣ ትገባ ይሆን ጫካ?
በድል ልትመለስ ዘመን አስገብራ?

እኔስ ምንድን ልበል? የዚህ ሁል ታዛቢ
ሀገርስ ምን ይበል? ሸክሙን ተሸካሚ
**(ፈቃደ አዘዘ፡ 1989፡ *እየሄድኩ አልሄድም*፡ 31)**

8. ለሆዴ መድሃኒት
ሆዴን እያመመ በጣም ቢያስጨንቀኝ
መድሀኒት ለማግኘት ከሀኪም ቤት ሄድኩኝ
ከዚያ እንደደረስሁ ሀኪሙ ተጠርቶ
ልብሴን አስወለቀኝ አልጋ ተዘርግቶ
"ሆዴን ይቆርጠኛል ቅጥል ያደርገኛል
የኔውስ በሽታ በጣም አስግቶኛል
መድሀኒት እሻልኝ በጣም ጠንቶብኛል፡፡"
እንዲህ ስወተውት መፍትሄው ቸግሮኝ
ብልቃጥ አመጣና "ካፍህ አስቀምጥ" አለኝ፡፡
ግራ ቢሆንብኝ
የበሽታ አዋቂው ሀኪሙ ያዘዘኝ

አፌን ለሱ ትቼ ባሳቤ እንዲህ አልኩኝ።
"በሽታዬ ያለው በሆዴ ነገሩ
እነሱ ካፌ ላይ ምርመራ ጀመሩ?"
ይህን በመጠየቅ ራሴ በራሴ
እየተንተባተብኩ ቀንቼ ከራሴ
በእጄ እያሳየሁ "አውጡልኝ" አልኳቸው
"ለሙቀት ነው" አሉኝ ዶክተሮች አትኩረው።
አፌ ከተያዘ በሙቀት አሳበው
የሆዴን በሽታ እንዴት ልናገረው?
እኔ ዝም ካልኩማ ማን አለ የሚያውቀው?
ካልታመመው ስፍራ ካፌ ብልቃጥ ከተው
ዝም በል ይሉኛል በሽታዬን ስተው?
ምንስ እንደማደርግ ብዙ ሳልጨነቅ
የአፌን ውስጥ ብልቃጥ አደረግሁት ውልቅ
በዚህ ንድድ ብሎኝ በክፉ አይኔ እያየሁ
"ምን ማድረጋቸው ነው?" በማለት ተቆጣሁ።
እኒህ ሀኪሞቹ
ጤና ጠባቆቹ
መድሀኒት ያውቃሉ ሲሏቸው ሰዎቹ
የእኔን በሽታዬን የሚያሰቃየኝን
እንዴትስ እንደሆን ሳልናገር ቅጡን
እንደመሰላቸው በመተንፈሻዬ ብልቃጥ መክተታቸው
ይኸው ነው እንግዲህ አዋቂነታቸው ሀኪም ያስባላቸው?
አፉ እየተያዘ ዝም ያለው ሰው ሁሉ ጤና መሰላቸው?
በማለት አጋዤን ብወተውታቸው
ዳግመኛ ብልቃጡን አንስተው
ካፍህ አርገው አሉኝ ሙቀቴን እንዳውቀው

ደግሜ እንድከተው
ምኔ ነው ያበደው?
አፌ ከተያዘ በሽታዬን አውጭው
ስፍራውን ግድሚያውን ሁሉ የሚያሳየው
ሀኪሙ እንዴት ያውቃል?
ከአፍ መረመረና ስለሆድ ምን ያውቃል?
ብዬ ጠየቅኋቸው
ብቻ ምን ገብቷቸው
ሀኪም ቤት ዋሉ እንጂ መቼ ሀኪም ናቸው፡፡

. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

9. ቆቅ ለቆቅ

ዶሮዬ ቆቅ ሆነች፡፡
ከእጄ ውስጥ ሾለከች፡፡
ገባች ከጥሻው ውስጥ ወደ ጉራንጉሩ
"ካንዱ ወደ ሌላው መሽከረከር ማማሩ!!"
አለችኝ ሳገኛት
እኔም ቆቅ መሆኔን ማንም አልነገራት፡፡
(ፈቃደ አዘዘ፡ 1985፡ 06)

10. መሰላል

ለመንጠላጠያ ለእግር መራገጫ...
መሰላል ስንሰራ...
ከታች መደገፊያ.... ከላይ መወጣጫ
ስንደረድረው በተራ በተራ
አንዱንም ሳልጀምር ስንከራተት ገና
እኔ እንጨት ፍለጋ
ከዚያ ላይ ቁጢጥ አልክ...

ያንተ ሰው ሆነና...

አጥንትና ስጋ።

(መቅደስ ጀንበሩ፡ 1990፡ 109)

11. ያ የማየው ከሰል ያ ጥቁረት
ውስጡ የተቀበረው ፍም እሳት
አራጋቢ አራግቦት
እየተቀጣጠለ ሄደ
እየነደደ።
እና በትንታጉ ወጋገን
ስንቱን አየን
ስንቱን
ስንቱንስ ልናይ ይሆን
ስንቱን
ቢለቀን አይነ ጥላ
የሶስት ሺ አመታት ከለላ
እውርነት።
ያፍዝ ያደንግዝ ምትሃት።

(ሰይፉ መታፈሪያ፡ 1969፡ የተስፋ እግር ብረት፡ 19)

12. እምቡጥ ጽጌረዳ
እንቡጥ ጽጌረዳ - ከደጃፉ ተክሎ
ማነው የማይጠብቅ - ሁለት አይኑን ስሎ
ያውም ገና ለጋ - ቀንበጥ ጽጌረዳ
ለብዙሃን ሀሴት - ስትወጣ ማለዳ
ማነው ዘብ የማይቆም - ድንገት ስትፈነዳ።
...................................................

ውቢት ጽጌረዳን - ቀጥፎ ሊያጠወልግ
የመጣው በሽታ - ብዙ እጽዋት ሲጠርግ
እሷን ግን አልቻለም - እንኳንስ ሊቀጥፋት
በጁም አልዳሰሳት - በጣቱም አልነካት
ጓዴ ዘብ የቆመው - በክንዱ ከለላት፡፡
(አበራ ለማ፣ 1977፣ 15-16)

13. እንጃልሽኝ ንቢት
ንብ አርፋብኝ
መርፌዋን ተክላብኝ
ብትወጋኝ
አመመኝ፡፡ አመመኝ፡፡
እና ጥርጣሬ ገባኝ፡፡
0
የሚል፡-
ትሰጠው ይሆናል
ይህን ውጋት
ለሚሰጥዋት
ማር እምትሰራበት፡፡
0
ምስኪን አበባዎች
ሽብርቅርቅ ቀለማት
ሽቱ ኡደት
ጣፋጭ የሚመጠጥ
ሲለውጡ በውጋት፡፡
0
ምስኪን አበባዎች

ተጠቃን አያውቁ

ቁርሾ አይደብቁ

ያ በድንነታቸው

እንዴት ጠቀማቸው!

(ሰይፉ መታፈሪያ፣ አፈር ያነሳ ስጋ፡ 21)

## መ. ሰውኛ

ስለሰውኛ ዘይቤ ከመግለጽ በፊት የዘይቤዎችን አይነትና ቁጥር በሚመለከተው ክፍል የተነሳውን ሃሳብ ማስታወስ ተገቢ ነው::

በሃገራችን የዘይቤ አይነቶችን በሚመለከት የሚቀርበው ትንተና እንደሌላው የትምህርት ዘርፍ ሁሉ በቀጥታ ከውጭ ተተርጉሞ የገባ በመሆኑ አንዳንድ ቦታ ላይ

- ተጠይቃዊነትን ያልተከተለ
- ምክንያታዊ ያልሆነ
- ለኛ የማይስማማ

ሆኖ ይገኛል::

የተወሰኑ ዘይቤዎች:

- በመሰረታዊ ባህሪያቸው ተመሳሳይ ሆነው እያሉ
- ከሚለያዩበት ይልቅ የሚመሳሰሉበት ነገር ጎልቶ እየታየ
- ከጭራ የቀጠኑ ልዩነቶችን በቻ ከግንዛቤ በማስገባት

ራሳቸውን ችለው ሲስተናገዱ ቆይተዋል::

ለዚህ በአብይ ማስረጃነት ከሚወሰዱት ውስጥ የሚከተሉት ዘይቤዎች የጠቀሳሉ::

- ሰውኛ
- እንቶኔ

ዘይቤዎቹ በዝርዝር ነጥቦች፣ በአቀራረብ ረገድ ከመለያየታቸው በስተቀር በመሰረታዊው ጉዳይ ተመሳሳይ ናቸው::

የሁለቱም ዘይቤዎች:

- መሰረታዊ ባህሪና አመሰራረት ከሰው ጋር የተያያዘ ነው::
- የሚመሰረቱት ሰው ያልሆኑ ነገሮችን ወስዶ እንደሰው በመቁጠርና የሰውን ባህሪ በማላበስ ነው::

በዘይቤዎቹ መካከል ያለው ልዩነት ራሳቸውን ችለው ለየብቻ እንዲቆሙ የሚያስችላቸው አይመስልም::

<u>ሰውኛ</u> የሰውን ሁለንተናዊ ባህሪ ሰው ላልሆኑ ነገሮች በመስጠት ይመሰረታል::

በዚህ ዘይቤ ውስጥ ሰው ያልሆኑ ነገሮች እንደሰው:

- ይበላሉ
- ይጠጣሉ
- ይደሰታሉ
- ያዝናሉ
- ይቦርቃሉ
- ይስቃሉ
- ያለቅሳሉ
- ያስባሉ
- ክፉውን ከደጉ ደጉን ከክፉ ይለያሉ

<u>እንቶኔ</u> በአጠገብ የሌለን ነገር ከአጠገብ እንዳለ በማሰብ ይመሰረታል::

- ስለምናዊ ጥያቄ በማቅረብ
- እንደሚያዳምጥ በማሰብ
- መልስም እንደሚሰጥ በመቁጠር
    - የሚጠየቅበት

- የሚለመንበት
- ብሶና ችግር የሚገለጽበት

ነው::

ስለሆነም ከዚህ በላይ ባሉት ሁለት ዘይቤዎች መካከል ያለው ልዩነት በየራሳቸው ራሳቸውን ችለው ለመቆም የሚያበቃቸው አይመስልም::

ዘይቤዎቹን ራሳቸውን በማስቻል ለየብቻ ማስቀመጥ ከሚከተሉት ነጥቦች ረገድ ተጠይቃዊ አይሆንም::

- በመካከላቸው ያለው አንድነት ስለሚያመዝን
- በመሰረታዊ ጉዳይ ስለሚመሳሰሉ
- ለየብቻ ቢቀመጡ ለመለየት የሚያስችል ጉልህ ጉዳይ ባለመኖሩ
- ለየብቻ ማስቀመጡ የዘይቤዎቹን ቁጥር ማብዛት እንጅ ሌላ ከዚህ የጠነከረ ፋይዳ የሌለው በመሆኑ

<u>አሊጎሪ</u> ረቂቅ ለሚባሉ ነገሮች የተጨባጭነትና የሰውን ባህሪ በመስጠት የሚዋቀር ዘይቤ ነው::

ከነዚህ ረቂቅ ነገሮች ውስጥም የሚከተሉት ይጠቀሳሉ::

- ሃሳብ
- ክፋት
- ድንቁርና
- ተንኮል
- ትህትና
- ቅንነት
- እውቀት
- አሉባልታ
- ክህደት
- እብሪት
- ስስት
- ትእግስት
- ጀግንነት
- መሰሪነት

ይህ ዘይቤ፡

- ከላይኞቹ የሚለየው የሰውን ባህሪ የሚላበሱት ነገሮች ረቂቅ (abstract) በመሆናቸው ነው::
- በመሰረታዊው ጉዳይ (ሰው ላልሆኑ ነገሮች የሰውን ባህሪ ማላበስ) በሚለው ግን ከላይኞቹ ሁለቱ ጋር ይመሳሰላል::

እነዚህን ሶስት ዘይቤዎች ራሳቸውን አስችሎ ቦታ መስጠቱ

- አንዱን ከሌላው ለመለየት ስለሚያስቸግር
- ቁጥር ከማብዛት በስተቀር የሚሰጠው አገልግሎት እምብዛም በመሆኑ

በአንድ ላይ ማዋሀድ፣ ካስፈለገም በአንድ አበይ ክፍል ስር በንኡስነት ማስቀመጥ የሚሻል ይመስላል::

የሚከተሉት ግጥሞች ለሰውኛ ዘይቤ ምሳሌነት ይጠቀሳሉ::

1. ጸደይ ልትመጣ ነው ደገሰች አበባ
   ቁንን ተሰናድታ አቀረበች ኮልባ
   አደይም ጀመረች ቀይ ቀለም ትቀባ
   በለስ ከተፍ አለች ሰውነቷን ታጥባ
   ከወይኒቱ ጋራ አዳራሽ ልትገባ
   መሬት አነጠፈች ለምለም እሳርን
   ምድር ጎዘጎዘች ቅጠል ምንጣፍን
   በጣም ደስ እንዲላት መኖሪያቸው ደን
   ባመት የምትመጣ ወይዘሮ ጥቢን
   ጅረት ስታቀብል የጠጁን በተሃ
   ምንጭ ይዛ ደረሰች እጅግ የጠራ ውሃ::

(አለማየሁ ሞገስ: *የአማርኛ ግጥምና ቅኔ:* 68 - 69)

2. ዘመኑ ያዛጋል

ፍቅርን ተርቦ
ጥላቻን በልቡ
ስልቻ ጠቅጥቆ፡፡
ሰላምን ተርቦ
ቁንጣን ተወጥሮ
በጦርነት ጠግቦ፡፡
በቁንጣን በረሃብ
በጥጋብ ቀጣና
በመንታ ፈተና
አለም ያፋሽጋል፡፡
(ፈቃደ አዘዘ)

3. ቀረሽ እንደዋዛ
እንደ ድመቶቹ
የትም እንደሚያድሩት
እንደስልክ እንጨቶች
እንደዛፍ ሀረጎች
እንደቤት ክዳኖች
ብርድ አቀራመደኝ
ስጠብቅ ስጠብቅ፡፡
"ትመጫለሽ ብዬ ሳይ ማዶ ሳይ ማዶ
የልጅነት አይኔ ሚሚ እንደበረዶ"
ትመጫለሽ ብዬ ደቂቃ ስቆጥር
ትመጫለሽ ብዬ ሰአቱን ስቆጥር
ትመጫለሽ ብዬ ባዝን ባንጐራጉር
ትመጫለሽ ብዬ በበራፍሽ ብዞር

ብርድ አቆራመደኝ

የመንገድ መብራቶች አይተው አፌዙብኝ

ወንዙ ቀለደብኝ

ጨለማው ሳቀብኝ

አለመምጣትሽን

አውቀዋል ያውቃሉ

መስኮቶች ጨልመው

ቤቶች ተቆልፈው

ከተማው ሲተኛ

አይተዋል ያያሉ

አለመምጣትሽን

አውቀዋል ያውቃሉ።

..............................

(ገብረ ክርስቶስ ደስታ)

4. የልብ ሃሳብ

ነፋሱም ይናገር - አይኔን ያበሳጨው

ካፋፍ ላይ አቁሞ - ቀልቤን ያታለለው

ምሽቱም ይናገር - አይኔን የጋረደው

የቅርቤን የሩቁ - አድርጎ ያሳየው

ቁሩም ይመስክረው - እግሬን የሸመቀው

ህያው በድን ሁኜ - እንድቆም ያረገው፤

ውርጩም ይተርከው - አንጀቴን የበላው

አገኘሽ ይመስል - ልቤን ያማለለው፤

ይናገር! ይናገር - መንገደኛውም

ምን ሁኜ ምን ይገፍ - ምን እንደማልም፤

ይናገር መንገዱም - ባለ ኮረኮንቹ፤

ለልቤ ማረፊያ - ላገኝ እንደሁ ምቹ፤
ይናገር አገሬም - የኔም መንደርተኛ
እውን እችል እንደሁ - ያላንች ልተኛ፤
ይናገር ጎረቤት - ይናገር ቤተኛ
ሳልስል አድር እንደሁ - ሳላይሽ ብተኛ፤
አይኔን ባስከፋውም፣ በነፋስ ቁንጥጫ
እግሬን ባስቀጣውም፣ በቁሩ ግልምጫ
አንጀቴን ባስበላም፣ በውርጩ መንጋጋ
ያሰብኩት ሳይሞላ፣ መች ሌቱ ሊነጋ?
(አበራ ለማ የማለዳ ስንቅ፡ 37)

5. ብቻዬን…
ሰዎች ርቀው ካጠገቤ -
ዙሪያዬን ከቦኝ ጸጥታ
በጸጥታው መሀል ስገዝ -
ናፍቆቴን ውጪ በዝምታ…
ቅጠሎች ተንሾካሾኩ -
ገባኝ እኔም ሃሜታቸው
ከብቸኝነት በረሃ -
ብቻውን ቀረ ማለታቸው::
ጥላዬም ይህን ሰማና
በዝምታ ተከተለኝ
ሁሉም ቢከዱህ እንኳ
እኔ አልከዳህም እያለኝ…
እባክህ ተወኝ ጥላዬ
አትሞግተኝ በሽንገላ
ማየቴ አይቀርም ከቆየሁ -

**አንተም ስትከዳኝ እንደሌላ..**

**(ታገል ሰይፉ፡ 1986፡ 53)**

**6.** **ደስታና ሃዘን ተስፋና ፍርሃት**
**የሰውን ልጅ እድሜ ይዘው ያላባት**
**እየቆራረጡ ተከፋፈሏት፡፡**

**(ከበደ ሚካኤል)**

**7.** **እስኪ ሞት ተጠየቅ የሁላችን ጌታ**
**ይህን ሁሉ ፍጥረት የፍጥረት ሁተታ**
**ላንተ ለጎበዙ ገላችን በርግጡ**
**አንተስ ወደህ ገዛህ ወይስ ወደው ሸጡ፡፡**

**8.** **እብሪትን ሲጥለው...**

**እብሪት ልቡ ቢያብጥ - ቢልቅ ከተራራ**
**በምላስ ደንፍቶ - በአንገት ቢንጠራራ**
**ብልህ ነው እየሱስ - ቃል አልተነፈሰም**
**ከእብሪቱም ጋራ - ሽቅብ አልነፈሰም**
**በትሁት መንፈሱ - ዝቅ ዝቅ አለና**
**ከስሩ ዘርጥጦ - ጣለው ከጐዳና**
**(ጌታ የሃዋርያትን እግር ስላጠበ)**

**(ታገል ሰይፉ፡ 1986፡ 52)**

9\. **የፍቅር ሰላምታ**

**ጸጉርሽን ዳብሶ በጆሮሽ ያለፈው**
**ነፋሱ ምን አለሽ**
**በመስኮት ላይ ሆነሽ፡፡**

የፍቅሬን ሰላምታ ሲያስተጋቡ ይዘው
ተራሮች የላኩት፤
በሩቅ የሚታዩት፡፡
የሚወዛወዙት ቆመው በመስኮትሽ
ዛፎቹ ምን አሉ?
ያንሾካሹካሉ፡፡
አይተዋል ደብዳቤ ማታ ስጽፍልሽ
ይግለጹ ምስጢሩን
ልቤ መሸበሩን፡፡
ልብስሽን ስትለብሽ ወፎች የሚዘፍኑት
የሚሉት ምንድነው?
ጡቶችሽን አይተው፡፡
በፍቅርሽ ሰላምታ ልቤን እንዲያክሙት
ላኪያቸው ይምጡልኝ
መድሃኒቱን ይስጡኝ፡፡
ኮከቦች ከሰማይ ይጠቃቀሳሉ
ውበትሽን አይተው፤
በሰማዩ ባህር ጠልቀው ይዋኛሉ
ፍቅርሽን ሊይዙ
ወደኔ ሊጓዙ፡፡
ምን አለች ጨረቃ በመስኮትሽ ገብታ?
ስትነካ ፊትሽን
ተደግፋ አልጋሽን፡፡
ልኬልሽ ነበረ የፍቅር ሰላምታ
ጠይቂያት ውሰጅ፤
መልሱንም ስደጅ፡፡
የቤተክርስቲያን ደወሉ ዘመረ
ምን ሆኖ ይጮሃል?

ሰው ይሰበሰባል
ጉዳችንን አይቶ ገልጦ ተናገረ
እባክሽን ለፍቅር
ሞተን እንቀበር።
ምነው ምን ፈለገ ሲጨፍር ከበሮ?
ተነሳ የሚለኝ
የሚቀሰቅሰኝ።
ፍቅርሽና ፍቅሬን በመሃረብ አስሮ
እንሂድ ተቃቅፈን
ደብቶ ይውሰደን
የበረረው ልቤ ካጠገቤ ጠፍቶ
ምን ሚስጥር አወራ?
ደንግጦ እየፈራ።
ስታንጎራጉሪ መኝታሽ ቤት ገብቶ
የፍቅሬን ሰላምታ
ይስጥሽ በቀስታ።

***10.*** ***ነጻነት***

ነጻነት ኩሩ ነሽ የሁሉ በላይ
ውስጡንም ውጭውን አልደፈር ባይ!
ቃልሽ ሃይለኛ ነው ሞገዱ ሲነሳ
መንፈስ የሚያሸብር እንቅልፍ የሚነሳ
ገላጋይ የሌለው ጦር የማይፈራ
ቁም ነገር የማይል ፍዳና መከራ!
ድምጽሽ ሙዚቃ ነው ሞገዱ ሲጠፋ
ለሰስ ለዘብ ያለ ህይወት የሚያፋፋ
የሰላሙ ዜማ የጸጥታው ቃና

ፍቅር የሞላበት ኑሮን የሚያቃና!
ነጻነት ቅኑ ነሽ ለስም ለዝናሽ
ቁጣሽ ሃይለኛ ነው ሲነካ ክብርሽ!
ነጻነት ህያው ነሽ ረቂቅ መንፈስ
ጥይት አይገልሽም ቦምብ መትረየስ!
ከብረት እስር ቤት ጥቅጥቅ ካለ ጥሻ
እልፍ ዘብ ከቆመ ከመቃብር ዋሻ
ጥሰሽ ትወጫለሽ ነፃነት ነሽና
ማንም አይዝሽም በሀይል በጭቆና!!!

አሰፋ ገብረ ማርያም፣ 1977፣ ጽጌረዳ ብእር፣ 45-46)

**11.** **አባይ**

የጥቁር ምድር ጥቁር ወዝ
የደም ፈሰስ ጥምዝምዙ
ቅርሱ
ውርሱ
የሃበሻ ስም መጠሪያ
የወረደ ካቢሲኒያ
አባይ ጥቁሩ ኢትዮጵያ

ቂም አያውቄ ገራገሩ
አባዘራፍ አባቸሩ
የጁን ሰጥቶ ጦም አዳሪ
ጥጋብ ሰጥቶ ተበዳሪ

ተምዘግዝጎ ተኸጎድጉዶ
ጥቁር አፈር አገር ወስዶ

ሂዶ

ወርዶ

ከሰው ምድር ከሰው ኬላ
የቆየውን
የድሮውን
በደል ቂሙን ብሎ ችላ
ከርሰምድር ቋት ሲሞላ
ማነው እስቲ ገር እንዳባይ
ወዳጅ ጠላቱን እማይለይ
ጦሙን አድሮ ለሰው ሲሳይ

ስቆ ስቆ አሳስቆ
ተምነስንሾ ተፍለቅልቆ
ሲያፋልመን ካገር ጋራ
እግሩ ሳይቀር ለኛ አድልቶ
ሲያዛምደን ደም አቃብቶ
አባይ ልቡ መች ተገኘ
ለባዳ እንጂ የተሞኘ
የናቱ ልጅ አመድ አፋሽ
ደግ ሰርቆ ጠላት አፋሽ
ጥጋብ ሰጥቶ ችጋር ቀማሽ
ሺ ብሎ ፏ እየረገገ
ወዳጅነት በፈለገ
ምነው የጁን ተነፈገ?

(ሰለሞን፣ 1988፣ ምስጢር፡ 14፣19

12. ያለውን ለማጥፋት ገብታ በማይሆነው
ሁሉን ቅጥ ማሳጣት ለሷ ቁም ነገር ነው
የምትሄድበትን ሳታውቀው ጨርሳ
እውሯን የምትሄድ እንዲያው በዳበሳ
ሳትፈራ ሳትሰጋ ሳታስተውል አስባ
እያቅነዘነዛት ገደል የምትገባ
አውቃለሁ ትላለች እውቀቷን በትና
ክልፍልፍ እብድ ነች እመት ድንቁርና
የጥፋቷ ብዛት ልክ የለውምና፡፡
(ከበደ ሚካኤል ብርሃነ ህሊና፡ 90 - 91)

ሠ. በስመ ሃዳሪ

1. ልቤ ጎረቤቴ

ልቤ ቤት ሰርቶልኝ - ደም ቧምቧው አጠገብ
ቁለቁል ሲለኝ ቁለቁል - ሽቅብ ሲለኝ ሽቅብ
ሲዞር እዞራለሁ
ልቤ መኖሪያዬ - ለሱ እታገላለሁ፤
ቢሆንም፣
ከዚህኛው ቤቴ - ይሻላል የልቤ
አድሽኝ አይለኝ - አዲስ ነው ሃሳቤ፡፡
አልወራረድም - ከሌላው ቤት ጋራ
በንጨት በብነበረድ - በጡብ ከተሰራ፤
ቢመሽ አያስጠጉኝ - ብጠፋ አይፈልጉኝ
ሁሉ በሩን ዘግቶ - ይተረካከማል

ኑሮውን በምላጭ - ይከረካክማል
ሊያስገባ - ሊያስወጣ
ይወጣል ይገባል፤
እኔ ብዙም የለኝ - ከዚህኛው ቤቴ
እንዳሻው ያዙረኝ - ልቤ ጎረቤቴ
(ፈርማዬ አለሙ፡ 1990፡ *እኛ 170 ግጥሞች*፣ 87)

2. አይኔን ሰው ራበው አይኔን ሰው ራበው
የሰው ያለህ የሰው የሰው ያለህ የሰው፡፡
(ዮፍታሄ ንጉሴ)

3. ምነው ጨክን ልቤ
ምነው ጨክን ልቤ ድፍን ቅል ሁንልኝ
ምንም አላየህም ተጣጥፈህ ተኛልኝ
ምነው ጀግናው ልቤ ትርበተበታለህ
እንደ መንፈቅ ህጻን ትልመጠመጣለህ?
ማመንክን ፈርተኸው ወዴትም አትደርስ
ፈርተህ አታስፈራኝ እንባህን አታፍስ፡፡
ምነው ጨክን ልቤ ፍፍን ቅል ሁንልኝ
በቆራጥነትህ እምነት ይደርብኝ፡፡
ምንድነው ሽብሩ ምንድነው ቱማታው
ብቻህን ላታድር በቁምህ ፍራቻው?
ጨከንከን በልልኝ ወዳጄ ልቤ ሆይ
ክረምቱን ሸኝተህ እያት ያቺን ጸደይ፡፡
ምነው ጨክን ልቤ ድፍን ቅል ሁንልኝ
ምንም አልሰማህም ተጣጥፈህ ተኛልኝ፡፡

አንተ መቁረጥ ላታውቅ እኔ በጅ ላልል
ምነው አሰነበትከኝ ውስጤን ስታማስል?
ልቤ ቁረጥ አንጂ ጀግንነትህን ልየው
ፈቅጄ ለጠላው ማባበልህ ምነው?
ምነው ጨክን ልቤ ድፍን ቅል ሁንልኝ
ምንም አላየህም ተጣጥፈህ ተኛልኝ::
ልቤ እሹሩሩ ጭንቅ አይችል ወዳጄ
አዘንም ደስታ መጥቶ ያውቃል ከደጄ::
ብዙም አዲስ ነገር ለኔ ህይወት የለም
መታለል እንደሞት ትንፋሽን ቢቆርጥም::

**(አበራ ለማ 1977 17-18)**

## ረ. ምስያ

በዚህ ዘይቤ ውስጥ

- ሁለት ታሪኮች ይኖራሉ::
- አንዱ የሚያጎላው የሚያገዝፈው ነው::
- ሌላው ሊተላለፍ ሊጎላ የተፈለገው ነው::
- የገጣሚው ትኩረትም ይህኛው ይሆናል::
- አብዛኛውን ጊዜ የሚያጎላው ታሪክ ቀድሞ ይመጣል::
- የሚጎላው ወይም ሊተላለፍ የተፈለገው ታሪክ ደግሞ በግጥሙ መዳረሻ አካባቢ ተከትሎ ይመጣል::

ይህ ዘይቤ ሲዋቀር፡

- በሁለቱ ታሪኮች መካከል የጠበቀ የይዘት የባህሪ የአውድ ጥምረትና ቁርኝት ሊኖር ይገባዋል::
- ታሪኮቹ አብረው የሚሄዱ የሚስማሙ መሆን ይገባቸዋል::
- የመሸጋገሪያ ቃላትና ሃረጋት ሊኖሩም ላይኖሩም ይችላሉ::

ምሳሌዎች፡

የከበደ ሚካኤል ታሪክና ምሳሌ ውስጥ ያሉት አብዛኞቹ ግጥሞች በዚህ ስር ይካተታሉ፡፡

1. ጠዋት ብትታይም ጸሃይ ከፍ ብላ
የማታ የማታ እርሷም አሽቆልቁላ
አይቀርም መጥለቋ አይቀርም መውረዷ
ሰውንም ስናየው ሳለ በህይወቱ
እሸት ነው ለጋ ነው በወጣትነቱ
በጠዋቱ ጉዞ ምንም ቢበረታ
አይቀርም መድከሙ ሲመሽ ወደማታ፡፡
(አፈወርቅ ዮሃንስ፡ 1961፡ *ስሜታዊ ግጥሞች*፡ 5)

2. አበባ ስታምር ቀለሟ ሲወዛ
ታበሻታለች ጨካኟ ጥንዚዛ
ባንድ ሰው ላይ ሲያዩ አንድ መልካም ነገር
ምቀኞች በቶሎ ለማጥፋት ለማጥቆር
ተመልካችን ሁሉ ብላሽ ነው ሊያሰኙ
ተግተው ይሰራሉ እንቅልፍም አይተኙ፡፡
(ከበደ ሚካኤል፡ 101 - 102)

## ሰ. አያዎ

ዘይቤው

- ውሸት በሚመስል ነገር እውነትን ማስተላለፍ ነው፡፡
- ላይ ላዩን ሲያዩት እውነትነት የሌለው የሚመስል ከእውነታው ጋር የሚጋጭ ሃሳብ የያዘ ይመስላል፡፡
- ወስጡን ሲመረምሩት ግን እውነትነት አለው፡፡

- በወስጡ ተቃራኒነት የሚታይባቸው ሃሳቦችን ይይዛል፡፡
- ተቃራኒነቱ ግን የቅርጽ ሳይሆን የሃሳብ ነው፡፡
- ተቃራኒ ቃላትና ሃረጋት የሚገኙበት አገላለጽ ሁሉ አያዎ ሊባል እንደማይችል ልብ ማለት ይገባል፡፡

ጥያቄ፡ ከሚከተሉት ግጥሞች ውስጥ በአያዎ ዘይቤ የተዋቀሩት የትኞቹ እንደሆኑ በምክንያት በማስደገፍ ግለጽ፡፡

1. እንዲህ ከሆነማ
አለማስተዋሌን ካላስተዋልኩኝማ
ከዚህ የበለጠ ምን ሲኦል አለና፡፡

2. እንዲህ ከሆነማ
አለማየቴንም ካላየሁኝማ
ከዚህ የበለጠ ምን ጽድቅ አለና፡፡

3. ሲሉ ይደመጣል
ሲያወሩ ይሰማል
ጆሮ ምን ይውጣል
ጉሮሮስ ምን ሰምቷል፡፡

4. ወይ አለማወቁ ማወቁን መምጠቁን

5. አይ እናንተ
የአባቶቻችሁ ልጆች
የአያቶቻችሁ ወላጆች፡፡

6. አወይ የኔ ነገር

ልብ አለማለቴን ልብ አለማለቴ።

7. መካዴን ማመኔ ያስመሰግነኛል

ወይ ያሸልመኛል ለጽድቅ ያበቃኛል?

ወይስ በጉማሬ ያስተለትለኛል።

ወይስ ወደ ሲኦል ያስወረውረኛል።

8. አንተ ሰማያዊ ሰማይ

የተደፋህብን እንደ ወስከምባይ

ቢነግሩህ ታያለህ ወይ

ቢጠይቁህ ትመልሳለህ ወይ

ቢጠሩህ ወይ ትላለህ ወይ

9. በሚያፍሩት አይኖቼ

ባይ ሳስተውላቸው

አይን አውጣ አይኖችሽን

በላ አጣሁላቸው

10. መኖር ያለህይወት በተለመደበት በጨለማ ሃገር

11. አንድ አዲስ ተገኝቶ ሌለው ግን ካረጀ

የሚናደው ነገር ላዲሱ ከበጀ

በዘመን መለወጥ እየተነወረ

ይቅር ከተባለ ልማድ የነበረ

ጠቃሚ ከሆነ ሲነቀል ሲጠፋ

"ማፍረስም መስራት ነው" ይለናል ፈላስፋ::
(ከበደ ሚካኤል: የቅኔ አዝመራ: 150)

12. የሞት ሞት

እየኖሩ - መሞት
በሕይወት - እያሉ፣
ቆመው - እየሄዱ፣
ሰርተው - እየበሉ፣
እያዩ - ታውረው
ሞትን - ይሸሻሉ
ጆሮም - አንጠልጥለው
ፍጹም - ላይሰሙበት
የቁም ሞትን - ሞቶ
ግን ከመሞት - ሽሽት
እሱ ነው - የሞት ሞት
ሞቶ ሞትን - መፍራት::

(ሰናይት አበራ: 1990: *እኛ 170 ግጥሞች*: 174)

13. እሽክሌከንታ ወይም የእንባ ሽለቆ

...............................................

ሲቀርቡት የራቀ ሲርቁት ቀረበ፣
ሲመቱት ዝም ያለ ሲተው ደበደበ፣
ሲያበሉት የሸሸ ሲነሱት ነጠቀ፣
ሲችሉት ያልቻለ እየነቀነቀ፣
ሲጠሉት ይወዳል ሲወዱት ሚጠላ፣
ሳይጥዱት በሰለ ሲጥዱት ማይፈላ::
ቢቀልቡት ከሳ ሲራብ ደነደነ፣

በዘር ላይ ወፍሮ በመኸር ቀጠነ፡፡
ቢያጠጡት ተጠማ ሳይጠጣም ረካ፣
እስኪ ይኸ ሁሉ እንደምን ይለካ?
ሲያነዱት ሚጠፋ ፍህሙ ተንደርክኮ፣
ሲተውት ይነዳል እንደ ፍግ ታምኮ፡፡
ቢሞሉት ጎደለ ሲተውት የሞላ፣
ሲያስሩት የሚፈታ ቢያጠብቁት የላላ፣
ሲቀነበብ ወጣ ሲፈታ ታሰረ፣
አረቂ እየጠጣ በውሃ የሰከረ፣
በጭለማ ሚሄድ በብርሃን ታውሮ፣
ከገደል የሚዘል ከሜዳ ተሰብሮ፡፡
ሳይታጠብ የነጻ ቢያጥቡት የሚሸት፣
መታጀሉ ንጣት መንጻቱ ግማት፣
እንዲህ አይደለም ወይ የሰው ሁል ፈሊጥ፣
ስራው የውሃ ሽታ ኑሮው ግርምቢጥ፡፡
**(ዮሃንስ አድማሱ፡ 1990፡ *እስኪ ተጠየቁ፡* 9 -10)**

**14.** **አጸለሌ**
የጸጥታው ጩኸት፣ የሞቱ ህያውነት
የትላንት ዛሬነት፣
ከርሞ ማሙዬነት፣
ዘወትር ልጅነት፡፡
**(ፈቃደ አዘዘ)**

**15.** ከበረዶ እሚበርድ ከእሳት የሚያቃጥል፣
ጋራ የሚያወጣ አዘቅት ውስጥ እሚጥል፡፡
ከማጣት የከፋ ከማግኘት የሚበልጥ፣

አንዴም የሚገፋ አንዴም የሚመረጥ፡፡
ምንድን ነው ቢሏችሁ፣
እንዴት ነው መልሳችሁ?
የዘወትር ጤነኛ ሁልጊዜ ታማሚ፣
በቀላሉ እሚገኝ ሲፈለግ አድካሚ፡፡
እውነተኛ ሆኖ ውሸት ተናጋሪ፣
ከቤት ውስጥ ሳይወጣ ወንዙን ተሻጋሪ፡፡
ምንድን ነው ቢሏችሁ፣
እንዴት ነው መልሳቸሁ?
ከሩቅ የቀረበ ከቅርቡ የራቀ፣
ከጉልህ ያነሰ ከንኡስ የላቀ፡፡
ከወርቅ የከበረ ከነሀስ የረከሰ፣
በጣም የዘገየ ፈጥኖ የደረሰ፡፡
ምንድን ነው ቢሏችሁ
እንዴት ነው መልሳችሁ?
(አፈወርቅ ዮሀንስ፡ 1964፡ 15)

16. በመንገድሽ ስሄድ እየሄድኩ አልሄድም
በቃ እኔም ተሸነፍኩ ያንችም ጉድ አያልቅም፡፡

17. ፈላስፋ ሲመክር አደራ ብሏል
በምትሰራው ስራ ቀስ በለህ ቸኩል፡፡

ሸ. ምጸት

1. ግራ ገባኝ
አንበሳውን ልሁን ጡንቻዬን ላፈርጥም፤
በክርን እንዳደቀው ይህንም ያንንም፤

እባቡን ልሁነው ልቤን እግር ላርገው፤
ሰርስሬ መርዤ ደሙን እንድጠጣው፡፡
ምስጥ ልሁንና ሬሳውን ልብላ፤
የሞተው ሞቶልኝ ካለው አልጣላ፤
እስስቲቱን ልሁን ከሁሉም ልዳራ፡፡
መስሎ መብላት ሳለ ጠላት ለምን ላፍራ፡፡
ጥንቸልዋን ልሁነው በፍርሃት ልሽቆጥቆጥ፤
ሳገኝ እየበላሁ ሲመጡብኝ ልሩጥ፡፡
ውሻ ልሁንና ይቁላላ ጅራቴ፤
ግብዙን ላስደስት ይጫወት በእምነቴ፡፡
አህያውን ልሁን ልደድብ በትዕግስት፤
ይነርቱኝ ይዘው ይጫኑብኝ ኩበት፡፡
እውቀት እውነት እምነት ቅንነት ግልጽነት፤
ዋጋቸው ምን ይሆን? የሰውነቴ ሀብት፡፡
እውነተኛ ልሁን? ወይስ ልሁን ታማኝ?
የቱ ያኮራኛል? የቱ ነው እሚያበላኝ?
ለምን ላስብ ቀድሞ? ምንስ ያሰጋኛል?
ለሆዴ እንደሆነ ህሊናና አእምሮን መሼጥ ይበቃኛል፡፡
ልብላ? ልበስብስ በቁሜ? ከብሬ ልከበር?
ወይስ ልሙትና ኮርቼ ልቀበር?
ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ መሆኑን አውቃለሁ፤
አልቀበር እንጅ እኔኮ ሞቻለሁ
አላማው ጠፋብኝ፤ ፍጹም ግራ ገባኝ፤
መልአክነት ስመኝ፤ ሰው መሆን ከብዶብኝ፡፡
(መስፍን ወ/ማርያም፡ *እንጉርጉሮ* 30)

ቀ. ቀደም ጠቃሽ

ግጥሙ ከመጻፉ በፊት ያለን ወይም የተፈጸመን ጉዳይ በማምጣት ለሃሳብ ማጉያነት

መገልገልን ይመለከታል፡፡

አመሰራረቱም የሚከተሉትን ነጥቦች ከግንዛቤ ያስገባል፡፡

- ስነጽሁፋዊ ስራዎችን
  - ታላላቅ የኪነጥበብ ሰዎችንና ስራዎች
  - በኪነጥበባዊ ስራዎች የሚጠቀሱ ጊዜያትንና ቦታዎችን
  - የገጸባህሪያትን ስሞች
  - የገጸባህሪያትን ድርጊቶች
- ታሪካዊ ስራዎችንና ድርጊቶችን
  - ታሪክ በመጥፎም ሆነ በበጎ ጎን የሚያስታውሳቸውንና የሚያውቃቸውን ሰዎች
  - በታሪክ የሚታወቁ ሰዎችን መጥፎም ሆነ ጥሩ ድርጊትና ባህሪ
  - በታሪክ የተከናወኑ ወይም ተከናውነዋል ተብለው የሚታሰቡ ድርጊቶችንና ክንዋኔዎችን
  - በታሪክ የታወቁ ጊዜያትንና ቦታዎችን
- በሃይማኖታዊ ስራዎች ውስጥ የሚነሱ ጉዳዮችን

ለምሳሌ

1. የሼክስፒርን ስራዎች በመንተራስ
   - ስስታሙን ሻይሎክ
   - ተንኮለኛውን ኢያጎ
   - ውስጣዊ ቁንጅና ያላትንና የዋህዋን ዴዝዲሞና
2. የመጽሃፍ ቅዱስን ታሪክ በመንተራስ
   - የራሄል እንባ
   - የእዮብ ትእግስት
   - የሎጥ ሚስት
3. ፍቅር እስከ መቃብርን በመንተራስ

ዘይቤው ከሁሉም ዘይቤዎች በላቀ ደረጃ የገጣሚውንም ሆነ የአንባቢውን ታሪካዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ኪነጥበባዊ ግንዛቤ የማንበብ ልምድ ያነበበውን የማገናዘብ እና የመመርመር ችሎታ ይጠይቃል።

ዘይቤው ሲመሰረት የሚከተሉትን ነጥቦች ከግንዛቤ ማስገባት ይገባል።

- ለሃሳብ ማጉያነት የተመረጠው ታሪክ በርግጥም ሃሳብን የሚያጎላ መሆኑን መመርመር
- የሃሳብ ማጉያው አብይ ክንዋኔ መሆኑን
- በአንባቢ ወይም አድማጭ ዘንድ ልዩ ስሜትን የሚፈጥር መሆኑን ልብ ማለት
- በማጉያነት የተጠቀሰው ጉዳይ ከሚጎላው ጉዳይ ጋር የሃሳብ ጥምረት ያለው መሆኑን ማስተዋል
- ያጎላል ተብሎ የተመረጠውን ጉዳይ ሊገለጽ ከተፈለገው ድባብ እና አውድ ጋር በጥብቅ መቆራኘቱን ማጤን
- ገጣሚው በቀደም ጠቃሽነት የተወሰደውን ጉዳይ በዝርዝር እና በጥልቀት ጠንቅቆ የሚያውቀው መሆኑን ማጤን

የሚከተለው ግጥም በዋነኛነት የተዋቀረው በዚህ ዘይቤ ነው።

1. ለሁሉም ጊዜ አለው ይላል ሰለሞን
እጠይቀው ነበር በተገናኘን
ሞት የሚሞትበት ጊዜው መች ይሆን?

በ. ግነት

አንድ ሃሳብ፣ ድርጊት፣ ነገር፣ ወዘተ ቀድሞ ከነበረበት ቅርጽ፣ ክብደት፣ ስፋት ቀዝቶ በአጠቃላይ ሁኔታ በልጦና ልቆ የሚገለጽበት መንገድ ነው።

ካለው እወነታ ላይ ለማሳመር፣ ለማጣፈጥ፣ ስሜትን ለመያዝ (ለመቆንጠጥ) ሲባል የሚደረግ በእውነታው ላይ የመጨመር ቀለም የመቀባት ጉዳይ ነው::

እዚህ ላይ ግን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ማንሳት ተገቢነት አለው::

1. ግነት ደረጃ አለውን?
2. ደረጃ አለው ከተባለስ እስከየት ድረስ ነው?
3. የግነት ሂደቱ ባለ አንድ አቅጣጫ ነው ወይስ ባለ ሁለት አቅጣጫ?

ሰማየ ጠቀስ ቤትክን በሩቅ እያየሁ
እንባዬን ከውስጤ ከምር አዘንባለሁ
እንባዬ ጎርፍ ሆኖ ህንጻህን ቢያፈርሰው
ባህሩ ምኞቴ ተሳካ ማለት ነው::
እንባ እኮ ጎርፍ ነው ሃይለኛ ሙላት
ጠራርጎ የሚወስድ በትንሽ ቅጽበት
እኔም ምርር ብዬ በእምባ እምታጠበው
ያን ተራራ ቤትክን ወንዝ እንዲወስደው ነው::

ተ. ደጋሚ ድምጽ

በቃላትና በሃረጋት ውስጥ የሚገኙ ድምጾችን ስርአታዊነትን በተከተለ መልኩ ይሆነኝ በሎ፣ አንድን ግብ ለማምጣት ሲባል በመደጋገም ይመሰረታል::

ቃላቱን በቅርጽ አመሳስሎ በማምጣት ይመሰረታል::

ዋና አገልግሎቱም ለግጥሙ ሙዚቃዊ ቃናን በማላበስ ለስሜት ቅርበት እንዲኖረው ማድረግ ነው::

ምሳሌ

1. አባሮ ለመያዝ ሮጦ ለማምለጥ
ታግሎ ድል ለማድረግ ተምሮ ለመብለጥ
ተፈጥሮን ለማዘዝ ለመግዛት ለመንዳት

ከምርቱ ለማፌስ ከምንጩ ለመቅዳት
አምሮ ለመታየት ጸጉርን ለማበጠር
ያስፈልጋል ቀድሞ ሰው ሁኖ መፈጠር::
(አፈወርቅ ዮሃንስ: 1968: ስሜታዊ ገጥሞች: 39)

2. የነገሬን ውሉን አጥበቆ ለማሰር
ታደረ ሲበላ፣ ሲጠጣ፣ ሲጨፈር
ምን እንደደረሰ ሲነጋ ባስጠይቅ
ተተረተረ አሉኝ ቋጠሮ ሳይጠበቅ

በመጀመሪያው ግጥም ውስጥ ያሉት አብዛኞቹ ቃላት:

- ግሳዊ ስሞች ናቸው::
- በመነሻቸው ላይ "ለ" የሚለው ድምጽ ይገኛል::

በሁለተኛው ግጥም ውስጥ:

- የአብዛኞቹ ቃላት ቅርጽ ተመሳሳይ ነው::
- የቃላቱ መነሻም "ሲ " ነው::

## 2.3 አሰነኛኘት (VERSIFICATION)

(The act of composition of verse, or a study of the art of writing metrically.)

የሚከተሉት ነጥቦች ወይም አባባሎች አሰነኛኘት ለሚለው የመነሻ ጽንሰ ሃሳብ ይሰጡናል::

1. "ስነግጥም ቅርጽ አለው፤ የሃረጋት መገናኘት፣ የድምጽ ስልት አወራረድ፣ የመስመሮች እጥረት የሚያስከትለው ቁልቁል ጥድፊያ፣ የመስመሮች እርዝመት የሚፈጥረው ከባድ ተጎታችነት፣ የዜማው ሁኔታ ... ሁሉ በስነግጥም ውስጥ ይታያል (ሰለሞን ደሬሳ: 1963: ልጅነት: 08)::

2. "ስነግጥም የራሱ ህግና ስርአት አለው:: የሃረግ፣ የስንኝ፣ የዜማ፣ የምጣኔ፣ የቀለም፣ ... ባህሪያትና ልክ መጤን አለበት (ሃይሉ ገ/ዮሃንስ፡ 1968፡ *ፍንዳታ፡* 21)::

3. ቁጥሩን (ሚትሩን ወይም ምቱን) የተመደበ የስንኝ ስልትና ቤት ባልደነገገው የቃላት መረን አሂዶ ስነግጥም ማለቱ የባሰ ጸያፍ ማሰኘቱ አይቀርም (ጸጋዬ ገብረ መድህን፡ 1966፡ *እሳት ወይ አበባ*፡ 12)::

ከዚህ በላይ በሃገራችን የስነግጥም ባለሙያዎች የተሰነዘሩት አስተያየቶች ወደ አሰነኛኘት (Versification) ምንነትና በውስጡ ወደሚያካትታቸው ነጥቦች ይመሩናል:: አሰነኛኘት፡

- የግጥምን ያጻጻፍ ጥበብ፣ በተለይም ከቅርጽ ረገድ ያለውን ይመለከታል::

አሰነኛኘት፡

- ሃረጋቱና ስንኞቹ የሚመጠኑበት
- ምቱ የሚጠበቅበት
- ምጣኔው የሚወሰንበት
- ዜማው የሚስተካከልበት
- የቤት አመታት ስልቱ የሚጤንበት
- የቀለማቱ ሁኔታ ከግንዛቤ የሚገባበት

ነው::

በመሆኑም አሰነኛኘት ሲነሳ የሚከተሉት ነጥቦች ይነሳሉ::

- ሃረግ
- ስንኝ
- ቤት አመታት

- ምት
- ምጣኔ
- ቀለም

ቀጥሎ እነዚህን ነጥቦች አጠር አጠር በማድረግና በምሳሌ በማስደገፍ እንመለከታለን፡፡

## 2.3.1. ሀረግ

የተለያዩ ብያኔዎች ሲሰጡት ቆይቷል፡፡

የተሻለ የሚባለውም "የመጀመሪያውን ድምጽ ማሰማት ከጀመርንበት ጊዜ አንስቶ ከፊል እረፍት እስከምናደርግበት ድረስ ያለው የቃላት ስብስብ ወይም ቃል ሀረግ ይባላል" የሚለው ነው፡፡

እዚህ ላይ ግን ከፊል እረፊት የሚደረግበት ከአንባቢ አንባቢ ሊለያይ ስለሚችል ሃረግን በማመልከቱ ረገድም ከአንባቢ አንባቢ ሊለያይ እንደሚችል ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

ምሳሌዎች፡

1. አንድ የፋኑስ መብራት/ በግብሩ የኮራ
   እንዲህ ሲል ተጣላ/ ከብርጭቆ ጋራ፡፡
   (ከበደ ሚካኤል)

2. ለምንድ ነው አልኩኝ/ ለምን ምክንያት
   ይህ አለም መኖሩ/ አዱኛ ህይወት
   ህጻን መወለዱ/ አርጅቶ ሊሞት
   ለምንድነው አልኩኝ/ ለምን ምክንያት፡፡
   (መንግስቱ ለማ)፡፡

3. የወለደችው/ እናት አምጣ
   ለሙያ ሚውል/ ሰበዝ ግራምጣ

የሚያደባልቅ/ ዲቡን ከዲብ፡፡
ፈጥኖ እሚያረካ/ የቆንጆ ልብ፡፡
(ዮሃንስ አድማሱ)

በግጥማዊ ሀረግ አከፋፈል ጊዜ የሚከተሉትን ነጥቦች ከግንዛቤ ማስገባት ያሻል፡፡

- ጽሁፋዊ ምልክቶችን (ስርአተ ነጥቦችን)
  - ሃረጋት በስርአተ ነጥብ ረገድ ዝግ ስንኞች (run off lines) እና ክፍት ስንኞች (run off lines) ተብለው ይከፈላሉ፡፡
    - ዝግ ስንኞች የሚባሉት ስርአተ ነጥብ የያዙት
    - ክፍት ስንኞች የሚባሉት ስርአተ ነጥብ ያልያዙት
- ስሜት ሰጭ የግጥሙን ክፍሎች
- በግጥሙ ውስጥ ያሉ ንግግሮችን (ምልልሶችን)

## 2.3.2. ስንኝ (Verse)

ስንኝም እንደ ሃረግ ሁሉ የተለያዩ ብያኔዎች ሲሰጡት ቆይቷል፡፡
የሚከተሉት ከተሰጡት በያኔዎች ውስጥ በምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡፡

1. "ባንድ መስመር እስከ ቤት መምቻው ድረስ የሚገኘው የግጥሙ ሀረግ ስብስብ ስንኝ ይባላል" አለማየሁ ሞገስ፡፡
2. "በግጥሙ ቤት ቃላት የሚሰካኩበት መንገድ ስንኝ ይባላል" መንግስቱ ለማ፡፡

እነዚህ ሁለቱ ግላጼዎች የሚከተሉት ደካማ ጎኖች አሏቸው፡፡

- በጽህፈት ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡
- ስንኙን ለመለየት የተጻፈውን ማየትን ግድ ይላሉ፡፡
- ግጥም ደግሞ የሚደመጥ እንጅ የሚነበብ አይደለም፡፡
- አጠቃላይ ናቸው፡፡

- ተጨባጭነት ይጎድላቸዋል (ወደ ግላዊነት ያመዝናሉ)።

አንድ ሰው ግጥሙን በሚያነብበት ጊዜ አነባበቡ ሃረጋቱን እና ስንኞቹን የሚጠቁም መሆን አለበት።
ከላይ ያሉት ገለጻዎች ግን ይህ ይጎድላቸዋል።
ስለሆነም ሌላ የተሻለ ይህን ደካማ ጎን ለማሻሻል የሚረዳ ብያኔ መፈለግ ይሻላል።

የሚከተለው ብያኔ ስንኝን በተሻለ ሊገልጸው ይችላል።

> የመጀመሪያውን ድምጽ ማሰማት ከጀመርንበት አንስቶ ከከፊል እረፍት ከፍያለ አንጻራዊ ሙሉ እረፍት እስከምናደርግበት ድረስ ያለውን የሃረጋት ስብስብ ይይዛል።

ምሳሌዎች፡

1. እስኪ ሰውነቴ የኔ ገላ አፈሩ
   እንዴት አደረገህ አለም ቤት ያሳሩ
   ገና ለጋ ነበርሁ ከለጋም ቀንበጥ
   የዚህ አለም ሰዎች ያወጡኝ ከቅጥ።

2. ፈላስፋው ሲመክር አደራ ብሏል
   በምትሰራው ስራ ቀስ ብለህ ቸኩል።

4. አለም የጠላውን፣ ህዝብ ያረከሰውን፣ ያንን ብላሹን ሰው
   በዘመናት መሃል፣ ግኡዝ እሱነቱን፣ ትውልድ እንዳይረሳው
   በምስሉ ትይታ፣ ተጠብቆ እንዲኖር፣ ርዝራዥ ግብሩ፣
   የገማ ትዝታው
   እንዲሆን አስበህ፣ ከሆነ አጅሬ፣ ጂኦባኒ ባቲስታ፣ ካሜራ
   መስራትህ

እኛ ኑራ ሁሴን በረካነት ይንሱህ።

ስንኝን ለመለየት የሚከተሉትን ነጥቦች ከግንዛቤ ማስገባት ይበጃል።

- አንደበታዊነቱን
- ቅርጻዊነቱን
- መዋቅራዊነቱን

በቅርጻዊነቱ - በአብዛኛው አንድ የግጥም መስመር ነው።

በመዋቅራዊነቱ ቃላት ለታቀደ አላማ የሚቀናጁበት፣ በቅንጅቱም ኪናዊነቱ የሚመዘንበት ነው።

በአንደበታዊነቱ - በአንድ ሙሉ ትንፋሽ የሚነበብ ነው።

አንድ ስንኝ ቢያንስ አንድ ሀረግ ያስፈልገዋል።

ሀረግ ስንኝ የሚሆንበት (ሀረግና ስንኝ አቻ ቅርጻዊ መዋቅሮች የሚሆኑበት) ጊዜም አለ።

የሚከተለው ግጥም ለዚህ በምሳሌነት ይጠቀሳል።

. ሳላቅፈው
ሳልስመው
ያለፈ ዘመኔ
ወዳጄ ልቤ ሰው
ልጅነት ብቻ ነው።
(ፈቃደ አዘዘ)

## 2.3.3. ቤት

በተለያዩ ሰዎች መጠነኛ ልዩነት የሚታይባቸው ብያኔዎች ሲሰጡት ቆይቷል።

የሚከተሉት በምሳሌነት ይጠቀሳሉ።

1. "የቃል ማሳረፊያውና የዜማ መግቻው ቤት ይባላል። - - - በመጀመሪያው ቤት የሚገኘው የግጥሙ ቤት መምቻ፣ በመጨረሻው የሚገኘው ቤት ደግሞ ቤት መድፊያ ይባላል" መርሴ ሀዘን።

2. "በእያንዳንዱ ቤት ቃሎች ይሰካካሉ፤ ይሰናኛሉ" መንግስቱ ለማ።

3. "በየስንኙ መጨረሻ የሚገኘው የመጨረሻ ሆሄ ቤት ይባላል" አለማየሁ ሞገስ።

የተሻለ የሚባለውና የሚመቸው ከመንግስቱ ለማ ጋር የተያያዘው እና ከስንኝ ጋር የሚዛመደው ነው።
ይህም የሚከተሉትን ፋይዳዎች ያስገኛል።

- ግጥሞችን ባለ ሁለት ቤት ግጥም፣ ባለ ሶስት ቤት ግጥም፣ ወዘተ እያሉ ለመጥራት አመች ይሆናል።
- በስነግጥም ውስጥ የሚገኙ ስያሜዎችን አብዝቶ ግራ ከመጋባት ያድናል።

## 2.3.4. ቤት አመታት (Rhyme)

### 2.3.4.1 ምንነት እና ፋይዳ

ቤት አመታት አልፎ አልፎ በየሀረጋቱ፣ አብዛኛውን ጊዜ ደግሞ በየስንኞቹ መጨረሻ ላይ የሚመጡ ድመጾች መመሳሰልን ይመለከታል።

- በስነግጥም እና በዝርው መካከል ላለ ልዩነት በዋነኛ መስፈርትነት ይጠቀሳል።
- ጥንታዊነት ያለው የስነግጥም ፍሬ ነገር ተደርጎ ይቆጠራል።

ቤት አመታት የሚከተሉት ስነግጥማዊ ፋይዳዎች አሉት።

- የዜማ መመላለሻ በመሆን ያገለግላል (ግጥሙ በዜማ እንዲነበብ ያግዛል)።
- ድምጾችን በተወሰነ ስርአት (pattern) በማምጣትና በመደጋገም የስነግጥሙን ኪናዊነት ለመጠበቅ ያስችላል።

- የስነግጥሙን መዋቅር በመክፈቻና መዝጊያ ለመጠበቅና ለማወቅ ይረዳል::
- ስነግጥሙ ከአንባቢና ከአድማጭ ጋር ውህደት እንዲኖረው ያግዛል::
- በቀላሉ እንዲታወስ ለማድረግ ያስችላል::

በሀገራችን የስነግጥም ታሪክ ቤት አመታት ከፍተኛ ቦታ ሲሰጠው ቆይቷል:: ተሰጥቶት የቆየው ቦታም "ግጥም ያለ ቤት መምታት ስነግጥም ሊባል አይችልም፤ አይታሰብም" እስከማለት ይደርሳል::

በመሆኑም አብዛኞቹ ጀማሪ ገጣሚያን፣ በተለይም ስለ ግጥም መሰረታዊ ባህሪያት ግንዛቤው የሌላቸው የግጥማቸውን የተዋጣለት መሆን አለመሆን ቤት ከመምታቱ ወይም አለመምታቱ ጋር ብቻ ያያይዙታል::

ለቤት መምታቱ ብቻ ስለሚጨነቁም፣ ሌሎችን ጉዳዮች ችላ ስለሚሉም በአብዛኛው የግጥምን ባህሪ የሚያላብሱ ቃላትን በተገቢው ቦታ አያስገቡም::

ይህም ግጥማቸውን እንዲበላሽ ያደርግባቸዋል::

በዚህ ረገድ ሁልጊዜ ዳር ገጠም የሚባሉትን ግጥሞች የሚያኈሳድጉዱት የመገናኛ ብዙሃን ይጠቀሳሉ::

የስነግጥም ውበትና ብቃት የሚመዘነው ቤት በመምታቱ ብቻ አይደለም::

እንዲያው ቤት መምታትን ብቻ እያሰብን ቤት ለመምታት የሚያስችሉ ቃላትን ብቻ የምንመርጥ ከሆነ የሚከተሉት ችግሮች ይከሰታሉ::

- ከግጥሙ ጋር ግንኙነት የሌላቸውን ቃላት እንመርጣለን::
- ቃላቱና ሀረጋቱ ከግጥሙ ጋር ያላቸውን (ሊኖራቸው የሚገባውን) ትስስር እንዘነጋለን::
- ዘይቤያዊነታቸውን ችላ እንላለን::
- ምናብ ጫሪነታቸውን እንረሳዋለን::
- የሚጫወቱትን ግጥማዊ ፋይዳ እንተወዋለን::
- ክሊሼ አንጋሽ ቃላት በግጥሙ ውስጥ ይገቡብናል::

የሚከተለው ለዚህ ማስረጃ ይሆናል፡፡

"እንጻፍ ግጥም የቀላ
በደም እንጅ መች በሳልሳ፡፡"

እዚህ ላይ ፍጹም ወይም ከፊል የሃሳብ ግንኙነት ሳይኖራቸው ቤት እንዲመቱ እየተባለ የሚደረደሩ ቃል ግጥሞችን በምሳሌነት ማንሳት ይቻላል፡፡

ምሳሌ

የሃረር መፋቂያ ጥርስ ያነጣል አሉ
ፎቶሽን ላኪልኝ ለሚመጣው ሁሉ፡፡

## 2.3.4.2. የቤት አመታት አይነቶች

በአማርኛ የግጥም አጻጻፍ ውስጥ የተለያዩ የቤት አመታት ስልቶች አሉ፡፡

እያንዳንዱ ገጣሚ በሚከተሉት ነጥቦች መነሻነት አንዱን ሁለቱን፣ ሁሉንም የቤት አመታት ስልቶች ሊመርጥ ይችላል፡፡

- ሊከተል በፈለገው ስልት (በምርጫው)
- በችሎታው
- ሊያስተላልፍ በፈለገው ጉዳይ

ከአማርኛ ስነግጥም ውስጥ የተለያዩ የቤት አመታት ስልቶች ይገኛሉ፡፡

ቀጥለንም የቤት አመታት ስልቶችን ለመከፋፈል ከሚያገለግሉት መስፈርቶች ረገድ እንመለከታቸዋለን፡፡

### ሀ. በትግጥሙ ውስጥ ቤት የሚመቱት ድምጾች ከሚገኙበት ቦታ ረገድ

### 1. ወጫዊ ቤት አመታት (End rhyme)

የየስኞቹን መድረሻ ድምጾች መመሳሰል ይመለከታል፡፡
በአማርኛ የስነግጥም ታሪክ በአብዛኞቹ ገጣሚያን ግጥሞች ውስጥ ይገኛል፡፡

## 2. ውስጣዊ ቤት አመታት (Internal rhyme)

በየስንኞቹ ውስጥ የሚገኙትን የየሃረጋቱ መጽረሻ ጽምጾች መመሳሰል ይመለከታል፡፡ የተወሰኑ እና ጥሩ ችሎታ ያላቸው ገጣሚያን የሚገለገሉበት ስልት ነው፡፡

ምሳሌዎች

2. ክንዶችሽ አቀፉኝ፣ አቅፈው አባበሉኝ፣ አባብለው አስተኙኝ
ውጋቴን ነጥቀውኝ፣ ቁስሌን አዘናጉኝ
ከሰመመን ጀርባ ----
እሾህ ላይ ሊያነቁኝ
ቁርንጮ ሊያለብሱኝ
በማቅ ሊፈትጉኝ፡፡
(ደበበ ሰይፉ)

## ለ. ቤት ከሚመቱት ድምጾች መመሳሰል ረገድ

## 1. ጥብቅ ቤት አመታት (Exact rhyme)

የየስንኞቹ የመጨረሻ ድምጾች ፍጹም ተመሳሳይ ወይም አንድ አይነት ሲሆኑ የቤት አመታት ስልቱ ጥብቅ ነው ይባላል፡፡

ምሳሌ፡ ብ፣ ብ፤ ጋ፣ ጋ፤ ሌ፣ ሌ፤ ሆ፣ ሞ፣ ሶ፤ ወዘተ.

## 2. ልል ቤት አመታት (Start rhyme)

የየስንኞቹ የመጨረሻ ጽምጾች የመመሳሰል ደረጃ ፍጹም አንድ አይነት እስከመሆን ካልደረሰ የቤት አመታት ስልቱ ልል ይባላል፡፡

ምላሴ ን፣ ስ፣ ር፣ ክ፤ ና፣ ባ፣ ጋ፣ ላ፣ ዳ፤ ወዘተ.

## ሐ. ቤት በሚመቱት ድምጾች ተዋረዳዊ (ቁልቁላዊ) የአቀማመጥ እና ተመሳሳይነት ስርአት መነሻነት

በአብዛኛው በውጫዊ ቤት አመታት ውስጥ ይስተዋላል::

በዚህ ረገድ የተለያዩ የቤት አመታት ስልቶች አሉ::

ከነዚህ የቤት አመታት ስልቶች ውስጥ ገጣሚው እንደሚመቸው፣ እንደፍላጎቱ እና እንደምርጫው አንዱን፣ ሁለቱን ወይም ሁሉንም ሊገለገል ይችላል::

ዋናው ነገር የሁሉንም ስልቶች ጠንካራና ደካማ ጎን ጠንቅቆ ተገንዝቦ ለአንድ አላማ፣ ስልታዊ በሆነ መንገድ መገልገሉ ላይ ነው::

በዚህ ረገድ ዋና ዋና የሚባሉት የቤት አመታት ስልቶች የሚከተሉት ናቸው::

### 1. ሀ ሀ ሀ - - - ቤት አመታት

በግጥሙ ውስጥ የሚገኙት ስንኞች ከመጀመሪያው አንስቶ እስከ መጨረሻ ድረስ በሙሉ በአንድ አይነት ድምጽ መጨረስን ይመለከታል::

የሚደጋገሙት የቤት መምቻ ድምጾች ተመሳሳይነትም ጥብቅ ተሚባለው ይሆናል::

ይህ የቤት አታት ስልት በሀገራችን የአማርኛ ስነግጥም ታሪክ ጥናታዊ የሚባለው ስልት ነው::

የቤት አታት ስልቱን በሁለት መንገድ ከፍሎ መመልከት ይቻላል::

### ኢ.ስልታዊ

ስንኞቹ ቤት እንዲመቱ ሲባል ብቻ የሚቀርብ ነው::

እያንዳንዱ ስንኝን በተመሳሳይ ፊደል እንዲጨርስ ተብሎ ከመታሰብ ያለፈ ፋይዳ የለውም::

ግጥሙ ከመጀመሪያው አንስቶ እስከመጨረሻ ድረስ በአንድ አይነት ድምጽ መጨረሱ ግጥሙን አሰልች ከማድረግ ባሻገር ምንም ስነግጥማዊ ፋይዳ አይኖረውም::

አብዛኛውን ጊዜ በዘመናውያን እና በእውቅ ገጣሚያን ዘንድ አይዘወተርም::

በዚህ ስልት የተጻፉትን አብዛኞቹን ግጥሞች በተጻፉበተ ዘመን ረገድ ስንመረምራቸው ቀደምት ናቸው::
አለበለዚያም በአለንበት ዘመን "የግጥም መሰረቱ፣ መለኪያው ቤት መምታት ነው" ብለው በሚያምኑ የዘመኑ ገጣሚዎች ይዘወተራል::
የሚከተሉት ግጥሞች ለዚህ በምሳሌነት ይጠቀሳሉ::

## ስልታዊ

በመሰረታዊው ጉዳይ ከላይ ስልታዊ ካልነው ጋር ተመሳሳይ ነው::
ልዩነቱ ይህኛው አንድ አላማ ኖሮት፣ ሆን ተብሎ፣ ለግጥሙ ከቤት መምታት ባለፈ አንድ ፋይዳ ለማላበስ ሲባል ተግባራዊ የሚሆን መሆኑ ነው::
ገጣሚው የቤት አመታት ስልቱን አሰልችነቱን ቢገነዘብም ለአንድ አላማ፣ ለአንድ ግብ ብሎ የሚከተለው ስልት ነው::
ለምሳሌ ደስታን ለመግለጽ ልልልል...፤ ዝምታን ለመግለጽ ምምም.....፤ ንዝንዝን ለማመልከት ኝኝኝ....፤ ሩጫን መንደርደርን ለማመልከት ድድድ...፤ የውሻ ጩኸትን አግራሞትን ለመፍጠር ውውው...፤ ወዘተ
ስነግጥማዊ አላማውም ከገጣሚ ገጣሚ ሊለያይ ይችላል::
መርምሮ ማግኘቱም የአንባቢው ወይም የአድማጩ ድርሻ ነው::

የሚከተሉት ግጥሞች ለዚህ በምሳሌነት ይወሰዳሉ::

1. ... ወይ አንገላገል
እንደሚነድ ፍልጥ እንደሚንቀለቀል፤
በሳት ተያይዞ፤ እሳት የሚመስል፤
ልቤ ሲንቦገቦግ ሲሰማኝ ሲከስል፤

አከላቴ ሲግል
ነፍሴ ልውጣ! ልውጣ! እያለች ስትዞል፣
ህይወት ከሞት ጋራ ሲመናጨቅ በጥል፣
ጥላቻና ፍቅር . . . . . . . . . . . . . በጥል፣
አየሩ ጭስ ሲሆን አፍኖ የሚገል፣
እኔ ልቤ ቆስሎ ስሆን የሰው ቁስል፣
የተበደለው ሰው ተስማመቶ ከበደል፣
ለበደል አድልቶ ከኔ ጋር ሲታገል፣
ወይ አይገላግሉን! ወይ አንገላገል
(መስፍን ወ/ማርያም፡ 1967፡ *እንጉርጉሮ፡* 23)

2. የኔ ፍቅር

የኔ ፍቅር ላንቺ ከጉዳይ ባይገባም፣
ብታውቂኝ፣ ባታውቂኝ፣ አንቺ ባትወጂኝም
ፍቅሬ አይለወጥም፣
ለውጡን አልጠብቅም፣
ስሜቴ አይሸጥም፡፡
የኔ ፍቅር ላንቺ ቢጠቅምም፣ ባይጠቅምም፣
ክብሬ ነው ብትይ፣ ውርደት ነው ብትይም፣
ፍቅሬ አይለወጥም፣
ለውጡን አልጠብቅም፣
ስሜቴ አይሸጥም፡፡
የኔ ፍቅር ላንቺ ገንፍሎ ባይፈስም፣
አበድሁኝ፣ ሰከርሁኝ፣ ታመመሁኝ ባልልም
ፍቅሬ አይለወጥም፣
ለውጡን አልጠብቅም፣
ስሜቴ አይሸጥም፡፡

የኔ ፍቅር ላንቺ የምኞት እንፋሎት፣ ሽውታ አይደለም፣
አግኝቼም አልጠግብሽ! አጥቼ አልከዳም
ፍቅሬ አይለወጥም፣
ለውጡን አልጠብቅም፣
ስሜቴ አይሸጥም።
(መስፍን ወ/ማርያም፡ 1967፡ *እንጉርጉሮ፡* 23)

3. ጊዜ በረርክ በረርክ
ጊዜ በረርክ በረርክ
ጊዜ በረርክ በረርክ
ግና ምን አተረፍክ
ግና ምን አጎደልክ?
ሞትን አላሸነፍክ
ህይወትን አልገደልክ።
(ደበበ ሰይፉ፡ 1992፡ 96)

4. ኝ.ኝ.ኝ (ለአብዮተኛ ምሁራን)
"የመሬት ስሪት ይፍረስ
ባርነት ይገርሰስ" ስለው ያሰቃየኝ
በይሁዳ አንበሳ መፈክር እጅና እፌን እያሰረኝ
"አንተ የማኦ ቅጥረኛ የሌኒን ሰላይ" ያለኝ
በ66 ቀደመኝ
"ኢትዮጵያ ትቅደም!
ህብረተሰባዊ ትሁን!" እያለኝ
አዝማቼ ሆኖ አዘመተኝ
ጠፋሪዬ ሆኖ ቀፈደደኝ
ቀፍድዶ እሱው ለፈፈ።

ኮሚዩሊዝምን ሰበከኝ
ሰብኮ ደግሞ ሰደበኝ
ሰድቦ ለሰዳቢ ሰጠኝ
"አናርኪስት ወንበዴ
ቡርዥዋ ምሁር" እያለኝ።
እንዲህ እንዲህ እድሜ ተስፋዬን የነጠቀኝ
በአበሳዬ ተፍለቅልቆ ያንጓጠጠኝ
ጉልበት መንፈሴን መጥምጦ ህሊናዬን ያሳደፈኝ
በግንቦት 20ም ቀደመኝ
የ17ቱን መከራ ሻይ ቡና ላይ እያጫወተኝ
የገዛ አበሳዬን ለኔው እየጠቀጠቀኝ
"አቤት ያሳለፍነው ፍዳ!
ቀላል መሰለህ?" እያለኝ
ኢሰፓን ባፉ ጨፍጭፎ፣ "አውሬ ነበር ደርግ" እያለኝ
በዲሞክራሲና ነጻነት፣ ቱለቱላው ሊያደነቁረኝ
እሱው፣ ስለቻርተር እየሰበከኝ
እሱው፣ "ሰላም መረጋጋት! ብሄር ብሄረሰብ!" እያለኝ
እሱው "ትምክህተኛ ምሁር" ብሎ እየጐነጠኝ
አለሁ ለጉድ የፈጠረኝ
ከየመጣው ጋር እሚጋልበኝ
ነገ እሚለኝ፣ እየናፈቀኝ//

**(ፈቃደ አዘዘ፡ 1985፡ *ጨኸት፡* 40)**

**5.** ድብብቆሽ

ድብብቆሽ
ያንዱ አንዱን ስርቆሽ
እሷ በዚያ

'አየሁህ!'
እኔ በዚህ
'አየሁሽ!'
ድብብቆሽ
የካብ ለካብ ግርዶሽ
ድብብቆሽ
ያንዱ ላንዱ ስርቆሽ
ያየሁሽ - አላየሁሽ
ፍጥጮሽ
ድብብቆሽ
የሰው በሰው ስርቆሽ
ድብብቆሽ
የነማሙሽ ቅልጦሽ
ድብብቆሽ
የራስ በራስ ስርቆሽ
ድብብቆሽ
የራስ በራስ ጥልፎሽ
ድብብቆሽ
የራስ በራስ ግርዶሽ
ድብብቆሽ!...
ያልረጋ ሶስት ጉልቻ፣
እርባን የሌለው ግትቻ::
(አበራ ለማ፡ 1980፡ *የማለዳ ስንቅ፡* 33)

## ለ. ሀ ሀ፤ ለ ለ፤ ሐ ሐ፤ ወዘተ. ቤት አመታት

ይህ ከዘመን ረገድ በአማርኛው ስነግጥም ታሪክ ከላይኛው ቀጥሎ የመጣና በአሁኑ

ዘመንም ገጣሚያን በስፋት የሚገለገሉበት ነው፡፡

በዚህ የቤት አመታት ስልት በአንድ አይነት ድምጽ ቤት የሚመቱት ተከታታይ ስንኞች ቁጥር ሁለት፣ ሶስት፣ አራት ወዘተ. ሊሆን ይችላል፡፡

በተመሳሳይ ድምጽ ቤት የሚመቱት ስንኞች ቁጥር የሚወሰነውም በገጣሚው ምርጫ ነው፡፡

ስነግጥማዊ ፋይዳ

- አሰልችነትን ማስቀረቱ ነው፡፡

## ሐ. ሀለ ሀለ፤ መሰመሰ፤ ወዘተ. ቤት አመታት

ይህ የቤት አመታት ስልት መሰረቱ ኢትዮጵያዊ እንዳልሆነ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡

በአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግስት ለዘመናዊ ትምህርት ወደ አውሮፖ የሄዱ ኢትዮጵያውያን ይዘውት የተመለሱት ስልት ነው፡፡

በዚህ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱት ተክለሃዋርያት ተክለማርያም ናቸው፡፡

የሚከተሉት ግጥሞች ለዚህ በምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡፡

1. የሰው አውሬ

ምን አለብኝ ብሎ፤ ማን አለብኝ ብሎ
የማይቆጠብ ሰው፤
ራሱን አታሎ፤ ሰውንም አታሎ
የውሸት የከበረው፤
የነፍሱን ኡኡታ የህሊናውን ጽምጽ አፍኖ ሸንግሎ
እንቅልፍ የሚወስደው፤
አይንና ጆሮውን ከአእመሮው ገንጥሎ
ቅሬታ እማይገባው፤
ሌሎች ሲበሳጩ፤ ሌሎች ሲሸበሩ፤ ብዙ ነገር ጎድሎ

ሞልቶለት ደስ ያለው፣

ከዙሪያው መበስበስ ከዙሪያው መሻገት እሱ ተገንጥሎ

የማይቆረቁረው፣

የሰው አውሬ እሱ ነው፡፡

(መስፍን ወ/ማርያም፡ *እንጉርጉሮ፡* 1967፡ 8)

2. ህይወት ሽንተረር … ገመዷ

ነጠላዋ ዝሃው ላልቶ

ሲሰፋ ሲጠብብ መንገዷ

ማገ ከድር ተለያይቶ

የማለዳ ጀንበር ናፍቆት

ለመመንጠቅ ከአረንቋ ማጥ

ሲቃ ጉጉት ቅትት … ቅትት

ስንዘረጋ ለመጨበጥ

(አረጋሽ ሰይፉ እና ሌሎችም፡ 1967፡ እኛ 170 ግጥሞች፡104)

3. መሰላል

ለመንጠላጠያ ለእግር መራገጫ…

መሰላል ስንሰራ…

ከታች መደገፊያ…. ከላይ መወጣጫ

ስንደረድረው በተራ በተራ

አንዱንም ሳልጀምር ስንከራተት ገና

እኔ እንጨት ፍለጋ

ከዚያ ላይ ቁጢጥ አልክ…

ያንተ ሰው ሆነና…

አጥንትና ስጋ፡፡

(መቅደስ ጀንበሩ፡ 1990፡ 109)

4. ስንብት

ስንሰነባበት ... ያይናችን ስር ላልቶ
የእምባ ጎርፍ ጅረቱ
የራሰው ደረቴ ጨቅይቶ ጨቅይቶ
የታጠብኩበቱ ... የታጠብክበቱ
ኳ ብሎ ደረቀ .... ቅርፊት አበጅቶ
ትንፋሽህ ቢርቀኝ በዛና ጊዜያቱ
የደመና ብርታት የጉሙ መጨፍገግ
ተራራና ባህር ጎዳናና መንገድ
የብልጭልጭ ብዛት የሰው መተፋፈግ
አይቻላቸውም ፍቅርን ያጠፉት ዘንድ
ይሄ ነበር ቃሌ ... ይሄ ነበር ቃልህ
መአልት ሲፈራረቅ .... ቀን ቀንን ሸኝቶ
አሁን ግን ደከመኝ .. አቅሜ ሰነፈልህ
ጊዜን ያህል ነገር መሀላችን ገብቶ
አመታት ሲገፉ ልቤም ዘመመልህ
ተረታ መሰለኝ ሌላ ተመልክቶ
ያኔ ስንለያይ! .. ሲደለቅ ከበሮ
መሸኛ ተብሎ .. አታሞ ሲመታ
የሆዴን መንሰፈሰፍ የልቤን ሮሮ
ያስተጋባ ነበር እንባዬ በእሪታ
አልገባኝም እንጂ አሁን ነበር ማልቀስ
እንጥፍጥፍ ብለህ ከልቤ ስትወጣ
ልቤ እየተረታ ተሸንፎ በአዲስ
አይኔ ሲቅበዘበዝ ወረት እያመጣ
መታጠብ አሁን ነው .. ይልቅ እንላቀስ!!

***(መቅደስ ጀምበሩ፡ 1990፡ 93)***

## ቴክኒካዊ ግጥሞች

***1.*** **በቀበሮ ጉድጓድ**

**በቀበሮ ጉድጓድ ቀበሮ መስሏቸው**

**በቀበሮ ጉድጓድ ቀበሮ መስሏቸው**

ውሾቹ አጓሩ በዛ ጩኸታቸው
አየሩን በከለው
ምድሩን አገረኘው ትፋት ድንፋታቸው!
አይ የውሾች ነገር፣
ማን በነገራቸው
ማን ባስተማራቸው
አንበሳ እንደሆነ የሚጠብቃቸው
አንበሳ እንደሆነ የሚጠብቃቸው::
**(ደበበ ሰይፉ፡ 1980፡ *የብርሃን ፍቅር፡* 71)**

**2.** **የቁልቁለቱ ሀይል**

አንዱ ነገር ካንድ እየተጋመደ፤
እየተዛመደ፤
እየተዋለደ፤
በመቆየት ብቻ ቀኑ እየረፈደ፤
አዲስ አዲስ ነገር እየተለመደ፤
ሃይል እየበረደ፤
ጭምቱ እያበደ፤
ቁም ነገሩ ቀርቶ እየተቀለደ፤
በቁልቁለት ጉዞ ሁሉም ተጣመደ::
ተያይዞ ነጎደ፤
እየተካካደ::
ዳገት ላይ ሰው ጠፋ፤ አቀበት ከበደ፤
ሁሉም በሸርተቴ ቁልቁለት ወረደ::
ሰው ተዋረደ፤
ገንዘብ ተወደደ፤
በምነቱ፤ በፍቅሩ፤ በክብሩ ነገደ፤

በቁልቁለቱ ኃይል እየተገደደ፡፡

(መስፍን ወ/ማርያም፡ 1967፡ *እንጉርጉሮ፡* 9)

3. እንደ መግቢያ

ህህህ

ስትፏድድ

ስትባክን ውለህ

ትትት

ንፍሮህን ቃቅመህ

ዘባተሎህን ደርበህ

ችችች

አዛባና ሽንት

ከመሬት

የተኛህበትን አጎዛ

ዘልቆ ስታገኘው

ወገብህን ስትመቻች

ክክክ

ሾክ የወጋህን

ድንጋይ የመታህን

እየተመለካከትክ

ቅማልና ትኋን

የወጋህን አከላትህን

እየደባበስክ

ይይይ

መልከኛውና ሻቃው

ጸሃፊውና ዳኛው

ማዶ ለማዶ ተፋጦ

ያሳደግኸውን
የወለድኸውን

ሊቀማህ ሲተያይ
ኘኘኘ
በሆነ ባልሆነው
በየጊዜው
ስትጎተት ስትታሰር
የምትመካበት ህገ
ሲጠፋ
የምትለው አለኝ
ርርር
ሃብትህን ተገፈህ
መኖር አስጠልቶህ
ጦርህን ከጣራ
መዥርጠህ
ጫካ ቤቴ ብለህ
ስትዞር
ካገር አገር
ውውው
መንከራተት ሰልችቶህ
ህይወት አንገፍግፎህ
መሬት መሬት
አስመልክቶህ
ሲስብህ
እናት አባትህ
የረገፉበት

አጽመ ርስትህዐ

ትዝታው

አፍየሌለህ አንተ ዋቶ አደር

ሊሰማህ ይሆን -- ያ

ስትል የምሰማህ ያውቃል እግዚአብሃር?

4. ቋጥኙ

መሠረተ ጽኑ

የብረት ምሰሶ ነኝ ባይ

ቋጥኝ በቋጥኝ ላይ፤

ንፋስ ራሱን ያዞረው

ሳር ቅጠል ድንጋይ አፈር

ስብርባሪ ነገር

ሲኮረኩመው እንዳከከው

ሲገፈትረው እንደዳሰሰው፤

(ትእዝብቱ ብቻ እያሳቀው)

ግና አንዲት ጠብታ… አንዲት ጠብታ

ውሃ ተሰኝታ

አፈር ስትነክስ

ድንጋይ ስትጎርስ

ውቅያኖስ

(መርከብ እምታፈርስ)

እና መች ቀረለት መነጠቁ

ከግሽር ዳሱ መውለቁ

እንዲያ እንዳልተነከተከተ

እንዳልሳቀ፤

ወደ ቁልቁል

**ወረደ**

**ቋጥኙ**

**እየ**

**ተን**

**ሰቀ**

**ሰ**

**ቀ**

**(ደበበ ሰይፉ፡ 1980፡ 66)**

**5. እ**

**ሽ**

**ቅ**

**ድ**

**ም**

**ድ**

**ም**

**እንደ ሮጥኩ፣**

**ከጥላዬ ቀድሜ፣**

**ከ17 አመቴ፣**

**ይኸው ዛሬ፣**

**ሃምሳ**

**ምናምን**

**አመቴ፡፡**

**እንኳን**

**እኔ ላይ**

**ልደርስበት፤**

**ጥላዬ ላይም**

**አልቻልኩበት፡፡**

**አንዴ**

**እየቀደመ፣**

**አንዴ**

**እየተከተለ፣**

**ይኸው**

**እስከዛሬ አለ፡፡**

**እኩል እንኳን፣**

**የምንሆነው**

**በተፈጥሮ**

**ግዴታ ነው፡፡**

**ብቻ አለሁኝ፣**

**እስከዛሬ፣**

**እንደሮጥኩኝ…**

**ቀድሜ…**

**ከጥላዬ…**

**ባሳቤ…**

**(ፈቃደ አዘዘ፡ 1994፡ ህበሾች ይኑሩ 30)**

6. ***የመጀመሪያው ቀን***

**አየችው**

**ተያዩ**

**አየና ወደዳት**

ቀኑ ማታ ነበር
ወደ ሆቴል ሄዱ
ሁለት እራት መጣ
ብርጭቆ ተጋጨ
አየችው
ተያዩ
አያት
ተሳሳቁ
በጠረጴዛው ስር
ጭኑ ጭኗን ነካው
ሲያያት
ፈገግ አለች
አየችው
ፈገገ
እጇን በጁ ያዘው
ጠበቅ አደረጋት
ጠበቅ አረገችው
ከፈሉና ወጡ
በከሰለው ሌሊት
ሁለቱ ነደዱ
ትንፋሻቸው ጋለ
ቤቱ ተቃጠለ
ፍራሹ ነደደ
ፍቅር ተያያዘ።

7. ዘላለማዊው ካሳ አባ ታጠቅ
የቋጥኙ ላይ እሬሳ

የዚያ አምበሳ

የካሳ

በመቶ አመቱ ቢያገሳ

ስንቱን

ስንቱን ቀሰቀሰውሳ::

(ሰይፉ መታፈሪያ፣ 1977፣ ጽጌረዳ ብእር፡ 103)

8. የቁልቁለቱ ሀይል

አንዱ ነገር ካንድ እየተጋመደ፤

እየተዛመደ፤

እየተዋለደ፤

በመቆየት ብቻ ቀኑ እየረፈደ፤

አዲስ አዲስ ነገር እየተለመደ፤

ሃይል እየበረደ፤

ጭምቱ እያበደ፤

ቁም ነገሩ ቀርቶ እየተቀለደ፤

በቁልቁለት ጉዞ ሁሉም ተጣመደ::

ተያይዞ ነጎደ፤

እየተካካደ::

ዳገት ላይ ሰው ጠፋ፤ አቀበት ከበደ፤

ሁሉም በሸርተቴ ቁልቁለት ወረደ::

ሰው ተዋረደ፤

ገንዘብ ተወደደ፤

በምነቱ፤ በፍቅሩ፤ በክብሩ ነገደ፤

በቁልቁለቱ ኃይል እየተገደደ::

(መስፍን ወ/ማርያም፡ *እንጉርጉሮ፡* 1967፡ 9)

## የአንድን ቃል ቅርጽ በመለዋወጥ (ዘሮችን በመደጋገም) ሀባብን ማጉላት

**1.** **ሁሉም ያልፋል?!**

አላፊው ያልፍና - አላፊ ሲተካ
ባላፊው ቀን ባህሪ - አላፊ ሲለካ
አላፊ አይመስሌ ቀን - ያልፋል ጓዙን ይዞ
ተጉዞ እንደመጣ - ደሞ ሊያልፍ ተጉዞ።
አንዳንድ አላፊ ቀን - ሊያልፍ ሲንጎራደድ
እኔው ባልፍበትስ - ወዳይቀሬው መንገድ?!
ሳያልፍ አልፌበት - በተራው ሲናደድ
ቀንም ይማረራል
እንደኔ በተራው
"ሁሉም ያልፋል?!" ይላል
ቆሞ እንደሚቆየኝ
ቀድሜው አልፌ - ኋል ኋላዬን ሲያየኝ
ሁለዜ ወደዛ - ወደዚህ - ትልልፍ ትልልፍ
እተወሰነበት እመድረሻ ቅንፍ።
ባንድ ተጠሙረን እኔ እድልና ወቅት
"ሁሉም ያልፋል" ባለው በብርቱው አንደበት
ለኔም አለፈብኝ ለሱም አለፍኩበት።
**(ፈርማዬ አለሙ: 1990: 88)**

**2.** *የጭነት እቃዎች*
*ስንመጣ ተጭነን*
*ስንሄድ ተጭነን*
*ስንኖር ተጭነን*
*ስንሞት ተጭነን*
*ምንም ምን አይደለን*
*የጭነት እቃ ነን።*
***(ፈቃደ ሀበሾች ይኑሩ 111)***

ልዩ ልዩ ጥያቄዎች፡

1. የጊዜን መገስገስ፣ ከጊዜ እየተተካ መሄድ ከአምስት ስንኞች ባልበለጠ ግጥማዊ በሆኑ ቃላትና ሃረጋት ግለጹ።

2. የሚከተለውን ግጥም የቤት አመታት ስልት ስልታዊነት ወይም ኢስልታዊነት ከግጥሙ በተወሰዱ ማስረጃዎች በማጣቀስ ተንትን።

ባልተመቸ ጊዜ

ባልተመቸ ጊዜ፤ ባልተመቸ ቦታ፤
የክረምት ጸሀይ፤ የሌሊት ብልጭታ፤
ከመቅጽበት ታይታ፤
ለዛ ባለው ውበት፤ በህጻን ፈገግታ፤
እንዲያው በቀስታ፤ እንዲያው በችልታ፤
በማታውቀው ሃይልዋ ልቤ ውስጥ ገብታ፤
ያረፈች፤ የተኛች፤ ድብቅ ነፍስ ነክታ፤
አንቀሳቀሰችኝ ነቃሁኝ ላንድ አፍታ።
ባልተመቸ ጊዜ ባልተመቸ ቦታ፤
የክረምት ጸሀይ የሌሊት ብልጭታ።
በማላውቀው ህይወት በማላውቀው ምልአት በተስፋ በደስታ
ሳታውቅ ነከረችኝ። አየች ስንገላታ።
ቁም ነገሩን ሁሉ አድርጋው ጨዋታ
እሷ ተደበቀች። በርዋን በኔ ዘግታ።

(መስፍን ወ/ማርያም፡ 1967፡ *እንጉርጉሮ፡* 51)

3. በሚከተሉት ግጥሞች ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች በስነግጥም ውስጥ ቃላት

በሚመረጡበት ጊዜ ከግንዛቤ የሚወሰዱ ነጥቦችን ከግንዛቤ በማስገባት በራስህ ቃላትና ሃረጋት ሙላ፡፡

4. በሚከተሉት ግጥሞች ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች ግጥሞቹን በጻፏቸው ገጣሚያን ቃላትና ሃረጋት ምንም ሳትለውጥ አሟላ ወይም አሟይ፡፡

5. የሚከተሉትን ግጥሞች ከቤት አመታታቸው ረገድ ተንትን(ኝ)፡፡

6. በግጥም ውስጥ ቃላትን በተለመደ ፍቻቸው መገልገል ያለውን ደካማ ጎን እና ደካማ ጎኑን ለማስወገድ ከሚያገለግሉት ነጥቦች ውስጥ ዋና ዋና የሚባሉትን ጠቃቅሱ፡፡

7. በግጥም ውስጥ ሰፋ ያለ ፍች ያላቸውን ቃላት በተደራቢ ፍቻቸው መገልገል ተመራጭ ነው የሚባልበት ምክንያት ምንድነው?

8. "የአንድ ግጥም የኢዘርዛሪነት ደራጃ  የሚለካው በግጥሙ ማጠር ወይም መርዘም (በዙ ወይም ጥቂት ገጾች በመሸፈኑ) ነው" ረገድ ነው በሚለው ሃሳብ ትስማማላችሁን?

9.  አንዳንድ የስነጽሁፍ ባለሙያዎች ከዘይቤ ስነጽሁፋዊ ፋይዳዎች ውስጥ አንዱ ተጨባጩን ረቂቅ ማድረግ ነው ይላሉ፡፡ ይህም ለመሆኑ በስነግጥም ውስጥ የሚለገው ጉዳዩ እንዲጎላ ተጨባጭ እንዲሆን ነው እንጅ ረቂቅ እንዲሆን ነውን? የሚል ጥያቄን ያነሳሉ፡፡
ሁለቱን እንዴት ታስታርቃቸዋለህ(ሽ)?